# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር

# የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር የ2014 በጀት ዓመት የግማሽ ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

**ጥር 2014 ዓ.ም.**

**አዲስ አበባ**

## አርዕስት ገጽ


የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር የ2014 በጀት ዓመት የ6 ወራት ዕቅድ አፈጻጸም

መግቢያ........................2

የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር የ2014 በጀት ዓመት የ6 ወራት ዕቅድ አፈጻጸም................5

I. በዝግጅት ምዕራፍ የተከናወኑ ተግባራት........................5

II. በትግበራ ምዕራፍ የሚከናወኑ ተግባራት........................6

ሀ. ቁልፍ ተግባራት........................6

ለ. ዐበይት ተግባራት........................7

ፕሮግራም አንድ፡ ሥራ አመራርና ድጋፍ አስተዳደር........................7

ፕሮግራም ሁለት፡ የመስኖ ልማት ፕሮግራም........................21

ንዑስ ፕሮግራም አንድ፡ የጥናትና ዲዛንና ግንባታ ን. ፕሮግራም........................21

ንዑስ ፕሮግራም ሁለት፡ የአቅም ግንባታ መስኖ ቴክኖሎጂ ን. ፕሮግራም........................58

ንዑስ ፕሮግራም ሶስት፡ የአካባቢና ማህበረሰብ ልማት ን. ፕሮግራም........................60

ፕሮግራም ሶስት፡ የመስኖ መሠረተ ልማት አስተዳደር ፕሮግራም........................63

ፕሮግራም አራት፡ የቆላማና አርብቶ አደር አካባቢዎች ምርምርና ልማት ዘርፍ........................73

የድጋፍ፣የክትትል፣ ከክልሎችና ሌሎች ሰክተሮች ጋር ስላለው ቅንጅታዊ አሰራር........................74

III. በበጀት ዓመቱ 6 ወራት በማጠቃለያ ምዕራፍ የተከናወኑ........................76

IV. ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች........................77

## መግቢያ

መንግስት ባደረገው የሴክተር መ/ቤቶች አስፈጻሚ አካላትን በአዲስ መልክ እንዲደራጁ ባደረገው መሠረት የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር **በአዋጅ ቁጥር** 1263/2014 በአዲስ መልክ በሚ/ር መ/ቤት ደረጃ እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት ከዚህ በፊት በመስኖ ልማት ኮሚሽን፣ በሰላም ሚኒስቴር የፌደራሊዝምና አርብቶ አደር ልማት ዘርፍ የአርብቶ አደር እና ከፊል አርብቶ አደር ልማት ጋር የተያያዙ እና በሌሎች አካላት ይከናወኑ የነበሩ ተግባራት ለመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር እንዲሰጡ ተደርገዋል።

ሚ/ር መ/ቤቱም ከተሰጡት ተግባራትና ሃላፊነቶች መካከል በዋናነት የመስኖ ልማትን በማስፋፋት እና በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ውሃን ማዕከል ያደረጉ የልማት ፕሮጀክቶችን ግንባታ በወቅቱ በማጠናቀቅና ወደ ልማት በማስገባት ህብረተሰቡን ተጠቃሚ በማድረግ የኑሮ ሁኔታቸውን ማሻሻል ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በዚሁ መሰረት መ/ቤቱ በመስኖ ልማት እና የቆላማ አካባቢ ልማት ምርምር ዘርፎች ላይ ከ10 ዓመት ዕቅድ ተመንዝረው በዕቅድ ዘመኑ የታቀዱ ግቦችን ማሳካት የሚችሉ በርካታ ፕሮጀክቶች ላይ በጀት በማስመደብ እመርታ ያለው ለውጥ ለማስመዝገብ እንዲያስችለው ይህ የተቋሙ ወጥ የሆነ የተከለሰ የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

በዚህ የተቋሙ የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ውስጥ በመስኖ ልማት ዘርፍ 23 የመካከለኛና ሰፋፊ መስኖ ልማት ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክቶች እና 17 የመስኖ መሠረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች ታቅደዋል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዚህ የመስኖ ልማት ዘርፍ በበጀት ኣመቱ ቀሪ ወራት የበለጠ የተሻለ የአፈጻጸም ውጤት ማስመዝገብ እንዲችል ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ በጀት እና የጥራት ደረጃ እንዲጠናቀቁ በቢሮና በመስክ በመገኘት ያልተቋረጠ ክትትል የሚደረግ ይሆናል፡፡ የመስኖ ልማት ዘርፍ ዋነኛ ዓላማው ግብርናችንን ከተፈጥሮ ዝናብ ጥገኝነት በማላቀቅ የግብርና ምርትና ምርታማነትን እንዲሁም ጥራትን በማሳደግ የምግብ ዋስትናን በቤተሰብ፣ በአካባቢና በአገር አቀፍ ደረጃ ማረጋገጥ፣ ለአግሮ ኢንዱስትሪ ጥሬ እቃዎችን የማቅረብ የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ብሎም የማህበረሰቡንና የአገሪቱን ኢኮኖሚ በማሳደግ ረገድ የበኩሉን አስተዋጽኦ ማበርከት ስለሆነ የዘረፉን ግቦች በስኬት በማጠናቀቅና ለህብረተሰቡ ጥቅም ላይ ለማዋል ከፍተኛ ጥረት የሚደረግ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል የቆላማ አካባቢ ምርምርና ልማት ዘርፍ ዋና ኣላማ ልዩ ድጋፍ የሚሹ ክልሎችን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል ፍትሃዊ የልማት ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ሲሆን ይህን ግብ ለማሳካት በበጀት ዓመቱ በመንግስት በተመደበ በጀትና ከውጭ በተገኘ ዕርዳታና ብድር የሚካሄዱ ፕሮጀክቶች በዚህ

በተከለሰ ዕቅድ ውስጥ እንዲያዙ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር ባሉባቸው ክልሎች (አፋር፣ ሶማሌ፣ ጋምቤላ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝና ኦሮሚያ ክልሎችና ደቡብ ህዝቦችና ብ/ብ/ ክልልና ዋግህምራ ዞን በተለያዩ ዘርፎች በርካታ የግንባታ ፕሮጀክቶች በዕቅድ ተይዘዋል፡፡

በዚህ ሰነድ የቀረበው የ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ስድስት ወራት አፈፃፀም፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች እና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን አካቶ የተዘጋጀ ነው፡፡

# የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር የ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያው 6 ወራት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር በህግ የተሰጠውን ሥልጣንና ኃላፊነት ለመወጣት እንዲያስችለው በ2014 በጀት ዓመት ወይም በአራተኛው የፕሮግራም በጀት ዘመን (ከ2013-2015) አራት ፕሮግራሞች እና 3 ንዑስ ፕሮግራሞችን በማዋቀርና የፕሮግራሞቹንም አፈጻጸም ስኬታማ ለማድረግ በበጀት ዓመቱ ውስጥ በርካታ ሥራዎችን እያከናወነ ይገናል፡፡

የመስኖ ልማት ኮሚሽን በሁለት ፕሮግራሞች የተዋቀረ ሲሆን እነዚህም

ፕሮግራም አንድ፡ የሥራ አመራርና ድጋፍ ፕሮግራም

ፕሮግራም ሁለት፡ የመስኖ ልማት ፕሮግራም

ፕሮግራም ሶስት፡ የመስኖ መሠረተ ልማት አስተዳደር ፕሮግራም እና

ፕሮግራም አራት፡ የቆላማ አካባቢዎች ኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራም ናቸው፡፡

በዚህም መሰረት በ2014 በጀት አመት የመጀመሪያው ስድስት ወራት የታቀዱና የተከናወኑ ተግባራት ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## ክፍል ሁለት፡- የበጀት ዓመቱ 6 ወራት ዕቅድ አፈፃፀም ዝርዝር ሪፖርት

በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያው 6 ወራት ታቅደው የተተገበሩ የካፒታል ፕሮጀክቶች አፈፃፀም በዝርዝር ቀጥሎ በተመለከተው መሠረት ቀርቧል፡፡

## I. በዝግጅት ምዕራፍ የተከናወኑ ተግባራት

- የዘርፉን የ2012 በጀት ዓመት አፈጻጸም በማኔጅመንት አባላትና ሰራተኛው በጋራ ግምገማ ካካሄደ በኋላ የዘርፉን የ2013 በጀት አመት አመታዊ ዕቅድ በማዘጋጀት በማኔጅመንት አባላትና ሁሉም ፈፃሚ ባለበት በጋራ በመገምገምና ሰነዱን በማዳበር የመጨረሻው የበጀት አመቱ የድርጊት መርሀ ግብር እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡
- ለአገልግሎት ፈላጊ ህብረተሰብ የተቀላጠፈ አገልግሎት መስጠት እንዲቻል በመልካም አስተዳደር ዙሪያ በ2012 በጀት ዓመት የታዩ ችግሮችን በመለየትና ከተገልጋዮች የተገኙ ግብዓቶች በመነሳት የ2013 በጀት ዓመት የመልካም አስተዳደርና ከለውጥ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሥራዎች ዕቅድ በማዘጋጀትና ሠራተኛው ተወያይቶበት ግንዛቤ እንዲጨብጥ ተደርጓል፡፡
- በተቋሙ ጠንካራ ቁመና ያለው የለውጥ ሰራዊት መገንባት እንዲቻል ትኩረት ተሰጥቶ እንዲሠራ በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ተከናውኗል፡፡

- በተቋሙ የውጤት ተኮር እቅድን በየዳይሬክቶሬቱ ላሉ ሠራተኞች ሳምታዊ፣ ወርሃዊና አመታዊ ዕቅድ በማዘጋጀት በአፈጻጸሙ ላይ ክትትል ተደርጓል፡፡ በዚህም የሚታዩ ጥንካሬዎችና ድክመቶችን በመለየት ጥንካሬዎች ይበልጥ ተጠናክረው የሚሄዱበትን እና ችግሮችም እንዲቀረፉ ተደርጓል፡፡

## II. በትግበራ ምዕራፍ የተከናወኑ

## ሀ የቁልፍ ተግባር አፈጻጸም

- **የበላይና መካከለኛ አመራር ሁኔታ፡-**
- የበላይ አመራሩ የ2013 በጀት ዓመት የዝግጅት ምዕራፍ ስራዎችን በመገምገም በየደረጃው የሚገኙ አመራሮችና ፈጻሚ ሠራተኛው ግንዛቤ በመያዝ ለአፈጻጸሙ ዝግጁ የማድረግ ስራ ተከናውኗል፡፡
- ከፍተኛ አመራሩ ከእቅድ ዝግጅት፣ ትግበራና ክትትል ጀምሮ በተቋሙ የሚከናወኑ የለውጥና መልካም አስተዳደር ስራዎች አፈጻጸም ሪፖርት የሚገመግምና አቅጣጫ የሚያስቀምጥ ሲሆን በዝግጅት ምዕራፍ ወቅት የ2012 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም እና የ2013 በጀት ዓመት እቅድ ዝግጅት በተለይ የተቋም ለውጥ፤ የለውጥ ሰራዊት ግንባታ፣ የመልካም አስተዳደርና ኪራይ ሰብሳቢነት ትግሎችን መሰረት ያደረገ የተቋሙን አመራርና ሰራተኞች ማዕከል ያደረገ ግምገማዊ ውይይት ተካሂዷል፡፡
- ሠራተኛውን በተመለከተ፡- የስራ ሰዓት የማክበር፣ የእቅድ አፈፃፀም ግምገማዎች ላይ ተሳትፎ የማድረግ፣ አዳዲስ ሃሳቦችን ለመቀበል ዝግጁ መሆኑና ካይዘን ለመተግበር ተነሳሽነት ማሳየቱ መልካም ጅምር ላይ መሆኑ በበጎ ጎኑ ታይቷል::
- በበጀት ዓመቱ ውስጥ በለውጥና መልካም አስተዳደር ረገድ በተከናወኑ ሥራዎች አማካይነት የአብዛኛው ሠራተኛ አመለካከት ላይ ለውጦች መታየታቸውና በዚህም የሠራተኛውን የቡድን ስሜት በማሳደግ በስራ አካባቢ የሚከሰቱ ችግሮችን በጋራ ለመፍታት ጥረት ተደርጓል፣
- የለዉጥ ሰራዊት ግንባታ አፈፃፀም በተመለከተ፡- በበጀት ዓመቱ ውስጥ በተደረጉ የሠራተኞች የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች የሠራተኛውን ግንዛቤ ከመፍጠር አንስቶ ጠንካራ የለውጥ ሰራዊት መገንባት እንዲቻል ወቅታዊ ውይይት ማድረግ፡ ተልዕኮን መፈጸምና እርስ በእርስ በመማማር በሂደት የአመለካከት፣ የአሰራር፣ የአደረጃጀት እንዲሁም የእውቀት ክፍተቶች በመሙላት ረገድ መልካም ጅማሮዎች ታይተዋል፡፡ በተቋሙ በሚደረግ ክትትልና እገዛ ሠራተኛው በራሱ ያከናወናቸውን ስራዎች መገምገምና ያልተሰሩትን ከነምክንያታቸው መረዳት እና በስራ ቦታ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በዉይይት ለመፍታት፣ ስራን በእቅድ

በማከናወን እና አፈጻጸምን በመገምገም ረገድ አጥጋቢ ሥራዎች (በቀጣይ የበለጠ መስራቱ እንደተጠበቀ ሆኖ) ተሠርተዋል፡፡

- መንግስት ለሴቶች የሰጠውን ማበረታቻ/Affarmative action/ ከግምት ውስጥ በማስገባት ቅጥር በመፈጸም፣ በስልጠና በማብቃትና ወደ አመራር የማምጣት ስራ ላይ አመራሩ ድጋፍ አድርጓል፡፡
- የመልካም አስተዳደርን በተመለከተ፡- በተቋሙ ያልተፈቱ የሠራተኞችም ሆነ ሌሎች የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመለየት ተገቢው ምላሽ ለመስጠት ጥረት ተደርጓል፡፡
- **የቅሬታና አቤቱታ ስርዓት ትግበራ፡-** በተቋሙ ውስጥ ለሚገለገሉ ባለድርሻ አካላት እና ለተቋሙ ሠራተኞች ተቋሙ በሚሰጣቸው አገልግሎቶች እና አሰራሮች ዙሪያ ቅሬታም ሆነ አስተያየት ሲኖራቸው ለአስተያየት መቀበያ የሚሆኑ የሐሳብ መስጫ ሳጥኖች በተመረጡ ቦታዎች እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡
- **የኪራይ ሰብሳቢነትን አመለካከትና ተግባር ከመዋጋት አንጻር**
    - በሩብ ዓመቱ ውስጥ የቋሚ እና አላቂ ንብረቶች የመንግስት የግዢ ደንብና መመሪያን ተከትሎ እንዲከናወን ከየስራ ክፍሉ ጥያቄ የቀረበ ሲሆን የተሽከሪካሪዎች አጠቃቀምን በተመለከተም አንድ ተሽከሪካሪ በኃላፊነት ለአንድ አሽከርካሪ በመስጠት ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡
    - ሠራተኞች ለሥራ የሚጠቀሙባቸውን የመንግስት ንብረቶችና ሌሎች አገልግሎቶች (መብራት፣ ውሃ፣ ወዘተ) በጥንቃቄና በቁጠባ እንዲጠቀሙ ተገቢውን ምክር የመስጠትና የግንዛቤ ማስጨባጫ ሥራ ተሰርቷል፡፡
    - ሠራተኛው የመንግሰትን የስራ ሰአት አክብሮ ቢሮ እንዲገባ፣የስራ ሰአቱን ለመንግስት ስራ አገልግሎት እንዲያውል እየተደረገ ይገኛል፡፡
- የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ከማረጋገጥ አንጻር፡- ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ትስስርና ቅንጅትን አጠናክሮ ለመቀጠል በሚያስችልበት ሁኔታ ላይ ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡ ኪራይ ሰብሳቢነትንና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የደንበኞች ተሳትፎ አስፈላጊ በመሆኑ ተቋሙ ይህን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት ጥረት አድርጓል፡፡

# ለ አበይት ተግባራት

## ፕሮግራም አንድ፡ ሥራ አመራርና ድጋፍ አስተዳደር

**ዓላማ፡-** ለዓላማ ፈጻሚ ፕሮግራም ስትራቴጂክ አመራርና ቀልጣፋ የድጋፍ አገልግሎት በመስጠት ተቋሙ የተጣለበትን ተግባርና ኃላፊነት እንዲወጣ ማስቻል፡፡

በፕሮግራም አንድ የታቀፉት ድጋፍ ሰጭ ዳይሬክቶሬቶች የግዥና ኮንትራት አስተዳደር፣ የፋይናንስ አስተዳደር፣ የዕቅድና በጀት ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ፣ ንብረትና ጠቅላላ አገልግሎት፣ የውስጥ ኦዲት፣ የህግ አገልግሎት፣ የሰው ሀብት አስተዳደርና ልማት፣ የኮሙኒኬሽንና የውጪ ግንኙነት እና የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ሲሆኑ የእነዚህ ድጋፍ ሰጪ የሥራ ክፍሎች የበጀት ዓመቱ የ6 ወራት የዕቅድ አፈፃፀም በጥቅል ሲታይ በአጥጋቢ ሁኔታ ተከናውነዋል፡- ዝርዝር አፈጻጸሙም ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

## 1. ፋይናንስ አስተዳደር

- ከገ/ሚ/ር በወቅቱ ተጠይቆ የሚፈቀድ የመደበኛና የካፒታል የጥሬ ገንዘብ ፍላጐት፤ ተፈቅዶ የመጣውን የመደበኛና የካፒታል በጀት ዝርዝር በገቢ መመዝገብ በየወሩ የተዘጋጀ የመንግሥት በጀት አጠቃቀም ሪፖርት ማቅረብ 100%፣
- ከገ/ሚ/ር ተፈቅዶ የመጣውን የመደበኛና የካፒታል በጀት ዝርዝር በገቢ መዝገብ መያዝ 100%፣
- ከበጀት አንፃር በወጪ መዝገብ የሚመዘገብ የተረጋገጠ ከመንግሥት የተገኘ መደበኛና የካፒታል በጀት 100%፣
- ከመንግሥት የመደበኛና የካፒታል በጀት የሚገኙ ተረጋግጠው የሚመዘገቡ ወጪዎች 100%፣
- የቋሚና የኮንትራት ሠራተኞችን ደመወዝና አበል ክፍያ መፈፀም እንዲሁም የተለየዩ ተቀናናሾችን ለሚመለከታቸው አካላት ገቢ ማድረግ 3 ታቅዶ አፈጻጸም 100%፣
- ለዕቃዎችና ለአገልግሎቶች ግዥ፣ ለኮንሰልታንቶች፣ ለግንባታ፣ ለውሎ አበልና ለሥራ ማስኬጃ፤ ለካሳ፤ ለክልሎች፤ በባንክ የሚፈፀሙ እንዲሁም የሚወራረዱ ክፍያዎች 100% ተከናውኗል፡፡
- ከሳጥን የሚከፈል እንዲሁም በሳጥን የሚገኝ የተመዛዘነ ከብር 5,000.0 ድረስ የሆኑ የተለያዩ ክፍያዎችን መፈፀም 100%፣
- በቅድሚያ ለተከፈለ የውሎ አበልና የሥራ ማስኬጃ የተወራረደ ሂሣብ ሪፖርት ማዘጋጀት 3 ታቅዶ አፈጻጸም 100%፣
- በጄነራል ሰብሲደሪ ሌዠር ላይ የሚመዘገብ የመደበኛና የካፒታል በጀት አጠቃላይ እንቅስቃሴ ሪፖርት ማዘጋጀት 100%፣
- ተገቢው የሂሣብ ሥራዎች እና ዕርምት ተከናውኖባቸው የተጠናቀቁ ሰነዶችን አደራጅቶ በመያዝ ለኦዲተሮችም ሆነ ለተለያዩ ጥያቄ ለሚያቀርቡ ተገልጋዮች ዝግጁ ማድረግ 100%፣

- የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ በወቅቱ ዘግቶ በዉጪ ኦዲተሮች ማስመርመር እቅድ1 ክንው1፣
- `በየሩብ ዓመቱ ለኦዲት ዳይሬክቶሬት የፋይናንስ ሪፖርት በማዘጋጀትና በማቅረብ የሚደረግ እገዛ እቅድ1 ክንው1፣
- በውስጥና በውጭ ኦዲተሮች የቀረቡ የኦዲት ግኝቶች ላይ አስፈላጊውን የእርምትና የክትትል ሥራ ማካሄድ፣
- ቋሚ የቢሮ ዕቃዎችና የፅህፈት መሳሪያዎች ጥቅል ግኘ የክትትል ስራ ማካሄድ፣
- ነዳጅና ቅባት እና የመለዋወጫ ግዢ በእቅዱ መሰረት፣
- በግኘ ኤጀንሲ በኩል የሚገዙትን ግኘዎች ክትትል ማድረግን 33.33%፣
- ጥቃቅን ፕሮፎርማዎች ግኘ እና የፅዳት ዕቃዎች ጥቅል ግኘ የክትትል ስራማካሄድ በዕቅዳቸው መሰረት ተከናውነዋል፣

## 2. ዕቅድና በጀት ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ

### ዕቅድ ዝግጅት

- የኮሚሽኑ መ/ቤት የ2013 በጀት አመት የድርጊት መርሃ ግብር ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ቀርቧል፡፡
- በዕቅድ አዘገጃጀት ሂደት ዘርፊ ብዙ ጉዳዮች መካተታቸውን የማረጋገጥ ስራ ተከናውኗል፡፡
- የተቋሙ የ2014 በጀት ዓመት የበጀት ፍላጎት ጥያቄ ተዘጋጅቶ ለገንዘብ ሚኒስቴር ቀርቧል፡፡

### ክትትል፣ግምገማና ሪፖርት ዝግጅት

- የ2013 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ባለድርሻ አካላት በሚፈልጉት ፎርማት መሠረት አዘጋጅቶ ለመላክ በታቀደው መሠረት ሪፖርቱ ተዘጋጅቶ ከተገመገመ በኋላ ለሚመለከታቸው አካላት ተልከዋል፡፡
- በበጀት ዓመቱ ውስጥ የ4 ሰነዶች ወይም ሪፖርቶች ዝግጅት ጥራትና ወቅታዊነት አስመልክቶ ግብረ መልስ ለመስጠት በታቀደው መሠረት የበጀት ዓመቱ ግብረ መልስ በየሥራ ክፍሉ በአካል በመገኘት ተሰጥቷል፡፡
- በበጀት ዓመቱ በሪፖርት አዘገጃጀት ሂደት ዘርፊ ብዙ ጉዳዮች መካተታቸውን የማረጋገጥ ስራ በ4 ሰነዶች ላይ ለማከናወን በታቀደው መሠረት ተከናውኗል፡፡
- የፕሮጀክቶችን አፈጻጸም በመስክ ላይ ክትትል ማድረግን በተመለከተ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ባለሙያዎች ጋር በቅንጅት በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን፣ አንጎለላና ጠራ ወረዳ በመካሄድ ላይ ያለውን የአጂማ ጫጫን ሎት3 የግድብ ግንባታ እና የላይኛው ጉደር ግድብ ግንባታ እንቅስቃሴ የማየትና በግንባታው ላይ ለወጣቶች እየተደረገ ያለውን የሥራ ዕድል ፈጠራ

ከፕሮጀክቱ ማናጀርና ሌሎች ሃላፊዎች እንዲሁም ከወረዳው አስተዳደር ጋር ድጋፉ ተጠናክሮ መቀጠል በሚችልበት ሁኔታ ላይ ውይይቶች ማድረግ ተችሏል፡፡

**ለመረጃ ፈላጊዎች መረጃ መስጠትን በተመለከተ፡-**

- ወቅታዊ የዕቅድ፣ክትትልና ግምገማ መረጃዎችን በማደራጀትና ለተጠቃሚዎች ለመስጠት በታቀደው መሠረት አገልግሎት ለማግኘት ደብዳቤ አጽፈው ለመጡና መረጃው እንዲሰጥ በኃላፊዎች ታዞ ለዕቅድና በጀት ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት ደብዳቤው ሲመራ መረጃውን ለተለያዩ መ/ቤቶች እና ግለሰቦች መስጠት ተችሏል፡፡

**በጀት ዝግጅትና አስተዳደር**

- የበጀት ዓመቱ የበጀት ፍላጎት ተዘጋጅቶ ለገንዘብ ሚ/ር ቀርቦ የተፈቀደ ሲሆን የበጀት አጠቃቀሙንም በየወሩ መረጃዎችን በማሰባሰብ ሪፖርት የማዘጋጀት፣ የውሎ አበል ወጪን ለመቆጣጠር እንዲቻል ለኮሚሽኑ መደበኛ ሥራዎች በጥቅል የተፈቀደውን ለየሥራ ክፍሎች በመመደብና ወጪውንም በየጊዜው በመመዝገብ ክትትል የማድረግ ሥራዎች ተከናውኗል፡፡
- የ2014 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት የበጀት ጥያቄ ተዘጋጅቶ ለገንዘብ ሚኒስቴር እንዲላክ ተደርጓል፡፡

➢ የዕቅድና በጀት ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት የበጀት ዓመቱ ዕቅድ አፈጻጸም 91.0 በመቶ ነው፡፡

## 3. የኮሚኒኬሽንና ውጭ ግንኙነት

➢ *በበጀት ዓመቱ ታቅደው የተከናወኑ ተግባራት*

- ➢ የተለያዩ መገናኛ ብዙሃንን ተጠቅሞ መረጃ ከማሰራጨት አኳያ፤በቁጥር 15 የዜና መግለጫ/ ፕሬስ ሪሊዝ ማዘጋጀትና ለሚዲያ መላክ ታቅዶ 19(127%)፣
- ➢ በቁጥር 15 ቃለምልልስ ለማካሄድ ታቅዶ 13 (87%) እና
- ➢ በቁጥር 120 ጊዜ የሃገር ውስጥና የውጭ ፕሬስና/ የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች ሞኒተር ማድረግ ታቅዶ 100% ተከናውነዋል፡፡
- ➢ **የህትመት ስራዎች**
    - በቁጥር 1 ጊዜ መልዕክት መቅረፅና ማስተላለፍ ታቅዶ 1 (100%)፣
    - በቁጥር 4 አርቲክሎችን ማዘጋጀትና መጠቀም ታቅዶ 6(150%) እና
    - በቁጥር 100 በራሪ ወረቀቶችን ማዘጋጀትና መጠቀም ታቅዶ 100% ተከናውነዋል፡፡
- ➢ **ሁነት ማዘጋጀትና መድረክ መምራት**
    - በቁጥር 7 ሁነት ማዘጋጀትና መድረክ መምራት ታቅዶ 9(129%)፣
    - በቁጥር አንድ የሰንደቅ አላማ ቀን ማክበር ታቅዶ 1(100%)፣

- የነጩ ፖስታ ጎርፍ ለነጩ ቤተ-መንግስት የመላክ ስነስርዓትን ማስተባበር ተከናውነዋል፡፡

➢ **መረጃን በወቅቱና በአግባቡ ለመረጃ ፈላጊና ለሚመለከተው አካል መስጠት**

- በቁጥር አንድ ጊዜ የመረጃ ማዕከላት ማጠናከር ታቅዶ 1 /100%/ እና
- በቁጥር 15 መረጃ ፈልጎ በአካል ለሚመጣ ቶሎ መረጃ መስጠት ታቅዶ 14 (93%) ተከናውነዋል::

➢ **የውስጥ ኮምዩኒኬሽን ማጠናከር**

- በቁጥር 1 ጊዜ የተቋሙን ሠራተኞች በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ ማወያየት ታቅዶ 2 /200%/፣
- በተቋሙ ዌብ ሳይት ፌስ ቡክ ላይ በቁጥር 15 ወቅታዊ መረጃ መጫን ታቅዶ 20/133%/፣
- በቁጥር ሁለቴ የመልካም ምኞት መግለጫ ካርድ ዝግጅትና ስርጭት ታቅዶ ህትመት አልተከናወነም፡፡ ነገር ግን ፖስት ካርዱ ተዘጋጅቶ በሚኒስቴር መ/ቤቱና በዳይሬክቶሬቱ ፌስ ቡክ ላይ ሶስቴ ተጭነዋል::
- በቁጥር 12 መረጃዎች በፊልምና በፎቶ ቀሪጸ መያዝ ታቅዶ 14 /117%/፣
- በቁጥር 6 መረጃዎችን በፎቶ ቀርፆ መያዝ ታቅዶ 7(117%)፣
- በቁጥር 6 መረጃዎችን በቪዲዮ ቀረፃ መያዝ ታቅዶ 7/117%/ ተከናውነዋል፡፡
- በቁጥር 3 ስልጠና ማስተባበር እና በቁጥር 2 ከፍተኛ የህዝብ ግንኙነት ባለሙያ ቅጥር ታቅዶ አልተከናወነም፡፡
- የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ቴሌግራም ቻናልና ዩቲዩብ ቻናል ተከፍተው መረጃዎች ለመጫን በእንተርኔት ችግር ምክንያት መጫን አልተቻለም፡፡
- በቁጥር አንድ የሚዲያዎች የልማት ቦታ ጉብኝት ማስተባበር ታቅዶ አልተከናወነም፡፡

## 4. የንብረትና ጠቅላላ አገልግሎት

- በግዥም ሆነ በእርዳታ የመጡ ቋሚና አላቂ ዕቃዎች በአግባቡ ተመዝግበዉ የስርጭት ስራዎች እንዲከናወኑ ተደርጓል፡፡
- የተሽከሪካርዎችን አጠቃላይ መረጃ በመያዝ ጥገና የሚያስፈልጋቸዉን ተሽከርካሪዎች የማስጠገን ስራ ተከናዉኗል፡፡
- የስምርት ስራን በተመለከተ በተለያዩ ጊዜ ለሰርቭስና መስክ የሚወጡ የናፍጣና ዘይት ክትትል ስራ ተሰርቷል፡፡
- አጠቃላይ የተሽከርካርዎች እስፐር ፓርት በሲስተም ተጠይቆ ግዥ ተፈፅሟል ፡፡

- ተሽከርካሪዎች የመስክ ስራ እና 1170 ጊዜ ለከተማ ስራ ተሽከሪካርዎች በምልልስ እንዲሰሩ ተደርጓል፡፡
- 33 ተሽከሪካርዎች በስራ ላይ እንዲሁም 20 ተሽከርካርዎች ጥገና ተደርጎላቸዉ በስራ ላይ ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪ አንድ ሞተር ሳይክል በስራ ላይ ይገኛል፡፡ በሌላ በኩል 1 ተሽከርካሪ ለመከላከያ በጊዜያዊነት ሲመደብ 2 ተሽከሪካሪዎች በቀድሞ ኮሚሽነሮች እጅ ይገኛሉ፡፡
- የስምርት ስራ እና የነዳጅ ስርጭት አጠቃቀም በተመለከተ በአጠቃላይ በ6 ወራት የናፊጣ እና የበንዚን ወጪ ድምር 747,094.60 (ሰባት መቶ አርባ ሰባት ሽህ ዘጠና አራት ብር ከ60 ሳንቲም) ስራ ላይ ዉሏል ፡፡
- ከቶታል ካሚፓኒ ለ51 ተሽከሪካርዎች የሚሆን የነዳጅ መግዣ ካርድ ተገዝቷል፡፡
- ከዉስጥና ከዉጪ ኦዲተሮች የሚቀርቡ ምክሮችና ግኝቶች ላይ አስፈላጊዉን እርምትና የክትትል ስራ ተደርጓል፡፡
- የቢሮዉ የዉሃ፣ የመብራት፣ የስልክና የኢንተርኔት የአገልግሎት ክፍያ ተፈጽሟል፡፡
- በ2013 በጀት ዓመት የፓምፕ ስርጭት ለክልሎች ሲከፋፈል ሊወሰዱ ባለመቻላቸዉ በአደራ መልክ ተቀብለን ካቆየናቸዉ ዉስጥ ለአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት 51 ፓምፕ እና ለበንሻንጉል ጉሙዝ 16 ፓምፕ በድምሩ 66 ፓምፖች እንዲረከቡ ተደርጓል፡፡
- ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ተካህዷል::

ከዕቅድ ዉጪ የተሰሩ ስዎች

- የመስኖ ልማት ኮሚሽን ወደ መስኖና ቆላማ አከባቢ ሚ/ር በማደጉ ምክንያት ከዉሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር መ/ቤት ወደ አዲሱ የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስተር መ/ቤት ዝዉዉር በመደረጉ ምክንያት ከእያንዳንዱ ባለሙያ የቢሮ ቋሚ ንብረቶችን በመረከብ ለሚኒስቴር መ/ቤት የማስረከብ ስራ በተጨማሪ ከሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ቋሚ ንብረቶችን በመረከብ ለባለሙያዎች የማስረከብ ስራ ተሰርቷል፡፡
- ከግብር ሚንስቴር 3 ተሽከሪካርዎች በማምጣትና ገቢ በማድረግ ስራ ላይ እንዲዉሉ ተደርጓል፡
- ከሰላም ሚኒስቴር ቋሚ እቃዎች ማለትም የፈርንቸር ዕቃዎችን በመረከብ ላልደረሳቸዉ ባለሙያዎች የማደል ስራ እየተሰራ ይገኛል፡

## 5. የህግ አገልግሎት

በ6 ወራት ውስጥ 28 የውል ስምምነት ሰነዶች ተረጋግጠዋል ይህም የዕቅዱ 93.3 % ነው ፡፡

በ6 ወር ውስጥ 30 የሕግ አስተያየቶችን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎችና የሥራ ክፍሎች ተሰጥተዋል ይህ የዕቅዱን 62.5 % ነው ፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተከሰሰባቸውና በከሰሰባቸው የፍትሐብሔር መዝገቦች ዙሪያ

- በኢትዮ ናይል የመስኖና ድሬይኔጅ ፕሮጀክት ጽ/ቤት አማካኝነት እየተከናወነ ባለው የተፋሰስ እንክብካቤ ሥራ ጋር በተያያዘ በአካባቢው በሚገኝ ወንዝ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው አርሶ አደሮች በጠቅላላ የገንዘብ መጠናቸው ብር 1,869,264.87 ( አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ስልሳ ዘጠኝ ሺህ ሁለት መቶ ስልሳ አራት ብር ከሰማንያ ሰባት ሳንቲም ) በሆነ አስራ ሶስት መዝገቦች በሚኒስቴር መ/ቤቱ ላይ የካሳ ክፍያ ክስ አቅርበውና ዳይሬክቶሬታችንም መልስ ሰጥቶ ጉዳዩ በተለያየ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡

- ከአርጆ ደዴሳ መስኖ ልማት ኘሮጀክት ጋር በተያያዘ 2 መዝገገቦች ለተመሰረተብን ክስ በኦሮሚያ ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት ቡኖ በደሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነፃ ተሰናብተን መዝገቡ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ነቀምት ተዘዋዋሪ ችሎት ይግባኝ ተጠይቆበት በጊዜ ቀጠሮ ላይ ይገኛል፡፡

- በድምሩ የብር 2,613,975 .95 (ሁለት ሚሊዮን ስድስት መቶ አስራ ሶስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ አምስት ከዘጠና አምስት ሳንቲም) ውል ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር የነበራቸው ሁለት የሥራ ተቋራጮች በገቡት የውል ግዴታ መሠረት ግዴታቸውን ሊወጡ ባለመቻላቸው የወሰዱትን ከላይ የተጠቀሰውን የቅድመ ክፍያ ብር ተመላሽ እንዲደደደርጉ የክስ አቤቱታ አቅርበን እና ክርክር ተደርጐ በሁለቱም መዝገቦች ከላይ የተጠቀሰውን ገንዘብ ሥራ ተቋራጮቹ እንዲከፍሉ አሰውስነን አንዱ መዝገብ ይግባኝ ተጠይቆበት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በቀጠሮ ላይ የሚገኝ ሲሆን የአንዱ መዝገብ አፈፃፀም በመታየት ላይ ይገኛል ፡፡

- በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት (ሰሜን ጎንደር) በመታየት ያሉ መዝገቦች ብዛት 4 ሲሆን መዝገቦቹ የያዙት ( ክስ የቀረበበት) የገንዘብ መጠን 13,700,946.21 (አስራ ሶስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሺህ ዘጠኝ መቶ አርበ ስድስት ብር ከሃያአንድ ሳንቲም ) በቀጠሮ ላይ ይገኛል
- ድምራቸው ብር 44,665,333.90 (አርባ አራት ሚሊዮን ስድስት መቶ ስድሳ አምስት ሺህ ሶስት መቶ ሰላሳ ሶስት ብር ከዘጠና ሳንቲም) በሆነ በሁለት መዝገቦች በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚኒስቴር መ/ቤታችን ላይ የክስ አቤቱታ ቀርቦ በመታየት ላይ ይገኛል

- በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሁለት መዝገቦች ይግባኝ ቀርቦባቸው በመታየት ላይ ይገኛል
- በኢትዮ ናይል የመስኖና ድሬይኔጅ ፕሮጀክት ጽ/ቤት የኮንትራት ሰራተኞች የነበሩ ሁለት ግለሰቦች የቅጥር ውላችን የተቋረጠው አለአግባብ ነው በሚል በባህርዳር ወረዳ ፍርድ ቤት የብር 548,000 በሚኒስቴር መ/ቤቱ ላይ ክስ አቅርበው እና ምላሽ ሰጥተን በቀጠሮ ላይ ይገኛል፤
- በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት 16 የፍ/ብሔር መዝገቦች በመታየት ላይ የሚገኙ ሲሆን መዝገቦች የያዙት (ክስ የቀረበበት ) የገንዘብ መጠን 3,603,000 በተለያየ ደረጃ በቀጠሮ ላይ ይገኛሉ
- ከቆጋ የመስኖ ግድብ ጋር በተያያዘ ግንባታውን ያከናወነው ቻይና ጃንግዚ የተባለ ሥራ ተቋራጭ ድርጅት ያልተከፈለኝ ብር 27,191,681.28 (ሃያ ሰባት ሚሊዮን አንድ መቶ ዘጠና አንድ ሺህ ስድስት መቶ ሰማንያ አንድ ብር ከሃያ ስምንት ሳንቲም) እና የአሜሪካን ዶላር 959,086.82 ( ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ሺህ ሰማንያ ስድሰት ከሰማንያ ሁለት) ክሱ በቀረበበት ወቅቱ በነበረው የምንዛሪ ተመን መሠረት (1USD= 36.72 ETB) በማስላት በድምሩ 62,409,349.31(ስድሳ ሁለት ሚሊዮን አራት መቶ ዘጠኝ ሺህ ሶስት መቶ አርባ ዘጠኝ ብር ከሰላሳ አንድ ሳንቲም) ከወጪ እና ኪሳራ ጋር ይከፈለኝ በማለት በውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር ላይ የክስ አቤቱታ አቅርቦ የነበረ ቢሆንም ጉዳዩ የሚመለከተው የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴርን ነው በሚል በክሱ ጣልቃ እንድንገባ ተጠይቆ ምላሻችንን አቅርበን እና በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ክርክር ተደርጎ ለብይን በቀጠሮ ላይ ይገኛል፡፡
- ከላይኛው ጉደር የመስኖ ግድብ ግንባታ የካሣ ክፍያ ጋር በተያያዘ በሁለት መዝገብ የብር 1,854,725 ክስ በሚኒስቴር መ/ቤታችን ላይ ቀርቦ ምላሽ ሰጥተን በቀጠሮ ላይ ይገኛል

## 6. የውስጥ ኦዲት

- የሥራ እቅድ ማውጣት (የኦዲት፣የውስጥ አሠራርን ማእከል ያድረገና የሥራ ክፍሉ የግኘ እቅድ) እቅድ ሦስት ክንውን ሦስት አፈጻጸም 100%፤
- የበጀት ዓመቱን የፈሰስ ሂሳብ መሥራት አንድ የተጠቃለለ ሪፖርት ማውጣት፤ እቅድ አንድ ክንውን አንድ አፈጻጸም 100%፤
- በየሩብ ዓመቱ የሳጥን ቆጠራ ሥራ መሥራት እቅድ የ2013 በጀት መዝጊያን ጨምሮ አምስት ክንውን ሦስት፣

- በግዥ ሠራተኛ እጅ የሚገኘውን ጥሬ ገንዘብና እንደ ጥሬ ገንዘብ የሚቆጠሩትን ተንጠልጣይ ሰነዶች መቁጠር መመዝገብና መተማመኛ መቀበል፣ በመመሪያ የተፈቀደላቸውን ሌሎችን ሥራ ክፍሎች ጥቃቅን ወጪ (የፒቲ ካሽ) ቆጠራ ማድረግና መተማመኛ መቀበል፣
- ወርሃዊ የሳጥን ሰነድ ቆጠራ ማድረግ እቅድ 6 ክንውን 100%፣
- የመደበኛ በጀት የገቢና የወጪ ሂሳብ አመዘጋገብ እና አያያዝ እንዲሁም አጠቃቀሙ በመመሪያው መሰረት ስለመሆኑ በኦዲት ምርመራ ማረጋገጥ፤ የ2013 አራተኛ ሩብ ዓመት ኦዲት ምርመራን ጨምሮ የግማሽ ዓመቱ እቅድ ሶስት አፈጻጸም ሁለት (የ2013 ዓመት የፈሰስ ሂሳብ እና የአራተኛ ሩብ ዓመት) ተሠርቷል፤ አፈጻጸሙም 67%፣
- የ2013 አራተኛ ሩብ ዓመቱ ገቢ እና የወጪ ሂሳብ ሰነድ ምርመራ ተሠርቷል፣
- ግንባታቸው የተጠናቀቁ እና ርክክብ የተደረጉትን ፕሮጀክቶችን በአካል ተገኝቶ የምልከታ ሥራ መሥራትና ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ሪፖርት ማድረግ እቅድ ሦስት ክንውን ሁለት (አፈጻጸም 67%)፣
- የክዋኔ ኦዲት ሥራ መሥራት እቅድ አንድ ክንውን 1/3 (አፈጻጸም33%)፣
- የኦዲት ክትትል ማድረግ የስድስት ወሩ እቅድ ሁለት ክንውን ሁለት አፈጻጸም 100% ተከናውኗል፣
- ሌሎች ሥራዎችን መሥራት፤ ሠራተኛና ሥራ ክፍሎች የምክር አገልግሎት መስጠት፤ የሥራ ድጋፍ ማድረግ፤ የፎረም ስብሳባ ላይ መሳተፍ እና የኢፍሚስ ስልጠና ዘግይቶም ቢሆን ስልጠና ተወስዷል፡፡
  - የዳይሬክቶሬቱ የስድስት ወራት አማካይ አፈፃፀም 85.22% ነዉ፡፡

## 7. የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ

- በመ/ቤታችን ሴት ሰራተኞች በስራ ዕድል ፈጠራ ዙሪያ ስልጠና መስጠት 50 ታቅዶ መስሪያ ቤቱ በአዲስ እየተደራጀ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ማከናወን ስላልተቻለ አደረጃጀቱ ሲጠናቀቅ በቀጣይ የሚከናወን ይሆናል፡፡
- ስርዓት ፆታ እና የመስኖ ልማት አካታችነት ላይ ለሴቶች፣ወጣቶች እና አጋር አካላት ስልጠና መስጠት ዕቅድ ወ 30 ሴ 35 ድምር 65 ሰው መስሪያ ቤቱ በአዲስ እየተደራጀ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ማከናወን ስላልተቻለ አደረጃጀቱ ሲጠናቀቅ በቀጣይ የሚከናወን ይሆናል፡፡
- በበጋ መስኖ ልማት በስንዴ ምርትና በአትክልት ፍራፍሬ ተደራጅተዉ የሚያለሙ ወጣቶችን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ዕቅድ 1 ክንዉን 1 ወይም አፈጻፀሙ 100%፣

- በቆጋ መስኖ ልማት ላይ ተደራጅተዉ ለሚያለሙ 200 በላይ ለሚሆኑ ሴቶችና ወጣቶች የድጋፍና ክትትል ስራ በማድረግ በስራ ዕድል ፈጠራ ዙሪያና በሚያመርቱት ምርት ዙሪያ የገበያ ትስስር ፣በማህበራዊ ለዉጥ እንዲሁም በቁጠባና በኢኮኖሚያዊ ዕድገት ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ተከናዉኗል፡፡
- ጎንደር ርብ መስኖ ፕሮጀክት የተለያዩ የበጋ አትክልትና ፍራፍሬ ተደራጅተዉ ለሚያለሙ 70 ሴቶችና ወጣቶች በስራ ዕድል ፈጠራ እንዲሁም ለሚሰሩት ስራ የኢኮኖሚ ለዉጥ ለማምጣት ቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ በቁጠባና በብድር አመላለስ ዙሪያ የግንዛቤ ፈጠራ ስራ ተሰርቷል፡፡ በቀጣይም የመስኖ ልማት ፕሮጀክቱ ካለበት ክልል ተጠሪ ቢሮ እንዲሁም ወረዳ የጥቃቅንና አነስተኛ ስራ ዕድል ፈጠራ ኢንተርፕራይዝና ከግብርና ጋር በጋራ በመሆኑ ተደራጅተዉ ለሚያለሙ ወጣቶችና ሴቶች የድጋፍና ክትትል ስራዉ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡
- ዓለም አቀፍ የነጭ ሪባን ቀንን በተለያዩ ዝግጅቶች ማክበር ዕቅድ 42 (ወ 18 ሴ 24) ክንውን 66 (ወ 27 ሴ 39) ወይም ከዕቅድ በላይ 157% ተፈጽሟል፡፡ የዘንድሮዉ የነጭ ሪባን ቀን /ፀረ ጾታዊ ጥቃት ቀን/ የተከበረዉ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ 30ኛ ጊዜ በሀገራችን ደግሞ ለ16ኛ ጊዜ የሚከበር ሲሆን መሪ ቃሉም ‹‹ሰላም ይስፈን በሴቶችና ህጻናት ላይ የሚደርስ ጥቃት ይቁም›› በሚል የተከበረ ነው፡፡
- ሁሉም ዳይሬክቶሬቶች የሴቶችን፣ ህፃናትና ወጣቶችን ጉዳይ በእቅዶቻቸው እንዲያካትቱ /ሚኒስትሪም/ በደብዳቤ በማሳወቅ ሜኒስትሪም አድርገዉ ወይም አካተዉ እንዲሰሩ ተደርጓል፡፡
- የተገልጋይ ፍላጎት ጥያቄ ምላሽ ማግኘታቸዉን ማረጋገጥ በዕቅዱ መሠረት ተከናውኗል፡፡

➢ የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት የበጀት ዓመቱ አፈጻጸም 83.3 በመቶ ነው፡፡

## 8. ሰው ሀብት አስተዳደርና ልማት

- የዳይሬክቶሬቱን ዓመታዊ እቅድ በማዘጋጀት ወደ ትግበራ ተገብቷል፣
- ዝቅተኛ ተፈላጊ ችሎታንና የሰው ሃይል አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን መሰረት ያደረገ የሰው ሀይል ስምሪት እንዲኖር ጥረት ተደርጓል፣
- የአመት ፈቃድ ያላቸው ሰራተኞች በእቅድ የተመራ የስራ ፈቃድ እንዲጠቀሙ ለስራ ክፍሎች በደብዳቤ የማሳወቅ ስራ ተሰርቷል፣
- ለተቋሙ ሠራተኞች ባጅ እና ጊዜያዊ መታወቂያ በማዘጋጀት ተሰጥቷል፣
- የዋስትና ደብዳቤ ለሚጠይቁ ሰራተኞች በጠየቁ ቁጥር ተሰጥቷል፣
- የስራ ልምድ ለሚጠይቁ ሰራተኞች በጠየቁ ጊዜ ተሰጥቷል፣

- በእድሜ ለጡረታ በመድረስ 3 ሰራተኞች፣ በሞት 2 ሰራተኞች በራስ ፈቃድ 1 ሰራተኛ በድምሩ 6 ሰራተኞች በ6 ወራት ውስጥ ከተቋሙ ተሰናብተዋል፣
- የመስኖና ልማት ኮሚሽን ከሰላም ሚ/ር አርብቶ አደር ጉዳዮች ጋር ተዋህዶ የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር በመቋቋሙ ወደ መ/ቤታችን የተዛወሩ 29 ሰራተኞች የግል ማህደር ከሰላም ሚኒስቴር ጋር ርክክብ በማድረግ የግልና የስራ ፋይላቸውን በመረከብ በመ/ቤት ተደራጅቶ እንዲቀመጥ ተደርጓል፣
- ከሰላም ሚኒስቴር የመጡ ሰራተኞች በስራ ላይ መሆናቸውን በማረጋገጥ ከታህሳስ ወር ጀምሮ ደመወዝ እንዲከፈላቸው ለፋይናንስ በደብዳቤ የማሳወቅ ስራ ተሰርቷል፣
- ምቹ የስራ ሁኔታን ለመፍጠር የሚያግዙ ሥራዎችን (ካፍቴሪያ ማህበራዊ ግንኙነቶች፣ሽማቾች) ለማከናወን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር ተግባራዊ እንዲሆኑ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፣
- የስነ-ምግባር መርሆች ስራ ላይ እንዲውሉ የማድረግ ጥረት ተደርጓል፣
- የተቀናጀ የመረጃ አያያዝ ስርዓት ተግባራዊ እንዲሆን የተቋሙን ሰራተኞችን መረጃ በሶፍት እና በሃርድ ኮፒ እንዲደራጅ ተደርጓል፣
- የስራ ሰአት መቆጣጠሪያ አቴንዳንስ ከፔሮል ጋር ለማስተሳሰር ጥረት በመድረግ ላይ ይገኛል፤
- የተቋሙ ሰራተኞች ስራ አፈጻጸም በየስድስት ወሩ እንዲመዘኑ ለስራ ኃላፊዎች በደብዳቤ በማሳወቅ ክትትል በመድረግ ላይ ይገኛል፣

## 9. ስነምግባርና ፀረ-ሙስ

- .የህዝብ ተመራጮች፣ ተሿሚዎች እና ሰራተኞች እንደተመረጡ፣ እንደተሾሙ፣ እንደተመደቡና እንደተቀጠሩ የመጀመሪያ የሀብት ምዝገባ እንዲያካሂዱ እንዲሁም በማንኛውም ምክንያት አገልግሎታቸውን ሲያቋርጡ የአገልግሎት ማቋረጥ ምዝገባ አካሂደው እንዲለቁ የአሰራር ስርዓት ተዘርግቷል፣
- .ከፌደራል ስነ ምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን ጋር በየ6 ወሩ የስራ አፈፃፀም ግምገማ ላይ ተሳትፎ ተደርጓል፣
- በመስኖ ልማት ተቋማት የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ስራ በመስራት ክትትልና ማድረግ ተሰርቷል፣
- ጥቆማዎችን ማሰባሰብና በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲዉሉ ማድረግ ተከናውኗል፣
- .ለመስኖልማት አመራርና ሰራተኞች የስነ-ምግባርና ሞራል እሴቶች እና ሙስና መከላከል ላይ ስልጠና ተሰጥቷል፣

- በተቋሙ ዉስጥ የሁሉም ሃብት አስመዝጋቢዎች መረጃ ማደራጀት፣ወቅታዊማድረግና ለኮሚሽኑ መላክ ተሰርቷል፣
- በተቋሙ ዉስጥ አዲስ ለተሾሙ፣የተቀጠሩና የተመደቡ አመራርና ሰራተኞች ስራ ከመጀመራቸው በፊት የስነ ምግባርና ሞራል እሴቶችና ሙስና መከላከል ስልጠና እዲያገኙ ተደርጓል፣
- በተቋሙ ቢያንስ 5/አምስት/ የሙስና መከላከል የአሰራር ስርዓት ጥናት በማካሄድ የማሻሻያ ሀሳቦችን እንዲተገበር 2 ታቅዶ 150% ተከናውኗል፣
- በስነ ምግባራቸዉና ሙስና በመከላከል ረገድ ላቅ ያለ ድርሻ ያስመዘገቡ አካላት እዉቅና እንዲገኙ ተደርጓል፣
- በተቋማችን የዓለም አቀፍ የፀረሙስና ቀን በደመቀ ሁኔታ ተከብሯል፣
- የተቋማችን የውስጥና የውጭ ኦዲት ሪፖርት እንዲደረስ ማድረግ ግኝቶችም የመፍትሔ ሀሳብ እንዲየገኙ ማድረግ ተግባራዊነትን መከታተል ስራ ተሰርቷል፣
- በስነምግባር ግንባታና ሞራል እሴቶች ግንባታና ሙስና መከላከል ላይ የህትመት ውጤት መልዕክቶችን ማዘጋጀት፣ ማሰራጨትና መለጠፍ ስራ ተሰርቷል፣
- የተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎችን በመጠቀም መልዕክቶችን ለተቋሙ ሰራተኞች ተደራሽ ማድረግ ስራ ተሰርቷል፣

## 10. ኤች አይ ቪ መከታተያ

- ፕሮጀክት ሳይት ለሚገኙ ሰራተኞች ባዮ-ሜዲካል የፀረ-ኤች.አይ.ቪ. አገልግሎቶች እንዲያገኙ በአቅራቢያ ካሉ ጤና ተቋማት ጋር ፕሮጀክት ሳይቶች ትስስር እንዲፈጥሩ ማድረግ ለትላልቅ የግንባታ ፕሮጀክቶች (ላይኛዉ አዋሽ፣ማእከለኛዉ አዋሽ(ወረር)፣ ታችኛዉ አዋሽ(ሰመራ/ዱፍቲ፣ አዳማ ማእከል፣ ቆጋ፣ ባህርዳር ማእከል፣ መገጭ፣) የተቀናጀ ክትትልና ድጋፍ ተደርጎል፣
- በ6 ወራት ኤች.አይ.ቪ.ንና ኮረና- covid 19 በተመለከተ የመከላከል መልዕክቶችን የያዙ የመረጃና ስርጸት ትምህርት ማቴሪያሎችን በማሳተምና በማሰባበስብ በፕሮጀክት ሳይቶችና በዋናው መ/ቤት የማሰራጨት ሰራ ተሰርቷል፣
- የክፍሉን የፋይናንስ አቅም ለማጎልበት ፕሮፖዛል የተዘጋጀ ሲሆን በጀት የማፈላለግ ስራ በሀሂደት ላይ ይገኛል፣.
- 5000 ኮንዶም በፕሮጀክት ሳይቶች የማሰራጨት ስራ ተሰርቷል፣

- ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው ለሚገኝባቸው ሰራተኞች የገንዘብና የስነልቦና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ የመረጃ ማሰባሰብ ስራ ተሰርቶ ወደትግበራ ለመግባት ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል፣
- ወላጃቸውን በኤድስ ላጡ ተጋላጭ ህጻናት የገንዘብና የስነልቦና ድጋፍ እንዲያገኙ ለማድረግ የዳሰሳ ጥናት እየተካሄደ ነዉ፣
- ቫይረሱ በደማቸው ለሚገኝባቸው ሰራተኞች የ"ART" በአግባቡ እንዲወስዱ ክትትል የማድረግ ስራ እየተሰራ ነዉ፣

***በስራ አመራርና ድጋፍ ፕሮግራም ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች፡-***

***ያጋጠሙ ችግሮች***

- በአንዳንድ ዳይሬክቶሬቶች የሰዉ ሀይል አለመሟላት በክፍሉ የስራ አፈጻጸም ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩ፣
- የቢሮ መገልገያ ቁሳቁሶችና የተሽከርካሪ ዕቃዎች የግዥ ጥያቄ ለፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት (ግዥ ቡድን) ቢቀርብም ግዥው በወቅቱ መፈጸም አለመቻሉ፣
- ሳኒታይዘርና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች በየወሩ ተገዝተው ለሠራተኛው እንዲሰጡ ቀደም ሲል ቢወሰንም ተግባራዊ አለመደረጉ፣
- ማንኛውም የቢሮ መጠቀሚያ ቁሳቁስ ግዥ በIFMIS ሶፍትዌር አማካይነት ጥያቄ ካልቀረበ ግዥ እንደማይፈጽም በመደረጉ እና በስራ ክፍሎች ያሉ ሁሉም ሰራተኞች በቂ ስልጠና ባለመውሰዳቸውና በሶፍትዌሩ ጥያቄ ባለማቅረባቸው ለቢሮ መገልገያ የሚውሉ አላቂና ቋሚ ዕቃዎች ግዥ በተሟላ መልኩ መፈጸም አለመቻሉ፣
- ለመስክ ስራ ተሽከርካሪ በሚፈለገው ወቅት ማግኘት አለመቻል፣

***የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች***

- የቢሮ ጥገናና ፓርቲሽንና መሰል ስራዎች በሂደት ላይ ይገኛል፣
- የሰዉ ሀይል እስኪሟላ ባለዉ የሰዉ ሀይል ተሸፍኖ እየተሠራ ይገኛል፡፡
- በIFMIS ሥራ ላይ የተፈጠረውን ችግር መቅረፍ እንዲቻል ስልጠና ላልወሰዱ ሠራተኞች ስልጠና እንዲሰጥ እየተጠየቀ ይገኛል፡፡

**ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች**

- የሰው ኃይል ዕጥረት በሚታይባቸው የሥራ ክፍሎች ብቁ የሆኑ ሠራተኞችን በመቅጠር ማሟላት፣
- አዳዲስ ተጨማሪ ተሽከርካሪዎች የሚገኙበትን መንገድ ማፈላለግና ጋራዥ በብልሽት የቆሙትን ተሽከርካሪዎች በአፋጣኝ በማስጠገን ወደ ስራ እንዲገቡ ማድረግ፣

# ክፍል አንድ፡ የመስኖ ልማት ዘርፍ የ6 ወራት አፈጻጸም

## ፕሮግራም ሁለት፡ መስኖ ልማት ፕሮግራም

### ሀ. ንዑስ ፕሮግራም አንድ፡ የመስኖ ጥናት፣ዲዛይንና ግንባታ ንዑስ ፕሮግራም

### ሀ1. የመስኖ መሠረተ ልማት ግንባታ

### 1. የመገጭ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት

***መግቢያ***

*የመገጭ ግድብ ፕሮጀክት የሚገኘው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ጎንደር ዞን በጎንደር ዙሪያ ወረዳ ሲሆን የዚህ ግድብ ዓይነት* Rock fill Dam *ሆኖ የሚገነባው በተመረጠ አፈር፣ በድንጋይና በሼል (ዋልካ አፈር) ነው፡፡ ግድቡ* 185 *ሚሊዮን ሜ. ኪዩብ ውሃ የመያዝ አቅም ያለው ሲሆን በሰከንድ* 662 *ሜ.ኩብ ትርፍ ውሃ ማስተንፈስ የሚችል ርዝመቱ* 54 *ሜትር የሆነ የትርፍ*

ውሃ ማስወገጃ አካል (spill way)፣ በሰከንድ 20 ሜ.ኩብ ውሃ መቀበልና መቆጣጠር የሚችል ቁመቱ 64.7 ሜትር የሆነ የውሃ መቀበያና መቆጣጠሪያ ማማ /Intake tower/፣ የወገቡ ስፋት 2.5 ሜትር የሆነ በሰከንድ 40 ሜ.ኩብ ዉሃ ወደ መስኖ መሬት ሊያደርስ የሚችል የመስኖ ቦይ ወይም ቱቦ እና የወገቡ ስፋት 1 ሜትር የሆነ የመጠጥ ውሃ ማስተላለፊያ ቱቦ (የሁለቱም ቱቦዎች ርዝመት 220 ሜትር ነው) የሚኖረመው ነው፡፡

የፕሮጀክቱ ግንባታ እየተከናወነ ያለው መንግስታዊ የልማት ድርጅት በሆነው በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽ የውሃ መሰረተ ልማት ሥራዎች ዘርፍ ሲሆን የጥራት ቁጥጥር እና የማማከር ሥራው ደግሞ መንግስታዊ የልማት ድርጅት በሆነው በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ዲዛይንና ሱፐርቪዥን ኮርፖሬሽን የውሃና ኢነርጂ ዲዛይንና ቁጥጥር ስራዎች ዘርፍ አማካይነት ነው፡፡

**የፕሮጀክቱ ዓላማ**

የግንባታው ዓላማም በመገጭ ወንዝ አዋሳኝ በሆኑና በአካባቢው የሚገኙ አርሶ አደሮችን የምግብ ዋስትና ማረጋገጥና ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት የበኩሉን አስተዋጽኦ ከማበርከት አኳያ ከ14000 እስከ 17,000 ሄክታር የመስኖ እርሻ የማልማት ስራ እና በተጨማሪም በጎንደር ከተማ እና በጎንደር ዙሪያ በሚገኙ ትናንሽ ከተሞች ለሚኖረው ህብረተሰብ የንፁህ መጠጥ ውሃ አገልግሎት ማቅረብ ነው፡፡ ይህ ፕሮጀክት በመስኖው ዘርፍ የታቀዱትን የሁለተኛው አምስት አመት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ግቦች ለማሳካት ከተያዙት ፕሮጀክቶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡

**የፕሮጀክቱ የ2014 በጀት አመት ግብ**

በበጀት ዓመቱ 19.53% በማከናወን የግድቡን አጠቃላይ ግንባታ በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 70.97% ወደ 90.50% ማድረስ፡፡

**የፕሮጀክቱ የግማሽ ዓመት አፈጻጸም**

እስከ ሁለተኛው ሩብ ዓመት የግድቡን ግንባታ 8.64 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 0.56 በመቶ ወይም የዕቅዱን 6.48 በመቶ በማከናወን አጠቃላይ ግንባታው በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 70.97% ወደ 71.53% ማድረስ ተችሏል፡፡

ግቦቹን ለማሳካት እስከ ሁለተኛው ሩብ ዓመት የታቀዱና የተከናወኑ ዝርዝር ተግባራት

- በዋና ግድብ (Main Dam) ላይ 3.75 ለማከናወን ታቅዶ 0.30% በማከናወን የዕቅዱን 8.18 በመቶ የተከናወነ ሲሆን አጠቃላይ ዋናው ግድብ ሥራ 70.66% ደርሷል፡፡
- የውሀ ማስተንፈሻ (Spillway) ላይ 1.703 ለማከናውን ታቅዶ 0.031% በማከናወን የዕቅዱን 1.82 በመቶ የተከናወነ ሲሆን አጠቃላይ የውሀ ማስተንፈሻ(Spillway) ሥራ 87.03% ደርሷል፡፡

- የውሀ ማስተላለፊያ (conduit) 1.013 ለማከናወን ታቅዶ 0.040% በማከናወን የዕቅዱን 3.95% የተከናወነ ሲሆን አጠቃላይ የውሀ ማስተላለፊያ (conduit) ሥራ 70.70% ደርሷል፡፡
- የውሀ ማስወጫ ማማ(Intake Tower) 2.15 ለማከናወን ታቅዶ 0.195% በማከናወን የዕቅዱን 9.04 በመቶ የተከናወነ ሲሆን የውሀ ማስወጫ ማማ(Intake Tower) ሥራ 52.38% ደርሷል
- በዋና ግድብ (Main Dam) ላይ በ2012 ዓ.ም ክረምት ላይ በመሰንጠቅ (crack) የተንሸራተተ የክሌይ፣የሼል፣የአሸዋ እና የድንጋይ ሙሌትን የማንሳት ሥራ **(ከዕቅድ ውጪ ተከናውኗል)**

**በ6 ወራት የተፈጠረ የሥራ ዕድል**

| የፕሮጀክቱ ስም | የሥራ ዕድል ተጠቃሚ የሆኑ ዜጎች | | | | | | | | | የተቀጠረ ተቋራጭ ድርጅት ብዛት | የተቀጠረ አማካሪ ድርጅት ብዛት | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከ18-35 ዓመት | | | ከ35 ዓመት በላይ | | | ድምር | | | | | |
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | | | |
| መገጭ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት | 589 | 116 | 705 | 171 | 9 | 180 | 760 | 125 | 885 | 7 (1 ዋና ተቋራጭ እና 6 ንዑስ ተቋራጮች) | 1 | 8 |

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** እስከ ሁለተኛው ሩብ ዓመት ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ ብር 450.53 ሚሊዮን ብር ታቅዶ 265.66 ሚሊዮን ብር ወይም የዕቅዱን 58.97 በመቶ ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ ውሏል፡፡

**ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች**

**ያጋጠሙ ችግሮች፡-**

- በዋናው ግድብ ላይ እየተከናወነ ያለው የማስተካከያ ሥራ በጣም ሰፊ በመሆኑ በዋናው ግድብ ላይ በዕቅድ ተይዞ የነበረው ሥራ ሙሉ ለሙሉ እንዲቋረጥ መደረጉ፣
- በግደቡ የላይኛው ክፍል ያለውን የአሸዋ ምርት ለማምረት በአካባቢው ማህበረሰብ የካሳ ክፍያ ጥያቄ ምክንያት ማምረት አለመቻሉ፣

- በሁሉም የአርማታ ሥራ በሚፈልጉ የስራ ክፍሎች ላይ የዋናው ተቋራጭም ሆነ የንዑስ ተቋራጭ አቅም ውስንነት፣ ተደጋጋሚ የአርማታ ማቀነባበሪያ ብልሽትና የአድሚክሰር ዕጥረት በተፈለገው መጠን ሙሌት ማከናወን አለመቻል ናቸው፡፡

**የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች**

- በዋና ግድብ ላይ የተከሰተውን የመሰንጠቅና የመንሸራተት ችግር ለመለየት ከአማካሪው እንዲሁም ከዋናው ተቋራጭ ባለሙያዎች በሥፍራው በመገኘት ጉዳዩን የተመለከቱት ሲሆን የአማካሪው መሀንዲስ ከፍተኛ ባለሙያዎች የችግሩን ጥልቀት እንዲሁም የማስተካከያ ሥራው እሰከምን ይደርሳል በሚለው ሰፊ ጥናት ያደረጉ ሲሆን ዝርዝር ጥናቱ ተጠናቆ እስኪቀርብ ግን የተሸንራተተው ክፍል እንዴት ይውጣ ቀጣይ ሥራ እንዴት ይቀጥል በሚለው ላይ በሳይት ደረጃ ስምምነት ተደርሷል፡፡ በዚህም መሠረት በዋናው ግድብ ላይ በዚህ በጀት ዓመት ሊኖር የሚችለው ዋና ሥራ ይህንኑ የተበላሸ ሥራ የማስተከከል እና ክረምቱ ከመድረሱ በፊት አስተማማኝ ሁኔታ ላይ ማድረስ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ ሆኖም የማስተካከያ ሥራው ሊወስድ የሚችለውን ጊዜ እንዲያጥር በማድረግ በቀሪ ጊዚያት ተቋራጭ ድርጅቱ የማካካሻ ዕቅድ እንዲያቀርብ በማድረግ በእቅድ ውስጥ የነበረ የሙሌት ስራ እንዲያከናውን የሚደረግ ይሆናል፡፡ በዚህ የማስተካከያ ሥራ ላይ ከፍተኛ የባለሙያ ውይይቶች የተደረጉ ሲሆን ማስተካከያው እንዴት ይሰራ በሚለው ላይ በርካታ አማራጮች ቀርበው ሰፊ ክርክር ከተደረገ በኃላ በጊዜም፣በወጪ እንዲሁም በጥራትም የተሸለ ነው በተባለው ላይ መሰማማት ተደርሶ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡
- ባለው ወቅታዊ ሁኔታ በክልሉ ተዘግተው ከነበሩ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ወደ ሥራ ከተመለሱት ውስጥ የግብርናና የገጠር ልማት መምሪያ አንዱ ሲሆን ይህም ቀደም ሲል ከካሳ ጉዳይ ጋር እና ሌሎች ተዛማች የማህበራዊ ችግሮች ጋር የነበረውን ክፍተት ለማስተካከል እንደሚረዳ ይጠበቃል በዚህም መሠረት የጎንደር ከተማ አስተዳደር ግብርና ገጠር ልማት መምሪያ ቀደም ሲል ልኬት ተካሂዶባቸው ነገር ግን የካሳ ግምት ስሌት ሳይካሄድባቸው የነበሩ ይዞታዎችን የካሳ ግምት በመሥራት በፍጥነት ወደ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እንደሚልክ ቃል ገብቶልናል በዚህም መሠረት በሼልና በአፈር ምርት ላይ የነበረውን የማምረቻ ይዞታ እጥረት ይስተካከላል ተብሎ ይጠበቃል፡፡
- ለአርማታ ሙሌት ተጨማሪ ግብዓት የሆነው አድሚክሰር በገበያ ላይ ለማግኘት አስቸጋሪ እየሆነ እንደሆነ በተቋራጩ እየተገለጸ ቢሆንም ይህንን ግብዓት በማይፈልጉ የአርማታ ስራ ክፈሎች ላይ ሥራውን በሥፋት እንዲያከናወን ከተቋራጩ ጋር መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡ በመጨረሻም ይህ ሪፖረት በተጠናቀረበት ወቅት የአድሚክሰር ምርት ወደ ፕሮጀክቱ ገብቷል፡፡

**ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች**

- ሁለተኛው ሩብ ዓመት እንደ መጀመሪያው ሩብ ዓመት በጣም ደካማ እንቅስቃሴ የታየበት በመሆኑ በተመሳሳይ በግድቡ ላይ ተፈጠረው የመንሸራተት ችግር በዚህ ቦታ ላይ ያቀድነውን ለማሳካት አንቅፋት በመሆኑ እሱን የማስተካከል ሥራው እንደተጠበቀ ሆኖ በኢንቴክ ታውር እንዲሁም በስፒልዌይ ላይ ከፍተኛ ስራ መሥራት ይጠበቅብናል፡፡ ለዚህም ተቋራጩ በተለይ በአርማታ ማቀነባበሪያ ተደጋጋሚ ብልሽትና የአቅም ውስንነት ላይ ጠንክሮ እንዲሰራ ከፍተኛ ግፊት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
- የአሸዋ ምርትን በስፋት ለማምረት ከክልሉ ከፍተኛ ባለስልጣናት ጋር ግንኙነት በመፍጠር በተለየ መልኩ ለእንደዚህ ዓይነት ሥራዎች መፍተሄ የሚሰጥበት መንገድ ሊፈለግ ይገባል፡፡

## 2. የጊዳቦ ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት /ተጨማሪ ግንባታዎች/

የጊዳቦ ግድብና መስኖ ልማት ኘሮጀክት ከአዲስ አበባ 390 ኪ.ሜ ላይ በኦሮሚያና በደቡብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥታት የሚገኝ ነው፡፡

**የፕሮጀክቱ ዓላማ**

63,000 ሚሊዮን ሜ.ኩ ውሀ የሚይዝ የዋና ግድብ፣ የውሃ መቆጣጠሪያ ማማ፣ የትርፍ ውሃ ማስወገጃ ስትራክቸር እና የውሃ ማስወጫ በመገንባት 13,400 ሄ/ር መሬት ለማልማት ታሳቢ ያደረገ ሲሆን የፕሮጀክቱ ግንባታ ቀደም ሲል ተጠናቋል፡፡ በዚህ በጀት ዓመትም ተጀምረው በመካሄድ ላይ የነበሩት የተጨማሪ ካናል እና የማህበራዊ ተቋማት ግንባታ ሥራዎችን ለማጠናቀቅ በዕቅድ ተይዞ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

**የፕሮጀክቱ የ2014 በጀት ዓመት ግቦች**

- በሎት-2 እየተገነባ ያለውን የግራ እና የቀኝ የመስኖ ውሃ ማቅረቢያ ዋና ቦይ እና የማህበራዊ ተቋማት ግንባታን በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ ከነበረበት 57.60 በመቶ ወደ 100 ማድረስ እና
- የመስኖ መሬት ዝግጅት ሥራ በበጀት አመቱ በመጀመር የሥራውን 25% ማጠናቀቅ ናቸው፡፡

**የፕሮጀክቱ የግማሽ ዓመት አፈጻጸም**

- በሁለተኛው ሩብ ዓመት በሎት-2 እየተገነባ ያለውን የግራ እና የቀኝ የመስኖ ውሃ ማቅረቢያ ዋና ቦይ ግንባታ 24.79 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 14.52 በመቶ ወይም የዕቅዱን 58.57 በመቶ በማከናወን አጠቃላይ ግንባታው በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 57.60% ወደ 72.12% ማድረስ ተችሏል፡፡

**ግቦቹን ለማሳካት የተከናወኑ ዋና ዋና ዝርዝር ተግባራት፡-**

- የአፈር እና ድንጋይ ቁፋሮ ሥራ 60,324 ሜ. ኩብ፣
- የአፈር፣ ድንጋይ እና አሸዋ ሙሌት ሥራ 36,985 ሜ. ኩብ፣
- የኮንክሪት ሙሌት ሥራ 2058 ሜ. ኩብ፡፡

**በ6 ወራት የተፈጠረ የሥራ ዕድል**

| የፕሮጀክቱ ስም | የሥራ ዕድል ተጠ.ቃሚ የሆኑ ዜጎች | | | | | | | | | የተቀጠረ ተቋራጭ ድርጅት ብዛት | የተቀጠረ አማካሪ ድርጅት ብዛት | ድም |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከ18-35 ዓመት | | | ከ35 ዓመት በላይ | | | ድምር | | | | | |
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | | | |
| ጊዳቦ መስኖ ልማት ፕሮጀክት | 545 | 77 | 622 | 114 | 1 | 115 | 659 | 78 | 737 | 1 | 1 | 2 |

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** በ6 ወራት ውስጥ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ ብር 140.24 ሚሊዮን ብር ታቅዶ 95.07 ሚሊዮን ብር ወይም የዕቅዱን 67.8 በመቶ ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ ውሏል፡፡

**ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች**

**ያጋጠመ ችግር፡-**

- ተቋራጭ ድርጅቱ OPC ሲሚንቶ ከፋብሪካ የለም በሚል ምክንያት የካናል ኮንክሪት ስራ ያቆመ መሆኑ እና የግንባታ ማሽነሪዎችን በሚፈለገው መጠን ማቅረብ አለመቻሉ (ለረዥም ጊዜ ያገለገሉ ማሽነሪዎችን በማቅረቡ ማሽነሪዎቹ በተደጋጋሚ የሚበላሹና በቂ ምርት የማይሰጡ መሆናቸው)፣
- ተቋራጭ ድርጅቱ ለፕሮጀክቱ ትኩረት ሰጥቶ መስራት አለመቻሉ፡፡

**የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች**

- ተቋራጭ ድርጅቱ የማሽነሪ እና የሲሚንቶ አቅርቦት ችግሮችን እንዲፈታ በሳይት ደረጃ በደብዳቤ ተገልፆለታል፤
- ሳይት ላይ በተደረጉ የሦስትዮሽ ስብሰባዎች ተቋራጭ ድርጅቱ የግብአት አቅርቦት ችግሮችን በመፍታት የካናል ኮንክሪት ስራ በአፋጣኝ እንዲጀምር ተገልፆለታል፡፡

**ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፡-**

- የተጨማሪ ካናል ግንባታ ስራን እስከ ሚያዝያ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ለማጠናቀቅ ታቅዶ እየተሰራ ያለ ቢሆንም የተቋራጭ ድርጅቱ አፈፃጸም ዝቅተኛ በመሆኑ ፕሮጀክቱ በ2014 የበጀት አመት እንዲጠናቅቅ ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

- ተቋራጭ ድርጅቱ በፕሮጀክቱ ባለቤት የክፍያዎች መዘግየት አስፈላጊ ግብዓቶችን ለማቅረብ እንደሚቸገር በሳይት ደረጃ በተደረጉ የሣስትዮሽ ስብሰባዎች እየገለጸ በመሆኑ የፕሮጀክቱ ባለቤት ክፍያዎችን ቶሎ መፈጸምና ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## 3. አርጆ ዴዴሳ ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት

**መግቢያ**

አገራችን ኢትዮጵያ ካሏት የተፈጥሮ ሀብቶች ውስጥ አንዱ የገፀ-ምድር የውሃ ሀብት ሲሆን ይህንን የውሃ ሀብት በአግባቡ በመጠቀም የምግብ ዋስትናን በአስተማማኝ ሁኔታ ማረጋገጥ ይቻል ዘንድ ወንዞችን ገድቦ መያዝና የመስኖ ልማትን ማስፋፋት ወሳኝ ተግባር ነው፡፡ ይህንንም ለማሳካት በተለያዩ የአገሪቷ ተፋሰሶች የግድብ ግንባታ ፕሮጀክቶች የተጀመሩ ሲሆን ከነዚህ የግድብ ግንባታ ፕሮጀክቶች ውስጥ አንዱ የአርጆ-ዴዴደሳ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ነው፡፡

**የፕሮጀክቱ ዓላማ**

የአርጆ-ዴዴሳ ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክትን በመተግበር ረገድ ያለው ቀዳሚ ዓላማ አሁን በአገሪቱ ያለውን የስኳር ፍላጎት አሟልቶ የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት፣ የሥራ እድል መፍጠርና ድህነትን መቀነስ ናቸው፡፡

**የበጀት ዓመቱ ዋና ዋና ግቦች**

- የግድብና ተጓዳኝ ስራዎች ግንባታን በ2014 በጀት ዓመት 16.16% በማከናወን ግንባታውን በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 83.28% ወደ 99.44% ማድረስ፣
- የመሠረተ ልማት ግንባታ ሥራ በ2014 በጀት ዓመት 3.59% በማከናወን ግንባታውን በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 96.41% ወደ 100.00% ማድረስ፣
- የመስኖ መሬት ዝግጅት ግንባታ ሥራ በመጀመር በ2014 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ 15% ማድረስ፡፡

**የፕሮጀክቱ የግማሽ ዓመት አፈጻጸም**

- እስከ ሁለተኛው ሩብ ዓመት መጨረሻ ድረስ የግድብና ተጓዳኝ ስራዎች ግንባታን 7.34% ለማከናወን ታቅዶ 1.41% የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙ 19.21% ነው፡፡ በዚህም አጠቃላይ የግድብ ግንባታውን በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 83.28% ወደ 84.69% ማድረስ ተችሏል፡፡

**ግቦቹን ለማሳካት የታቀዱና የተከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፡-**

- የቀኝ ኮርቻ ግድብ (Right Saddle Dam) ስራ በክብደት 16.73% ለማከናወን ታቅዶ 5.3% በክብደት ወይም የዕቅዱ 31.68% የተከናወነ ሲሆን በአጠቃላይ 24% ደርሷል፡፡

- የኮርቻ ግድብ የመሰረት ማጠናከር ሥራ (Grouting Works) በክብደት 19.62% ለማከናወን ታቅዶ 12.12% ወይም የዕቅዱ 61.77% የተከናወነ ሲሆን በአጠቃላይ 64.5% ደርሷል፡፡

**በ6 ወራት የተፈጠረ የሥራ ዕድል**

| የፕሮጀክቱ ስም | የሥራ ዕድል ተጠ.ቃሚ የሆኑ ዜጎች | | | | | | | | | የተቀጠረ ተቋራጭ ድርጅት ብዛት | የተቀጠረ አማካሪ ድርጅት ብዛት | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከ18-35 ዓመት | | | ከ35 ዓመት በላይ | | | ድምር | | | | | |
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | | | |
| አርጆ-ዴዴሳ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት | 180 | 97 | 277 | 80 | 3 | 83 | 260 | 100 | 360 | 2 | 1 | 3 |

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** በ6 ወራት ውስጥ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ ብር 375.01 ሚሊዮን ብር ታቅዶ 198.18 ሚሊዮን ብር ወይም የዕቅዱን 52.8 በመቶ ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ ውሏል፡፡

***ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች***

***ያጋጠሙ ችግሮች***

- በአካባቢው በተከሰተ የፀጥታ ችግር ምክንያት የግድብ ግንባታውን የሚያከናውነው ተቋራጭ ድርጅት 5 የቁፋሮ ማሽኖቹ በመቃጠላቸው ምክንያት በተወሰነ ደረጃ የስራ መቀዛቀዝ መኖሩ እና
- የትርፍ ውሃ ማስወጪያ ውቅር የሚገነባው ተቋራጭ ድርጅት ውለታ በመቋረጡ በዕቅድ የተያዙ ስራዎችን ማከናወን አለመቻሉ፡፡

**የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች**

- ተቋራጩ ከአካባቢው አስተዳደር ጋር ባደረገው ውይይት የፀጥታ ማስከበር ሥራ በመከናወኑ በሙሉ አቅሙ እንዲንቀሳቀስ ጥረት ተደርጓል እንዲሁም
- የትርፍ ውሃ ማስወጪያ ውቅር /spilway/ የሚገነባው ተቋራጭ ውለታ እንዲቋረጥ በማድረግ ሥራው የግድብ ግንባታ እያከናወነ ላለው ተቋራጭ ተሰጥቶ ሥራውን የማስቀጠል ሥራ ተጀምሯል፡፡

**ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች**

- የግድቡ ዉሃ የሚተኛበት (Reservoir Area) ዉስጥ ላሉ የልማት ተነሺ የሚሆኑትን የህብረተሰብ ክፍሎች ከወዲሁ ማንሳትና ሌላ ቦታ ማስፈር ባለመጀመሩ ወደፊት በግንባታ ሂደት ላይ መጓተት ሊያስከትል ይችላል፣

- ለትርፍ ውሃ ማስወጪያ ውቅር ግንባታ ሥራ ሊውል የሚችል የሲሚንቶ አቅርብቶ ችግር ሊያጋጥም ስለሚችል ከወዲሁ አቅርቦቱ የሚስተካከልበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት ያስፈልጋል፣
- በተቋራጭ ድርጅቱ በኩል የግብአት (የማሽነሪ፣ የነዳጅ እና የኮንስትራክሽን እቃዎች) አቅርቦት ችግሮች መፈታት እንዲችሉ ጥብቅ ክትትል ማድረግ፣
- ለተቋራጭ ድርጅቱ የሚከፈሉ ክፍያዎች በcash flow ችግር ምክንያት እንዳይዘገዩ ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## 4. የኢትዮጵያ ናይል መስኖና ድሬይኔጅ ፕሮጀክት

**መግቢያ**

ርብ መስኖና ድሬኔጅ ፕሮጀክት የሚገኘው በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በደቡብ ጎንደር ዞን፣ ከጣና ሀይቅ በሰተምስራቅ በኩል በ 2 ወረዳዎች ማለትም በሊቦ ከምከምና በፎገራ ወረዳዎች ነው፡፡ ፕሮጀክቱ የሚያካትታቸው ሁለት ወረዳዎች ሲሆኑ.፣ እነሱም ፎገራ ወረዳ እና ሊቦከምከም ወረዳ እንደነበር ይታወቃል፣ ነገር ግን ከጥቅምት ወር 2010 ዓ.ም. ጀምሮ የአለም ባንክ የብድር ግዜ ስለተጠናቀቀ መንግስት በራስ አቅም ፕሮጀክቱን ለማጠናቀቅ እየሰራ ይገኛል፡፡ናቸው፡፡ አሁን ባለው ሂደት በርብ 3400 ሄ/ር መሬት ለማልማት የመስኖ አውታርና ተያያዥ የግንባታ ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡

**የፕሮጀክቱ ዓላማ**

ፕሮጀክቶቹ በሚካሄዱባቸው አካባቢ ማለትም በርብ መስኖ አውታር ግንባታ በሚካሄድበት አካባቢ ለሚኖረው ህብረተሰብ የምግብ ዋስትናቸውን በማረጋገጥ የኑሮ ደረጃቸውን ማሻሻል ነው፡፡

**የፕሮጀክቱ የ2014 በጀት ዓመት ግብ**

- የርብ መስኖና ድሬኔጅ ግንባታን በበጀት ዓመቱ 20.29 በመቶ በማከናወን አጠቃላይ ግንባታው በ2013 በጀት አመት መጨረሻ ከነበረበት 79.71 በመቶ ፕሮጀክቱን 100% ማጠናቀቅ፡፡

**የፕሮጀክቱ የግማሽ ዓመት አፈጻጸም**

እስከ ሁለተኛው ሩብ ዓመት መጨረሻ ድረስ 6.10 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 1.24 በመቶ ወይም የዕቅዱን 20.33% ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህም አጠቃላይ የግድቡን የግንባታ አፈጻጸም በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 79.71% ወደ 80.95% ማድረስ ተችሏል፡፡

**ግቦቹን ለማሳካት የታቀዱና የተከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፡-**

- የመስኖ ውሃ ቦይ (ከዋና ቦይ እስከ ሶስተኛ ቦይ)፣ ለድሬኔጅ፣ ለጎርፍ መከላከያ ዳይክ ለመስራት እንዲሁም ለመንገድ ስራ የሚሆን ማቴሪያል ማምረቻ ቦታ በመምረጥ የላቦራቶሪ ፍተሻ ተደርጎ በማጠናቀቅ ማምረት መጀመር፡፡
- ከፕራይመሪ ካናል የተከማቸ ደለል ማውጣት እና ቁፋሮ መጀመር
- የቀኝ እና የግራ ዋና ቦይ ቁፋሮ እና ኢምባንክመንት ግንባታ ማካሄድ
- የቀኝ እና የግራ ዋና ቦይ ሁለተኛ እና ሶስተኛ ቦይ ኢምባንክመንት ሙሌት ማካሄድ
- የወንዝ መግራት ስራ ማካሄድ ናቸው፡፡

**በ6 ወራት የተፈጠረ የሥራ ዕድል**

| የፕሮጀክቱ ስም | የሥራ ዕድል ተጠቃሚ የሆኑ ዜጎች | | | | | | | | | የተቀጠረ ተቋራጭ ድርጅት ብዛት | የተቀጠረ አማካሪ ድርጅት ብዛት | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከ18-35 ዓመት | | | ከ35 ዓመት በላይ | | | ድምር | | | | | |
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | | | |
| የርብ መስኖና ድሬኔጅ ግንባታ ፕሮጀክት | 100 | 20 | 120 | 24 | 2 | 26 | 124 | 22 | 146 | 1 | 1 | 2 |

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** በ6 ወራት ውስጥ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ ብር 183.39 ሚሊዮን ብር ታቅዶ 30.56 ሚሊዮን ብር ወይም የዕቅዱን 16.7 በመቶ ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ ውሏል፡፡

**ያጋጠመ ችግር፡-**

- ከመጀመሪያዉ ኮንትራት ጋር በተያያዘ ስራዎች አልቀዉ ነገር ግን በመቆየት የተበላሹ ስራዎች በአዲሱ ዉል አለመካተታቸዉ (Work Varation) እና በመጀመሪያው ኮንትራክተር ተሰርተው ድጋሜ ስራ የሚያስፈልጋቸው በአናት ስራ (Diversion Weir)፣ የመስኖ ቦዩች እና ተዛማች እስትራክቸሮች ላይ ሊገጥም የሚችል ብልሽት ይህም በፕሮጅክቱ አፈጻጸም ላይ ተጸዕኖ ማሳደር፡፡
- በአካባቢው አልፎ አልፎ የሚከሰቱ የህብረተሰብ ችግሮች መኖራቸው (Social Problem & Right OffWay)፡፡
- ለመስኖ ቦይ ግንባታ እና የወንዝ መግራት ስራ ከፍተኛ የተመረጠ አፈር የሚያስፈልግ በመሆኑ የካሳ ክፍያ የተከፈለበት ቦታ ህብረተሰቡ ባለመልቀቁ ምክንያት ለስራ ምቹ አለመሆን
- ለመስኖ ቦይ ግንባታ የሚፈለጉ ቦታዎች ላይ አርሶአሩ ቤት መገንባት እና ክፍያ የተፈጸመባቸው የግንባታ ቦታዎች አርሶ አደሩ ዛፍ ለመቁረጥ ፍቃደኛ ያለመሆን

- አካባቢው በተለምዶ የባህላዊ የመስኖ ልማት ተጠቃሚ በመሆኑ ለግንባታው መሬቱን ምቹ አለመሆን እና በሰብል መሸፈን

**የተወሰደ የመፍትሄ እርምጃ፡-**

- በአሰሪ መ/ቤቱ ትዕዛዝ መስረት የቆጠራ ስራ በመስራት ያልተካተቱ ስራዎች እንዲካተቱ፤ የተበላሹ ስራወች የብልሽት መጠናቸውን በመለካት ማካተት፤ በኮንትራቱ ተይዘው በመብዛትም ሆነ በማነስ ያላቸውን መጠን በመለካት ለአሰሪ መ/ቤቱ ቀርቦ አስያየት ተሰጥቶበታል፣
- በኮንትራክተሩ እና በአካባቢው የአስተዳደር አካል ካሳ የተከፈለበትን ቦታ በማጣራት ለስራ ምቹ ለማድርግ እየተሞከረ ነው፣
- ለአፈር ሙሊት የሚያስፈልግ ቦታ እና መጠንን በአማካሪና በኮንትራክትር በኩል ተሰርቶ ለአሰሪ መ/ቤቱ በቀረበው መሰረት መ/ቤቱም ለሚመለከተው ወረዳ ደብዳቤ በመጻፍ ቦታው እንዲፈቀድ ጥያቄ አቅርቧል፣
- ባለቤቱ (መስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚ/ር) ሁለት ባለሙያዎችን በመመደብ ሳይት ላይ ከአማካሪ እና ከተ~ራጭ ድርጅቱ ጋራ ተረዳድተው እነዲሰሩ እና ችግሮችን በቅርበት ለመፍታት እየሞከሩ ይገኛሉ፣
- ባለቤቱ (መስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚ/ር) 3 አባላት ያለው ኮሚቴ በማቋቋም ከካሳ ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመፍታት ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

**ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፡-**

- የመሬት አቅርቦት ችግርን በመቅረፍ ለግንባታ ስራ ማቅረብ፣
- ተቋራጮች የማሽነሪና የሰው ኃይል አቅርቦትን ስራው በሚጠይቀው ልክ እንዲያቀርብ ማድረግ፣
- አርሶ አደሩ ስለመስኖ ልማት ጥቅም ያለውን ግንዛቤ የማሳደግ ስራ በተከታታይ መስራት፣
- ለፕሮጀክቱ ግንባታ የሚውሉ ማቴሪያሎች የሚገኙበት ቦታ የካሳ ክፍያ በአሰቸኳይ ማጠናቀቅ፣
- በመጀመሪያው ኮንትራት ተጠናቀው የተበላሹ፣ በአሁኑ ኮንትራት ያልተካተቱ ስራዎችን እና ተጨማሪ የስራ መጠን ልዩነቶችን መርምሮ በአሰቸኳይ ውሳኔ መስጠት፣

## 5. የወልመል የመስኖ ልማት ፕሮጀክት

**መግቢያ**

የመስኖ ልማት ኮሚሽን በ2012 የበጀት አመት ግንባታቸውን ካስጀመራቸው ፕሮክቶች አንዱ የወልመል የመስኖ ልማት ፕሮጀክት ሲሆን ፕሮጀክቱም በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስ በባሌ ዞን ደሎመና ወረዳ ውስጥ የሚተገበር ነው፡፡ ፕሮጀክቱ ተግባራዊ ሲደረግ 3 ሜትር ከፍታ እና 50 ሜትር ርዝመት ያለው የወንዝ መቀልበሻ እና 30 ኪ.ሜ. ርዝመት ያለው መጋቢ የወሃ ቦይ ግንባታ የሚካሄድ ሲሆን 11,040 ሄክታር ማልማት የሚችል የመስኖ አውታር ግንባታም የሚከናወን ይሆናል፡፡ በፕሮጀክቱ ግንባታ ሁለት አገር በቀል ተቋራጭ ድጅቶች የሚሳተፉ ሲሆን አንደኛው ተቋራጭ ድርጅት የወንዝ መቀልበሻ እና መጋቢ የወሃ ቦይ ግንባታ ሥራውን ሲያከናውን ሁለተኛው ተቋራጭ ድርጅት ደግሞ የመስኖ አውታር ግንባ ሥራውን የሚያከናውን ይሆናል፡፡

**የፕሮጀክቱ ዓላማ፡-**

የወልመል መስኖ ልማት ፕሮጀክትን በመተግበር ረገድ ያለው ቀዳሚ ዓላማ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ የሥራ እድል መፍጠርና ድህነትን መቀነስ ናቸው፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግቦች፡-** -

- የወንዝ መቀልበሻና ዋና ቦይ ስራዎች (ሎት-1) ግንባታን በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከደረሰበት የ40.18% አፈጻጸም ላይ 40.70% በማከናወን ወደ 80.88% ማድረስ፡፡
- የመስኖ መሬት ዝግጅት ሥራን (ሎት-2) በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከደረሰበት የ21.19% አፈጻጸም ላይ 42.95% በማከናወን ወደ 64.14% ማድረስ፡፡

**የፕሮጀክቱ የግማሽ ዓመት አፈጻጸም**

- አስከ ሁለተኛው ሩብ አመት መጨረሻ ድረስ የወልመል መስኖ ልማት ፕሮጀክትን (ሎት-1) 20.63 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 13.01 በመቶ ወይም የዕቅዱን 63.06% ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህም አጠቃላይ የፕሮጀክቱን የግንባታ አፈጻጸም በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 40.18% ወደ 53.19% ማድረስ ተችሏል፡፡
- አስከ ሁለተኛው ሩብ አመት መጨረሻ ድረስ የወልመል መስኖ ልማት ፕሮጀክትን (ሎት-2) 24.92 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 11.47 በመቶ ወይም የዕቅዱን 46.03 በመቶ ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህም አጠቃላይ የፕሮጀክቱን የግንባታ አፈጻጸም በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 21.19% ወደ 32.66% ማድረስ ተችሏል፡፡

**ግቦቹን ለማሳካት የተከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፡-**

**ሎት-1፡-**

- የአፈር ቁፋሮ እና ማስወገድ ሥራ 419 ሜ.ኩብ ተከናውኗል፣
- የድንጋይ ቁፋሮ እና ማስወገድ ሥራ 255 ሜ.ኩብ ተከናውኗል፣

- የኮንክሪት ሙሌት ሥራ 7,815 ሜ.ኩብ ተከናውኗል፣
- የዋና መስኖ ቦይ የአፈር ሙሌት ሥራ የግንብ ሥራ 25,164 ሜ.ኩብ ተከናውኗል፣
- የዋና መስኖ ቦይ የግንብ ሥራ 23,546 ሜ.ኩብ ተከናውኗል፡፡

**ሎት-2፡-**

- የአፈር ቁፋሮ እና ማስወገድ ሥራ 101,063 ሜ.ኩብ ተከናውኗል፣
- የድጋይ ቁፋሮ እና ማስወገድ ሥራ 2,976 ሜ.ኩብ ተከናውኗል፣
- የኮንክሪት ሙሌት ሥራ 1,319 ሜ.ኩብ ተከናውኗል፣
- የዋና መስኖ ቦይ የአፈር ሙሌት ሥራ የግንብ ሥራ 17,091 ሜ.ኩብ ተከናውኗል፣
- የዋና መስኖ ቦይ የግንብ ሥራ 6,947 ሜ.ኩብ ተከናውኗል፡፡

**በ6 ወራት የተፈጠረ የሥራ ዕድል**

| የፕሮጀክቱ ስም | የሥራ ዕድል ተጠ.ቃሚ የሆኑ ዜጎች | | | | | | | | | የተቀጠረ ተቋራጭ ድርጅት ብዛት | የተቀጠረ አማካሪ ድርጅት ብዛት | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከ18-35 ዓመት | | | ከ35 ዓመት በላይ | | | ድምር | | | | | |
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | | | |
| ወልመል መስኖ ልማት ፕሮጀክት | 1167 | 259 | 1426 | 334 | 83 | 417 | 1501 | 342 | 1843 | 2 | 1 | 3 |

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** በግማሽ ዓመቱ ውስጥ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ ብር 397.52 ሚሊዮን ብር ታቅዶ 337.76 ሚሊዮን ብር ወይም የዕቅዱን 84.97 በመቶ ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ ውሏል፡፡

**ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰደ የመፍትሄ እርምጃ**

**ያጋጠሙ ችግሮች**

- የቦታው አቀማመጥ አስቸጋሪ በመሆን (10+500 to 12+500 ኪ.ሜ ፊደር ካናል) (Deep cut) ተቋራጭ ድርጅቱ ሥራውን በዕቅዱ መሰረት ማከናወን አለመቻሉ (ሎት-1)፣
- የሲሚንቶ ግብአት እጥረት (ሎት-1)፣
- የጠጠር እጥረት (Shortage of Aggregate) (ሎት-2)፣
- ተቋራጭ ድርጅት በሚፈለገው መጠን የግንባታ ማሽኖችን እና ግብአት ማቅረብ አለመቻሉ (ሎት-2)፡፡

**የተወሰደ የመፍትሄ እርምጃ፡-**

- አማካሪ ድርጅቱ ከተቋራጭ ድርጅቱ ጋር በመሆን አማራጭ የግንባታ አሰራር ስራአቶችን እንዲያቀርብ የሥራ መመሪያ ተሰጥቶታል፣

- ተቋራጭ ድርጅቱ የሲሚንቶ አቅርቦት ችግሩን እንዲፈታ ተነግሮታል በሚ/ር መ/ቤቱም በኩል ድጋፍ ተደርጎለታል፣
- ተቋራጭ ድርጅቱ በፕሮጀክቱ ላይ ያለውን የጠጠር አቅርቦት ችግር እንዲፈታ በአማካሪ ድርጅቱ በኩል በደብዳቤ እንዲገለፅለት እና ማሻሻያዎችን እንዲያደርግ ትዕዛዝ ተሰጥቶታል፣
- ተቋራጭ ድርጅቱ በሚፈለገው መጠን የግንባታ መሽኖችን እና ግብአት እንዲያቀርብ ደብዳቤ ተፅፎበታል፡፡

**ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፡-**

- በሎት-1 ላይ ወጥነት ያለው የሲሚንቶ አቅርቦት እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋል፣
- በሎት-2 ላይ የሚታየውን የጠጠር አቅርቦት ችግር እና የማሽን አቅርቦት እጥረትን በወቅቱ መፍታት ያስፈልጋል፡፡

## 6. የጨልጨል መስኖ ልማት ፕሮጀክት

**መግቢያ**

የጨልጨል የመስኖ ልማት ፕሮጀክት በ2012 በጀት ዓመት የተያዘ አዲስ ፕሮጀክት ሲሆን የሚገኘውም በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በባሌ ዞን ራይቱ ወረዳ ውስጥ ነው፡፡ ፕሮጀክቱ ተግባራዊ ሲደረግ ቁመቱ 46.5 ሜትር የሆነ ግድብ የሚገነባ ሲሆን 4,146 ሄክታር ማልማት የሚችል የመስኖ አውታር ግንባታም የሚከናወን ይሆናል፡፡ በፕሮጀክቱ ግንባታ ሁለት አገር በቀል ተቋራጭ ድርጅቶች የሚሳተፉ ሲሆን አንደኛው ተቋራጭ ድርጅት የግድብ ግንባታ ሥራውን ሲያከናውን ሁለተኛው ተቋራጭ ድርጅት ደግሞ የመስኖ አውታር ግንባታ ሥራውን የሚያከናውን ይሆናል፡፡

**የፕሮጀክቱ ዓላማ፡-**

የጨልጨል ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት ዓላማ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ የሥራ እድል መፍጠርና ድህነትን መቀነስ ናቸው፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግቦች፡ -**

- የግድብ እና ተያያዥ ስራዎች ግንባታን (ሎት-1) በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከደረሰበት የ12.93% አፈጻጸም ላይ 39.56% በማከናወን ወደ 52.49% ማድረስ፡፡
- የመስኖ መሬት ዝግጅት ሥራን (ሎት-2) በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከደረሰበት የ30.27% አፈጻጸም ላይ 64.65% በማከናወን ወደ 94.92% ማድረስ፡፡

**የፕሮጀክቱ የግማሽ ዓመት አፈጻጸም**

- እስከ ሁለተኛው ሩብ አመት መጨረሻ ድረስ የጨልጨል መስኖ ልማት ፕሮጀክትን (ሎት-1) 11.91 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 0.75 በመቶ ወይም የዕቅዱን 6.30% ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህም አጠቃላይ የፕሮጀክቱን የግንባታ አፈጻጸም በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 12.93% ወደ 13.68% ማድረስ ተችሏል፡፡
- እስከ ሁለተኛው ሩብ አመት መጨረሻ ድረስ የጨልጨል መስኖ ልማት ፕሮጀክትን (ሎት-2) 29.90 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 12.52 በመቶ ወይም የዕቅዱን 41.87% ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህም አጠቃላይ የፕሮጀክቱን የግንባታ አፈጻጸም በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 30.27% ወደ 42.79% ማድረስ ተችሏል፡፡

**ግቦቹን ለማሳካት የተከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፡-**

ሎት-1

- የዋና ግድብና ተያያዥ ሥራዎች በድዛይን ለውጥ ምክንይት ብዙ ሥራዎች ሣይሰሩ የቆየ ቢሆንም በአሁኑ ሰዓት ሙሉ በሙሉ የተሻሻለ የፕሮጀክቱ ድዛይን ዶኩሜንት ለኮንትራክተሩ የቀረበ (የተሰጠ) እና እንደ ስፒልዌይ አይነት የመሳሰሉ ስራዎችን ለመስራት የታቀደ ቢሆንም በኮንትራክተሩ አቅም ውስንነት እና ለስራ ያለው ተነሳሽነት ዚቅተኛ በመሆኑ ምክንያት ሥራውን እስከሁን መጀመር አልተቻለም፡፡

ሎት-2

- የዋናና ሁሌተኛ ቦይ አፈሪና ድንጋይ ቁፋሮ 35,492 ሜ.ኩ.
- የዋናና ሁሌተኛ ቦይ ከንክሪት ንጣፍ ሥራ 13,811 ሜ.ኩ.
- የዋናና ሁሌተኛ ቦይ ግንብ ግንባታ ሥራ 24,161 ሜ.ኩ.
- የዋና ቦይ አፈር መመለስ ሥራ 13,767 ሜ.ኩ.

**በ6 ወራት የተፈጠረ የሥራ ዕድል**

| የፕሮጀክቱ ስም | የሥራ ዕድል ተጠ.ቃሚ የሆኑ ዜጎች | | | | | | | | | የተቀጠረ ተቋራጭ ድርጅት ብዛት | የተቀጠረ አማካሪ ድርጅት ብዛት | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከ18-35 ዓመት | | | ከ35 ዓመት በላይ | | | ድምር | | | | | |
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | | | |
| ጨልጨል | 867 | 75 | 942 | 239 | 8 | 247 | 1124 | 76 | 1211 | 2 | 1 | 3 |

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** በግማሽ ዓመቱ ውስጥ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ ብር 242.68 ሚሊዮን ብር ታቅዶ 174.47 ሚሊዮን ብር ወይም የዕቅዱን 71.9 በመቶ ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ ውሏል፡፡

**ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች**

**ያጋጠሙ ችግሮች**

**ሎት 1፡-**

- ለተቋራጭ ድርጅቱ ሙሉ የተሻሻል የዋና ግድብና ስፒልዌይ ድዛይን ዶክመንት ቢቀርብለትም ድርጅቱ የግንባታ ሥራውን መጀመር አለመቻል፣
- በተቋራጭ ድርጅት የተፈጠረውን የመሽነሪና የግንባታ ቁሳቁስ ችግር ለመፍታት የተደረገውን ሂደት አጥጋቢ አለመሆኑ፣
- ተቋራጭ ድርጅቱ ፕሮጀክቱን በቅንጅት ያለመምራትና ያለመስራት እና ለፕሮጀክቱ የተሰጠ ትኩረት አናሳ መሆን፡፡

**ሎት 2፡-**

- የንዑስ ተቋራጮት አቅም ውስንነትና የተሰጣቸውን ሥራ በጥራት አለመስራት፣
- በአከባቢው ላይ የተከሰተው የውሃ እጥረት ተቋራጭ ድርጅቱ በሙሉ አቅሙ ወደ ሥራ እንዳይገባ መሆኑ፣
- ሥራዎችን በእቅድ መሰረት መሥራት መቸገር፡፡

**የተወሰደ የመፍትሄ እርምጃ፡-**

ሎት 1፡-

- ተቋራጭ ድርጅቱ የተስተካከለ ዲዛይን እንዲደርሰው ከተደረገ በኃላ በአማካሪ ድርጅቱ በኩል ተደጋጋሚ ደብዳቤዎች እንዲፃፉ በማድረግ ሥራውን በፍጥነት እንዲጀምር ለተቋራጭ ድርጅቱ ተገልፆለታል እንዲሁም የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ አመራሮች በተገኙበት የሦስትዮሽ ስብሰባ በማድረግ ተቋራጭ ድርጅቱ ወደ ሥራ እንዲገበ ተነግሮታል፣
- ተቋራጭ ድርጅቱ አስፈላጊውን የግንባታ ማሽነሪዎች እንዲያስገባ የሥራ ትዕዛዝ ተሰጦታል፣
- ተቋራጭ ድርጅቱ በመስክ ላይ ያለውን የሰው ኃይል በአግባቡ በመምራት ሥራውን እያሰራ ባለመሆኑ የተቋራጭ ድርጅቱ የፕሮጀክት ሥራ አስካሄጅ እንዲተካ በአማካሪ ድርጅቱ በኩል ደብዳቤ እንዲፃፍ ተደርጓል፡፡

**ሎት 2፡-**

- የተወሰኑ ንዑስ ተቋራጭ ድርጅቶች ውለታ እንዲቋረጥ እና የተሻለ አፈፃፀም ያላቸው ንዑስ ተቋራጭ ድርጅቶቸ ስራውን እንዲቀጥሉ ተደርጓል፣
- በአከባቢ ያለውን ከፍተኛ የውሃ እጥረት ችግር መፍታት እንዲቻል ተቋራጭ ድርጅቱ የውሃ ጉድጓድ እንዲቆፍር የስራ ትዕዛዝ ተሰጦታል ቁፋሮውንም ጀምሯል፣

- በግንባታ ወቀት ሊያጋጥም የሚችሉ ችግሮችን በመለየት የአሰሪው ተወካይ፣ተቋረጭ እና አማካሪ ድርጅቶች በጋራ በመሆን የተቋራጭ ድርጅቱ የአሰራር ስርአት እንዲሻሻል ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

**ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች**

- ሎት-1 ተቋራጭ ድርጅት ሙሉ ዲዛይን ከሁለት ወር በፊት ተጠናቆ የተሰጠው ቢሆንም ኮንትራክተሩ እስከሁን ምንም ዝግጅት አለመድጉ ወደፊት ፕሮጀክቱ በውለታው መሰረት ሊጠናቀቅ ስለማይችል በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል በውለታው መሰረት አስተዳደራዊ ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል፣
- በሁለቱም ተቋራጭ ድርጅቶች በኩል የግብአት (የማሽነሪ፣ የነዳጅ እና የሲምነቶ) አቅርቦት ችግሮች መፈታት እንዲችሉ ጥብቅ ክትትል ማድረግ፡፡

## 7. የላይኛው ጉደር የግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት

**መግቢያ**

የላይኛው ጉደር የግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት በ2012 በጀት ዓመት የተያዘ አዲስ ፕሮጀክት ሲሆን የሚገኘውም በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በምዕራብ ሸዋ ዞን ጉደር ወረዳ ውስጥ ነው፡፡ ፕሮጀክቱ ተግባራዊ ሲደረግ 40.6 ሜትር ከፍታ ያለው ግድብ ግንባታ የሚካሄድ ሲሆን 4,926 ሄክታር ማልማት የሚችል የመስኖ አውታር ግንባታም የሚከናወን ይሆናል፡፡ በፕሮጀክቱ ግንባታ ሁለት አገር በቀል ተቋራጭ ድርጅቶች የሚሳተፉ ሲሆን አንደኛው ተቋራጭ ድርጅት የግድብ እና ተያያዥ ሥራዎች ግንባታ የሚያካሂድ ሲሆን ሁለተኛው ተቋራጭ ድርጅት ደግሞ የመስኖ አውታር ግንባታ ሥራውን የሚያከናውን ይሆናል፡፡

**የፕሮጀክቱ ዓላማ**

የላይኛው ጉደር ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክትን ዓላማ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ የሥራ እድል መፍጠርና ድህነትን መቀነስ ናቸው፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግቦች፡-**

- የግድብ እና ተያያዥ ስራዎች ግንባታን (ሎት-1) በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከደረሰበት የ27.48% አፈጻጸም ላይ 38.20% በማከናወን ወደ 65.68% ማድረስ፡፡
- የመስኖ መሬት ዝግጅት ሥራን (ሎት-2) በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከደረሰበት የ6.75% አፈጻጸም ላይ 55.00% በማከናወን ወደ 61.75% ማድረስ፡፡

**የፕሮጀክቱ የግማሽ ዓመት አፈጻጸም**

- አስከ ሁለተኛው ሩብ አመት መጨረሻ ድረስ የላይኛው ጉደር መስኖ ልማት ፕሮጀክትን (ሎት-1) 17.85 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 6.32 በመቶ ወይም የዕቅዱን 35.39% ተግባራዊ

ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህም አጠቃላይ የፕሮጀክቱን የግንባታ አፈጻጸም በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 27.48% ወደ 33.80% ማድረስ ተችሏል፡፡

- እስከ ሁለተኛው ሩብ አመት መጨረሻ ድረስ የላይኛው ጉደር መስኖ ልማት ፕሮጀክትን (ሎት-2) 4.00 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 0.58 በመቶ ወይም የዕቅዱን 14.50% ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህም አጠቃላይ የፕሮጀክቱን የግንባታ አፈጻጸም በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 6.75% ወደ 7.33% ማድረስ ተችሏል፡፡

**ግቦቹን ለማሳካት የተከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፡-**

ሎት-1፡-

- የግድብ መሰረት አፈር ቁፋሮ ሥራ 39,586 ሜ.ኩ.
- የግድብ መሰረት ድንጋይ ቁፋሮ ሥራ 5,305 ሜ.ኩ.
- ለኮንክሪት ሙሌት የተፈጨ ጠጠር ምርት 3,837 ሜ.ኩ.
- ለግድብ ሙሌት የሚሆን የድንጋይ ምርት 11,274 ሜ.ኩ.

ሎት-2፡-

- የመስኖ ቱቦ መቅበሪያ ቦይ የድንጋይ ቁፋሮ ሥራ 73,186 ሜ.ኩ.
- የመስኖ ቱቦ መቅበሪያ ቦይ የአፈር ቁፋሮ ሥራ 3,222 ሜ.ኩ.

**በ6 ወራት የተፈጠረ የሥራ ዕድል**

| የፕሮጀክቱ ስም | የሥራ ዕድል ተጠቃሚ የሆኑ ዜጎች | | | | | | | | | የተቀጠረ ተቋራጭ ድርጅት ብዛት | የተቀጠረ አማካሪ ድርጅት ብዛት | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከ18-35 ዓመት | | | ከ35 ዓመት በላይ | | | ድምር | | | | | |
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | | | |
| የላይኛው ጉደር | 390 | 172 | 562 | 107 | 18 | 125 | 497 | 190 | 687 | 2 | 1 | 3 |

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** በግማሽ ዓመቱ ውስጥ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ ብር 188.75 ሚሊዮን ብር ታቅዶ 152.76 ሚሊዮን ብር ወይም የዕቅዱን 80.9 በመቶ ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ ውሏል፡፡

**ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰደ የመፍትሄ እርምጃ**

**ያጋጠሙ ችግሮች**

**ሎት 1፡-**

- የግድብ መሰረተ ቁፋሮ ስራ መዘግየት፣
- በቂ የሆነ ማሽነሪ አቅርቦት ያለመኖሩ፣

- የግድብ እና ተያያዥ ሥራዎች የመሰረት ማጠናከሪያ ግራዉቲንግ ስራ መዘግየት፣
- የኮንስትራክሽን ግብአት ምርት መዘግየት እና በበቂ ዳረጃ እየተመረተ ያለመሆኑ፣
- ኮንትራተሩ ከቀጠራቸዉ ንዑስ ተቋራጭ ድርጅቶት ጋር ያለዉ ግንኙነት ዳካማ መሆኑ፡፡

**ሎት 2፡-**

- ለፕሮጀክቱ ግንባታ የሚያስፈልግ ቦታ በወቅቱ ባለመለቀቁ የቁፋሮ ሥራዎች መዘግየት፣
- የመስኖ ቱቦ ግዥ ሂደት መዘግየት፡፡

**የተወሰደ የመፍትሄ እርምጃ፡-**

**ሎት 1፡-**

- ለተቋራጭ ድርጅቱ በወቅቱ የዲዛይን ማሻሻያ ስራዎች በአማካሪ ድርጅቱ በኩል ተጠናቆ እንዲደርሰው የተደረገ ሲሆን ተቋራጭ ድረጀጅቱ የመሰረት ቁፋሮ ሥረውን እንዲያጠናቅቅ ጥረት የተደረገ ቢሆንም በዕቅዱ መሰረት ሊያከነውን ባለመቻሉ ተደጋጋሚ ውይይቶችን በማድረግ ሥራውን እንዲያፋጥን ጥረት ተደርጓል እንዲሁም በአማካሪ ድርጅቱ በኩል ለተቋራጭ ድርጅቱ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ እንዲደርሰው ተደርጓል፣
- ተቋራጭ ድርጅቱ በቂ ማሽነሪ እንዲያስገባ የሥራ ትዕዛዝ ተሰጥቶታል፣
- ተቋራጭ ድርጅቱ አቅም ያለውን ተቋራጭ ድርጅት በመቅጠር ወይም በራሱ አቅም ሥራውን በፍጥነት እንዲያከናውን ተደጋጋሚ ውይይቶች በማድረግ የሥራ ትዕዛዝ ተሰጦታል፡፡ ሆኖም ተቋራጭ ድርጅቱ በራሴ አቅም ስራውን ሰራለው የሚል ውሳኔ ላይ በመድረሱ እና ይህን ለማድረግ የአቅም እና የልምድ ውስንነት ያለበት በመሆኑ አማካሪ ድርጅቱ ተቋራጭ ድርጅቱ ስራውን መስራት የሚችል አቅም እንዳለው ገምግሞ ለሚ/ር መ/ቤቱ እንዲያሳውቅ የሥራ ትዕዛዝ ተሰቶታል፣
- ተቋራጭ ድርጅቱ የግንባታ ግብአት በፍጥነት እንዲያመርት ተደጋጋሚ የሥራ ትዕዛዝ ተሰቶታል፣
- ተቋራጭ ድርጅቱ የሚቀጥራቸውን ንዑስ ተቋራጭ ድርጅቶች ለሚ/ር መ/ቤቱ እያሳወቀ ያማይቀጥር በመሆኑ የአሰራር ችግር በማጋጠሙ ከእንግዲ ንዑስ ተቋራጭ ድርጅቶች ሲቀጠሩ የሚ/ር መ/ቤቱ ፍቃድ እንዲጠየቅ የሥራ መመሪያ ለተቋራጭ ድርጅቱ እና አማካሪ ድርጅቱ ተላልፏል፡፡ እንዲሁም ያሉትን ንዑስ ተቋራጭ ድርጅቶች በአግባቡ እንዲያስተዳድር የሥራ መመሪያ ተሰጦታል፡፡

**ሎት 2፡-**

- ተቋራጭ ድርጅቱ በተስተካከለው ዲዛይን መሰረት የቦታ ይለቀቅልኝ ጥያቄ በወቅቱ እንዲያቀርብ የሥራ ትዕዛዝ ተሰጥቶታል እንዲሁም የካሳ ክፍያ በወቅቱ እንዲፈፀም በሚ/ር መ/ቤቱ በኩል ጥረት ተደርጓል፣

- ተቋራጭ ድርጅቱ እስካሁን እያካሄድ ያለው የተወሰነ የቁፋሮ ሥራዎች ላይ ብቻ ሲሆን የመስኖ ቱቦ ግዥ ሂደት በመዘግየቱ ተቋራጭ ድርጅቱ አፈፃፀሙ ዝቅተኛ ሆኗል፡፡ በመሆኑም ተቋራጭ ድርጅቱ የመስኖ ቱቦ ግዥ ሂደቱን አጠናቆ ዕቃው ከውጭ አገር በፍጥነት እንዲያስገባ ለተቋራጭ ድርጅቱ ተነግሮታል እንዲሁም ክትትል እየተደረገ ይገኛል፡፡

**ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች**

- የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የካሳ አሰራር መመሪያ በአፋጣኝ ሊወጣ ይገባዋል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን የካሳ አከፋፈል ሂደት ላይ ችግር እየተፈጠረ በመሆኑ ፕሮጀክቱ የሚቆምበት ደረጃ ሊደርስ ይችላል፣
- ለሚ/ር መ/ቤቱ እየተለቀቀ የነበረው ገንዘብ አነስተኛ የነበረ በመሆኑ ለተቋራጭ ድርጅቶች ክፍያ እና የካሳ ክፍያ በወቅቱ መክፈል ባለመቻሉ ፕሮጀክቱ ላይ ጫና ፈጥሮ ቆይቷል፡፡ ይህ የገንዘብ ፍሰት አሁን የተሻሻለ ቢሆንም መቀጠል ካልቻለ ችግር ሊሆን ስለሚችል ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው፣
- የወረዳ አስተዳደሮች በሚፈላገዉ ልክ ለፕሮጀክቱ ክብደት ባለመስጠታቸዉ የፕሮጀክቱ ስራ በተለያየ ወቅት ያለ ምክንያት ስራ የሚያስቆሙ ግለሰቦች ላይ እርምጃ ያለመዉሰዳቸዉ ፕሮጀክቱን ስለሚጎዳ ክልል ትኩረት እንድሰጠዉ ማድረግ ይስፈልጋል፡፡

## 8. የላይኛው ርብ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት

***መግቢያ***

የላይኛው ርብ መሰኖ ልማት ፕሮጀክት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በደቡብ ጎንደር ዞን በፎገራ እና ሊቦ ከምከም ወረዳ የሚገኝ ሲሆን በመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስጤር ባለቤትነት፣ በአማራ ውሀ ስራዎች ኮንስትረክሽን ድርጅት ተቋራጭነት  እና በአማራ ዲዛይንና ቁጥጥር ስራዎች ድርጅት  የግንባታ ማማከርና ቁጥጥር  እየተከናወነ የሚገኝ ፕሮጀክት ነው፡፡

ፕሮጀክቱ ከርብ ግድብ የሚለቀቀውን ውሃ በመጠቀም 7,200 ሄክታር መሬት በመስኖ በማልማት በፎገራ 6 ቀበሌ እና በሊቦ ከምከም 5 ቀበሌ የሚኖሩ 2,400 ገበሬዎች ተጠቃሚ የሚያደርግ እና አርሶ አደሮቹ በአመት ሶስት ጊዜ በማምረት የተሻለ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ እንዲሁም ከራሳቸው አልፈው በሀገር ደረጃ ለታቀደው የምግብ ዋስትና ማረጋገጥና ኢኮኖሚ እድገት አስተዋጽኦ እንዲሰጥ ማድረግ ነው፡፡

የፕሮጀክቱ ዋና ዋና ሥራዎች 40 ሜትር የውሃ መቀልበሻ (Weir)፣ 2.1 ኪ.ሜትር  ዋና ቦይ ( primyery canal)፣ 31.0 km የቀኝ ክንፍ የውሃ ቦይ ካናል (Right main canal)፣ 27.32 የግራ ክንፍ የውሃ ቦይ ካናል (Left main canal)፣ 58 የውሃ ማሻገርያ ኮንክሪት ፍሉም(RCC Flume)፣

145 የውሃ ማከፋፈያ ሳጥን (Division box)፣ 47.29 ኪ.ሜ ሁለተኛ ካናል (secondery canal)፣ 159.75 ኪ.ሜ ሶስተኛ ካናል (Tertiary canal) እንዲሁም ከ 60 ኪ.ሜ በላይ የውስጥ ለውስጥ መንገድ ግንበታን አካቶ እየተሰራ ያለ ፕሮጀክት ነው፡፡

**የፕሮጀክቱ ዓላማ፡-**

የላይኛው ርብ የወንዝ መቀልበሻና መስኖ ልማት ፕሮጀክት ዓላማ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ የሥራ እድል መፍጠርና ድህነትን መቀነስ ናቸው፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግቦች፡-**የወንዝ መቀልበሻና ዋና ቦይ እና የመስኖ መሰረተ ልማት ግንባታ ስራዎች ግንባታን በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከደረሰበት የ 22.08% አፈጻጸም ላይ 34% በማከናወን ወደ 56.08% ማድረስ፡፡

**የፕሮጀክቱ የግማሽ ዓመት አፈጻጸም**

አስከ ሁለተኛው ሩብ ዓመቱ መጨረሻ የላይኛው ርብ መስኖ ልማት ፕሮጀክትን 10.36 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 2.41 በመቶ ወይም የዕቅዱን 23.26% ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህም አጠቃላይ የፕሮጀክቱን የግንባታ አፈጻጸም በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 22.08% ወደ 24.49% ማድረስ ተችሏል፡፡

**ግቦቹን ለማሳካት የተከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፡-**

- የሰራተኛ መኖሪያ የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ግንባታ 100% ለማጠናቀቅ ታቅዶ ተጠቋናል፣
- የአናት ስራ ላይ አለት የማፈንዳት ስራ እና ጠያያዥ ስራዎች ተከናውነዋል፣
- የዋና ውሃ ቦይ አለት የማፈንዳት ስራ እንዲሁም የማስተካከል ስራ 100 % ተጠናቋል የግንብ ስራ በመሰራት ላይ ይገኛል፣
- ለውሃ ማሳለፊያ የሚያገለግል ኮንክሪት ቱቦ ግንበታ ተከናውኗል፣
- ዋና ቦይ፣ የግራ ዋና ቦይ እና የቀኝ ዋና ቦይ የግንብና ተያያዥ ግንባታ ሥራዎች ተከናውነዋል፣
- የቀኝ ዋና ቦይ ወደ ግራ ዋና ቦይ ሚያሻግር ድልድይ ስራ እየተጠናቀቀ ይገኛል
- የውሃውን ዋና ቦይ ተከትሎ የሚሰራ የመንገድ ስራ ተከናውኗል፡፡

**በሩብ ዓመት የተፈጠረ የሥራ ዕድል**

| የፕሮጀክቱ ስም | የሥራ ዕድል ተጠ.ቃሚ የሆኑ ዜጎች | | | | | | | | | የተቀጠረ ተቋራጭ ድርጅት ብዛት | የተቀጠረ አማካሪ ድርጅት ብዛት | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከ18-35 ዓመት | | | ከ35 ዓመት በላይ | | | ድምር | | | | | |
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | | | |
| የላይኛው | 728 | 412 | 1140 | 122 | 4 | 126 | 850 | 416 | 1266 | 1 | 1 | 2 |

| | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ርብ | | | | | | | | | | | | |

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** በግማሽ ዓመቱ ውስጥ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ ብር 152.35 ሚሊዮን ብር ታቅዶ 129.17 ሚሊዮን ብር ወይም የዕቅዱን 84.8 በመቶ ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ ውሏል፡፡

**ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰደ የመፍትሄ እርምጃ**

**ያጋጠሙ ችግር፡-**

- ተቋራጭ ድርጅቱ ፕሮጀክቱ በሚጠይቀው ልክ ቅድመ ዝግጅት አድርጎ ያለመግባት፣
- በጥናት ወቅት ይገኛል ከተባለው የአካባቢ ላይ ከፍተኛ የአሸዋ እጥረት ማጋጠም፣
- በተቋራጭ ድርጅቱ በኩል የነዳጅ፣ የሲሚንቶ እና የብረት አቅርቦት ችግር፣
- የካሳ ክፍያ ክንውን በመዘግየቱ አርሶ አደሮች ቅሬታ በማንሳት ግንባታ ባግባቡ እንዳይሰራ ማስተጓጎል፡፡

**የተወሰደ መፍትሄ፡-**

- ተቋራጭ ድርጅቱ ፕሮጀክቱ በሚጠይቀው ልክ በማቴሪያል፣ በማሽነሪና የሰው ኃይል ዝግጅት እንዲያደርግ በፕሮጀክት ባለቤቱ፣በአማካሪውና በተቋራጩ መካከል ተደጋጋሚ ውይይት ተደርጎ ለውጥ እንዲመጣ ተደርጓል፣
- የአሸዋ ችግርን ለመፍታት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ፣ በአማካሪው እና ተቋራጭ ድርጅቱ ባለሙያዎች በጋራ ችግሩን ለመፍታት ባደረጉት ጥረት ችግሩን ለመፍታት የሚያስችሉ አማራጮች እንዲቀርቡ በማድረግ ችግሩን ለመፍታት ጥረት ተደርጓል፣
- ተቋራጭ ድርጅቱ የነዳጅ፣ የሲሚንቶ እና የብረት አቅርቦት ችግሮችን እንዲፈታ ጥረት ተደርጓል፣
- በካሳ መዘግየት ምክኒያት ቅሬታ ካነሱ አረሶ አደሮች ጋር ተደጋጋሚ ውይይቶችን በማድረግ ለጊዜውም ቢሆን ስራ እንዲቀጥ ተደርጓል፡፡

**ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች**

- የአሸዋ እጥረትን በዘላቂነት ለመፍታት የቀረበውን አማራጭ ቶሎ ውሳኔ መስጠት፣
- ተቋራጭ ድርጅቱ በፕሮጀክቱ ላይ እየታየ ያለውን የነዳጅ አቅርቦት ችግር በዘላቂነት እንዲፈታ ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ፣
- የሲሚንቶ ፍላጎት ሳይቋረጥ የሚያገኙበት መንገድ መፈለግ፣
- የገንዘብ ፍሰቱ እንዲሻሻል በማድረግ የመሬት ካሳ ግምት በሚ/ር መ/ቤቱ በኩል በወቅቱ መክፈል አስፈላጊ ይሆናል፡፡

## 9. ዱብቲ ዳይክና የመስኖ አውታር ጥገና

**መግቢያ**

የተንዳሆ PC-16 መስኖ ልማት ፕሮጀክት የጥገና ስራ ለማሰራት የኮንትራት ስምምነት በመስኖ ልማት ኮሚሽን እና በአፋር ውሀ ስራዎች ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ ሚያዝያ 26, 2012 ዓ.ም. ተከናውኖ የግንባታ ስራ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

ተንዳሆ PC-16 የጎርፍ መከላከያ ዳይክ ግንባታ እና የመስኖ ቦይ ጥገና ፕሮጀክት የሚገኘው በሰሜን ምስራቅ ኢትዮጵያ በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዞን 1 (በአውሲ ረሱ ዞን) ዱብቲ ወረዳ ከአዲስ አበባ 650 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡

አሁን ባለው ሂደት በተንዳሆ PC-16 መስኖ ልማት ፕሮጀክት 2,521 ሄ/ር መሬት ለማልማት የመስኖ አውታርና ተያያዥ የግንባታ ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡

**የፕሮጀክቱ ዓላማ**

በተንዳሆ PC-16 ፕሮጀክት አካባቢ በተደጋጋሚ የሚከሰተውን ጎርፍ በመከላከልና የተበላሸውን የመስኖ አውታር በመጠገን ለህብረተሰብ አገልግሎት ማዋል፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግብ፡-**

- የዳይክ እና የመስኖ አውታር ጥገና ስራዎች በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከደረሰበት የ 8.72% አፈጻጸም ላይ 91.28% በማከናወን ወደ 100% ማድረስ፡፡

**የፕሮጀክቱ የግማሽ ዓመት አፈጻጸም**

እስከ ሁለተኛው ሩብ ዓመቱ መጨረሻ የዱብቲ ዳይክ ጥገናና የመስኖ አውታር ግንባታ ፕሮጀክትን 44.36 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 11.12 በመቶ ወይም የዕቅዱን 25.07% ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህም አጠቃላይ የፕሮጀክቱን የግንባታ አፈጻጸም በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 8.72% ወደ  19.84% ማድረስ ተችሏል፡፡

**ግቦቹን ለማሳካት የተከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፡-**

- ለቦይ ሙሌት ስራ የሚሆን የተመረጠ አፈር ማምረቻ ቦታ ተለይቶ አስፈላጊው የአፈር መርመራ (ቴስት) ተሰርቷል፡፡
- የተቀዳሚ መስኖ ቦይ (PC) ጥገና ሥራ ላይ የማሶነሪ ጥገና ሥራ ተጠናቋል በተጨማሪም 5 የውሃ መቆጣጠሪያ ጌት ተሰርቷል፡፡
- የዳይክ ግንባታ ወደ 40,000 ሜ.ኪ የሙሌት እና ቆረጣ ስራ ተከናውኗል

**በሩብ ዓመት የተፈጠረ የሥራ ዕድል**

| የፕሮጀክቱ | የሥራ ዕድል ተጠ.ቃሚ የሆኑ ዜጎች | የተቀጠረ | የተቀጠረ | ድምር |
|---|---|---|---|---|

| ስም | ከ18-35 ዓመት | | | ከ35 ዓመት በላይ | | | ድምር | | | ተቋራጭ ድርጅት ብዛት | አማካሪ ድርጅት ብዛት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | | | |
| የዱብቲ ዳይክና የመስኖ አውታር ጥገና | 22 | 4 | 26 | 14 | 0 | 14 | 36 | 4 | 40 | 1 | 1 | 2 |

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** በግማሽ ዓመቱ ውስጥ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ ብር 116.65 ሚሊዮን ብር ታቅዶ 4.39 ሚሊዮን ብር ወይም የዕቅዱን 3.8 በመቶ ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ ውሏል፡፡

***ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰደ የመፍትሄ እርምጃዎች***

***ያጋጠመ ችግር፡-***

- በክልሉ ተከስቶ በነበረው የፀጥታ ችግር ምክንያት የግንባታ ማሽኖችን ሲያንቀሳቅሱ የነበሩ ግለሰቦች ስራ ምቀቅ እና እነሱን የሚተካ በወቅቱ አለማግኘት፣
- የስራ ተቋራጩ በዕቅዱ መሰረት ለስራው አስፈላጊ የሆነውን የሰው ሀይልና ማሽነሪ ማሟላት አለመቻሉ፣
- ከህግ ማስከበር ሂደቱ ጋር ተያይዞ የፕሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ  በሥራ ቦታ አለመገኘት፣
- የማህበራዊ ችግሮች በተደጋጋሚ ጊዜ ማጋጠም እና በዚህም ተቋራጭ ድርጅቱ ለተደጋጋሚ ጊዜ ስራ ማቆሙ፣
- በሚ/ር መ/ቤቱ በኩል በወቅቱ ክፍያዎችን አለመፈፀም ችግር፡፡

**የተወሰደ መፍትሄ፡-**

- ተቋራጭ ድርጅቱ ማሽኖችን የሚየንቀሳቅሱ ባለሙያችን በፍጥነት እንዲተካ በደብዳቤ እና በሦስትዮሽ ውይይቶች ላይ እንዲገለፅለት በማድረግ ችግሩ እንዲፈታ ጥረት ተደርጓል፣
- ተቋራጭ ድርጅቱ በዕቅዱ መሰረት የሰው ኃይል እና የግንባታ ግብአቶችን እንዲየሟላ ለተደጋጋሚ ጊዜ በደብዳቤ እና በቃል እንዲነገረው ተደርጓል፣
- የፕሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ በአስቸኳይ እንዲተካ በደብዳቤ ለተቋራጭ ድርጅቱ ተገልፆለታል፣
- ከሚመለከታቸው የክልል፣ የዞን እና የወረዳ አመራሮች በተገኙበት ውይይት በማድረግ ችግሩ እንዲፈታ ጥረት ተደርጓል፡፡ በዚህም የተወሰነ መሻሻል ቢመጣም ችግሩ ሙሉ በሙሉ ሊፈታ ግን አልቻለም፡፡ ወደፊት የክልል አመራሮች ባሉበት ችግሩ እንዲፈታ ውይይት ለማድረግ ታቅዷል፣

- ለሚ/ር መ/ቤቱ ይለቀቅ የነበረው ወራዊ የገንዘብ ፍሰት አነስተኛ በመሆኑ ለተቋራጭ ድርጅቱ ክፍያ መፈፀም ሳይቻል ቆይቷል፡፡ አሁን ግን የገንዘብ ፍሰቱ የተስተካከለ በመምጣቱ ክፍያዎች በሙሉ እንዲለቀቁ ተደርጓል፡፡

**ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች**

- የቀበሌና የወረዳ አመራሮች የስራውን አስፈላጊነት በመረዳት የሚከሰቱ ችግሮችን ለመፍታት ጥረት እንዲያደርጉ ማድረግ ያስፈልጋል፣
- የስራ ተቋራጩ የተሟላ ላብራቶሪ እንዲኖረው ግፊት ማድረግ ያስፈልጋል፣
- ተቋራጭ ድርጅቱ ለስራው በሚያስፈልገው ልክ የሰው ሃይል እና ማሽነሪ ወደ ስራ እንዲያስገባ ግፊትና ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል፣
- ወደፊት ለተቋራጭ ድርጅቱ ክፍያዎች እንዳይዘገዩ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## 10. አጂማ ጫጫ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት

***መግቢያ፡-***

የአጂማ ጫጫ መስኖ ልማት ፕሮጀክት የሚከናወነው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ሸዋ ዞን በአንጎለላ ጠራ ወረዳ በአጀማ ወንዝ ላይ ሲሆን 372 ሜትር ርዝመት (crest length) 45.5 ሜትር ከፍታ እንዲሁም 55.1ሚሊዮን ሜ. ኪዩብ ውሃ የመያዝ አቅም ያለው ግድብ በመገንባት የአንለላ ጠራን ና የባሶን ወረዳ ያካተተ 10 ቀበሌዎቸ ወስጥ 7 ሺህ ሄክታር መሬት በመስኖ እንዲያለማ ማድረግ ና 14 ሺህ አባውራዎችን የሚጠቅም ሲሆን በተጨማሪም የፕሮጀክቱ ቀዳሚ ዓላማ በሀገርም ሆነ በክልል ደርጃ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ የሥራ እድል መፍጠርና ድህነትን መቀነስ ነው፡፡እንዲሁም የአጅማ ጫጫ መስኖ ልማት ፕሮጀክት በ 3 ሎት የተከፈለ ሲሆን ሎት-1 ና ሎት-2 የ ቀኝ ና የግራ መስኖ አውታሮች ሲሆኑ ሎት-3 ግድብ ና ተያያዥ ስራዎችን ያካተተ ነው።

**የፕሮጀክቱ ዓላማ፡-**

የአጂማ ጫጫ መስኖ ልማት ፕሮጀክትን በመተግበር ረገድ ያለው ቀዳሚ ዓላማ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ የሥራ እድል መፍጠርና ድህነትን መቀነስ ናቸው፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግብ፡-**

- የግድብ እና ተያያዥ ስራዎች ግንባታን (ሎት-3) በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከደረሰበት የ22.82% አፈጻጸም ላይ 34.00% በማከናወን ወደ 56.82% ማድረስ፡፡
- የመስኖ መሬት ዝግጅት ሥራን (ሎት-1) 20.00% በማከናወን ወደ 20.00% ማድረስ፡፡
- የመስኖ መሬት ዝግጅት ሥራን (ሎት-2) 20.00% በማከናወን ወደ 20.00% ማድረስ፡፡

**የፕሮጀክቱ የግማሽ ዓመት አፈጻጸም**

- አስከ ሁለተኛው ሩብ አመት መጨረሻ ድረስ የአጂማ ጫጫ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት (ሎት-1) 5.00 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 2.25 በመቶ ወይም የዕቅዱን 45.00% ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህም አጠቃላይ የፕሮጀክቱን የግንባታ አፈጻጸም በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 0.50% ወደ 2.75% ማድረስ ተችሏል፡፡
- አስከ ሁለተኛው ሩብ አመት መጨረሻ ድረስ የአጂማ ጫጫ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት (ሎት-3) 13.40 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 4.31 በመቶ ወይም የዕቅዱን 32.16% ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህም አጠቃላይ የፕሮጀክቱን የግንባታ አፈጻጸም በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 22.82% ወደ 27.13% ማድረስ ተችሏል፡፡

**ግቦቹን ለማሳካት የተከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፡-**

**ሎት-1፡-**

- የዋና መስኖ ቦይ የአፈር ቁፋሮ ሥራ 34,734.091 ሜ.ኩ. ተሰርቷል፣
- የዋና መስኖ ቦይ የግንብ ግንባታ ሥራ 2,200 ሜ.ኩ. ተሰርቷል፣
- የተቋራጭ እና አማካሪ ድርጅቶች የመኖሪያ ቤቶች እና ቢሮዎች እየተገነቡ ይገኛሉ፡፡

**ሎት-3፡-**

- የቁፋሮ ሥራ 6,267 ሜ.ኩ. ተሰርቷል፣
- የኮንክሪት ሙሌት1,432 ሜ.ኩ. ተሰርቷል፣
- የኮንክሪት ብረት 96,198 ኪ.ግ. ተሰርቷል፣
- የመስኖ ውሃ ማስወጪያ ቁቦ ቀበራ 64 ሜትር ተሰርቷል፡፡

**በ6 ወራት የተፈጠረ የሥራ ዕድል**

| የፕሮጀክቱ ስም | የሥራ ዕድል ተጠ.ቃሚ የሆኑ ዜጎች | | | | | | | | | የተቀጠረ ተቋራጭ ድርጅት ብዛት | የተቀጠረ አማካሪ ድርጅት ብዛት | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከ18-35 ዓመት | | | ከ35 ዓመት በላይ | | | ድምር | | | | | |
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | | | |
| የአጂማ ጫጫ | 1,492 | 644 | 2,136 | 250 | 6 | 256 | 1,742 | 650 | 2,392 | 1 | 1 | 2 |

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** በግማሽ ዓመቱ ውስጥ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ ብር 191.4 ሚሊዮን ብር ታቅዶ 26.45 ሚሊዮን ብር ወይም የዕቅዱን 13.8 በመቶ ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ ውሏል፡፡

**ያጋጠመ ችግር፡-**

**ሎት-1፡-**

- ዋና የመስኖ ቦይ የሚገነባበት ቦታ ላይ የ formation ለውጥ መኖሩ አለመግባባቶችን ፈጥሮ ለተወሰነ ጊዜ ሥራው እንዲቆም መደረጉ፣
- ዋና ካናል ላይ አንዳንድ የግለሰብ ቤቶች መኖራቸው በነጻነት ለመስራት መቸገር፣
- በተቋራጩ በኩል የግልባጭ መኪና እጥረት መኖሩ፡፡

**ሎት-3፡-**

- በፕሮጀክቱ ላይ የOPC ሲሚቶ እጥረት መከሰት፣
- ፕሮጀክቱ ያለበት አካባቢ የጦርነት ቀጠና ሆኖ የቆየ በመሆኑ ተቋራጭ ድርጅቱ በሙሉ አቅም ወደ ሥራ መግባት አልቻለም እንዲሁም ለ 15 ቀናት ያክል በጦርነቱ ሳቢያ ፕሮጀክቱ ሙሉ በሙሉ ተዘግቶ መቆየቱ፣
- የግድብ ሙሌት ግብአት ማምረቻ ቦታ ወሰን የማስከበር ስራ መዘግየት፣
- የመሰረት ማጠናከሪያ ሥራ (grouting) ቢጀመርም በምንፈልገው ፍጥነት ሥራው እየሄደ አለመሆኑ፣
- ወረዳው የካሳ ግምቶችን በወቅቱ አስልቶ ቶሎ ወደ አሰሪ መሰሪያ ቤቱ አለመላክ፡፡

**የተወሰደ መፍትሄ፡-**

**ሎት-1፡-**

- የ Formation ለውጥ ችግር ሙሉ በሙሉ መፍትሄ እንዲሰጠው ተደርጓል፣
- ተቋራጩ ቤት ያለበትን አካባቢን እያለፉ መስራት እንዲችሉ ተድርጓል፣
- ተቋራጭ ድርጅቱ ያለበትን የገልባጭ መኪናዎች ችግር በፍጥነት እንዲፈታ በደብዳቤ እና በቃል እንዲነገረው በማድረግ ችግሩ እንዲፈታ ጥረት ተደርጓል፡፡

**ሎት-3፡-**

- ተቋራጭ ድርጅቱ ሲሚንቶ ለማቅርብ ባደርጉት ጥረት ከፍብሪካዎች ጋር ዘላቂ ግንኙነት በመፍጠር በአሁኑ ሰዓት የሲሚንቶ ችግር ሙሉ በሙሉ ተፈቷል እንዱሁም አማካሪ ድርጅቱ እና አሰሪ መስሪያቤቱ በመነጋገር opc ለጊዜው ሲጠፉ የጥራት ችግር ስላማያመጣ በ ppc የተወሰኑ ስትራክቸሮችን እየሰራ እንዲቆይ መወሰኑ ችግሩን ለማቃለል ጥረት ተደርጓል፣
- የፀጥታ ችግሩ እንደተፈታ ተቋራጭ ድርጅቱ በፍጥነት ወደ ሥራ እንዲመለስ ተደርጓል የማካካሻ ዕቅድ እንዲያዘጋጅ ተደርጓል፣
- በአሁኑ ሰአት የወሰን ማስከበር ስራ ለስራ እንቅፋት በማይሆን መልኩ እንዲፈታ ተደርጎ የግንባታ ግብአት ማምረት በቅርብ ቀናት ውስጥ የሚጀመር ይሆናል፣

- ከተቋራጭ ድርጅቱ ጋር በመነጋገር እና ችግሮች እንዲፈቱ በማድረግ የ grouting ስራ ከዚህ በተሻለ ሁኔታ እንዲፈጥን ክትትላችንና ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል፣
- አዲስ ከተዋቀረው የወረዳ መስተዳድር ጋር በመነጋገር የተሰራ የካሳ ግምት በፍጥነት ወደ ሚ/ር መ/ቤቱ እንዲክ ስምምነት ላይ ተደርሷል በዚህም ለውጥ ይመጣል ተብሎ ይገመታል፣

**ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፡-**

- የሲሚንቶ አቅርቦት ችግርን ለመፍታት በተለመደው አግባብ ለተቋራጭ ድርጅቶች ከፋብሪካዎች ጋር የሚያገናኝ ደጋፊ ደብዳቤ በመፃፍ መፍታት ያስፈልጋል፣
- የመሬት ካሳ ቶሎ ተሰርቶ እንዲቀርብ ግፊት ማድረግ፣
- ተቋራጭ ድርጅቱ ሥራ ከጀመረ በኃላ እንዳያቆም የወሰን ማስከበር ስራ ገሥራው እየቀደመ እንዲሰራ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፣
- ከፕሮጅት ሳይት ላይ ያልተጀመሩ ሎቶችን ቶሎ ወደ ስራ እንዲገቡ ግፊት ማድርግ (ለምሳሌ ሎት-2)፣
- የካሳ ክፍያ ወረዳው ቶሎ ሰረቶ ባለመላኩ ባለመሬቶቹ ስራ እንዳያስቆሙ ስጋት ስላለ በዚህ ላይ ቀድሞ መስራት ያስፈልጋል፣
- የካምፕ ስራዎች ከዚህ በፊት የተሰሩት በቆርቆሮ ሲሆን አሁን በጨረታ ሂደት ላይ ያለው ሎት-2 ወደ ብሎኬት ቤት ተቀይሮ መስራት ቢችል፡፡ ይህ በመሆኑ እንደ PMU የሚያገለግል በመሆኑ፡፡
- የሎት-2 የጨረታ ሂደት በፍጥነት ተጠናቆ ሥራው በ2014 የበጀት አመት ተግባራዊ እንዲሆን ከወዲሁ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፤
- የሎት-3 ተቋራጭ ድርጅት በ2013 የበጀት አመት ያሳየውን የተሻለ የሥራ አፈፃፀም እንዲያስቀጥል የተለየ ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

## 11. ካሊድ ዲጆ መስኖ ልማት ፕሮጀክት

**የፕሮጀክቱ ዓላማ፡-**

የካሊድ ዲጆ መስኖ ልማት ፕሮጀክትን በመተግበር ረገድ ያለው ቀዳሚ ዓላማ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ የሥራ እድል መፍጠርና ድህነትን መቀነስ ናቸው፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግብ፡-** የግድብ እና ተያያዥ ስራዎች ግንባታን እና የመስኖ አውታር ግንባታ በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከደረሰበት የ4.69% አፈጻጸም ላይ 63.54% በማከናወን ወደ 68.23% ማድረስ፡፡

**የፕሮጀክቱ የግማሽ ዓመት አፈጻጸም**

እስከ ሁለተኛው ሩብ አመት መጨረሻ ድረስ የካሊድ ዲጆ መስኖ ልማት ፕሮጀክትን 25.42 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 3.79 በመቶ ወይም የዕቅዱን 14.90% ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህም አጠቃላይ የፕሮጀክቱን 2013 የበጀት አመት ከደረሰበት 4.69% ወደ 8.48% ማድረስ ተችሏል፡፡

**ግቦቹን ለማሳካት የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፡-**

- የግድብ መሰረት ቁፍሮ እና ማስወገድ ሥራ 565,000 ሜ.ኩ. ተከናውኗል፤
- የውሃ ማስወጫ (Spillway) የመሰረት ቁፋሮ ሥራ 29,000 ሜ.ኩ. በላይ ተከናውኗል፣
- የግድብ መሰረት ማጠናከሪያ ሥራ (grouting and fault treatment work) ንዑስ-ተቋራጭ ድርጅት በመቅጠር ሥራው በመከናወን ላይ ይገኛል፣
- የ 6.7 ኪ የመዳረሻ መንገድ ጠረጋ እና ሙሌት ሥራ ተከናውኗል፤
- 68,000 ሜ.ኩብ ለግድብ ግንባታ የሚሆን ደቃቅ አሸዋ፣ 70,000 ሜ.ኩብ ለግድብ ግንባታ የሚሆን ድንጋይ እና 27,000 ሜ.ኩብ ለመንገድ ግንባታ የሚሆን የተመረጠ ድንጋይ፣ 30,000 ሜ.ኩብ ለግድብ ሙሌት የሚሆን የሸክላ አፈር ምርት እና 12,000 ሜ.ኩብ ምልስ አፈር ምርት ተመርቷል፣
- የመስኖ መስመር ዝርጋታ (main canal preparation work) የመሰረተ ቁፋሮ ለማስጀመር እንቅስቃሴ ተጀምሯል፣
- አብዛኛው የተቋራጭ ድርጅቱ እና የአማካሪ ድርጅቶች መኖሪያ ቤቶች እና ቢሮዎች ግንባታ ተጠናቋል፤

**በሩብ ዓመት የተፈጠረ የሥራ ዕድል**

| የፕሮጀክቱ ስም | የሥራ ዕድል ተጠ.ቃሚ የሆኑ ዜጎች | | | | | | | | | የተቀጠረ ተቋራጭ ድርጅት ብዛት | የተቀጠረ አማካሪ ድርጅት ብዛት | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከ18-35 ዓመት | | | ከ35 ዓመት በላይ | | | ድምር | | | | | |
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | | | |
| ካሊድ ዲጆ መስኖ ልማት | 45 | 30 | 75 | 27 | 15 | 42 | 72 | 45 | 117 | 1 | 1 | 2 |

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** በግማሽ ዓመቱ ውስጥ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ ብር 180.0 ሚሊዮን ብር ታቅዶ 67.04 ሚሊዮን ብር ወይም የዕቅዱን 37.2 በመቶ ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ ውሏል፡፡

**ያጋጠሙ ችግሮች፡-**

- ግድብ የሚገነባበት ቦታ ላይ ለሚኖሩ ባለይዞታዎች በወቅቱ ካሳ ከፍሎ ማንሳት ባለመቻሉ ተቋራጭ ድርጅቱ በሙሉ አቅሙ የመሰረት ቁፋሮ ሥራውን ማከናወን አለመቻሉ፣
- በባለድርሻ አካላት በኩል የሚደረግ እገዛ እና ድጋፍ ፕሮጀክቱ ከሚፈልገው አንጻር ሲገመገም ዝቅተኛና የዘገየ መሆን፣
- በስራ ተቋራጭ ድርጅቱ በኩል የማሽነሪ አቅርቦት አነስተኛ መሆን፣
- በሚ/ር መ/ቤቱ በኩል የክፍያ መዘግየት፣
- ተቋራጭ ድርጅቱ ለግንባታ ሥራ የሚውሉ አስፈላጊ የሆኑ ከፍተኛ አቅም ያለውን የሲሚንቶ ማብኪያ ማሽን፣ የድንጋይ መፍጫ እና የውሃ ማጠጫ መኪናዎችን በወቅቱ ማቅረብ አለመቻሉ፡፡

**የተወሰደ መፍትሄ፡-**

- የካሳ ግመታ ስራ ተጠናቆ ወደ ዋናው መስሪያ ቤት እንዲላክ ተደርጓል በተጨማሪም ካሳ የተከፈለባቸውን የመስሪያ ቦታ እንዲለቀቅ በስራው ባለቤት ተወካይ በኩል ግፊት ተደርጓል። ለካሳ ክፍያ የሚውል ገንዘብ እንዲለቀቅ በማድረግ ለካሳ ክፍያ የሚሆን ገንዘብ ወደ ወረዳው በመላክ ላይ ይገኛል፣
- ከሚመለከታቸው የክልል፣ ዞን እና ወረዳ መስተዳደሮች ጋር ተደጋጋሚ ውይይቶችን በማድረግ ለፕሮጀክቱ የሚፈለገው ድጋፍ እና እገዛ እንዲደረግ ግፊት ተደርጓል፣
- ለስራ ተቋራጩ ተጨማሪ ማሽነሪ እንዲያስገባ በአማካሪው በኩል ደብዳቤ እንዲፃፍ አድርገናል እንዲሁም በስራው ባለቤት ተወካይ በኩል የስራ አፈጻጸማቸውን በተመለከተ ለስራ ተቋራጩ ደብዳቤ እንዲገለፅለት ተደርጓል፣
- ተቋራጭ ድርጅቱ በወቅቱ የክፍያ ጥያቄ ባለማቅረቡ ምክንያት የክፍያ መዘግየት እንዳለ ሆኖ ጥያቄው ወደ ሚ/ር መ/ቤቱ ከመጣ በኃላ ክፍያው በገንዘብ ፍሰት እጥረት ምክንያት የዘገየ ቢሆንም አሁን ገንዘቡ እንዲለቀቅ በመደረጉ ችግሩ እንዲፈታ ተደርጓል፣
- ተቋራጭ ድርጅቱ አስፈላጊ የሆኑ የግንባታ ማሽነሪዎችን ወደ ፕሮጀክቱ እንዲያስገባ የሥራ ትዕዛዝ ተሰጥቶታል እንዲሁም በአማካሪ ድርጅቱ በኩል የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ለተቋራጭ ድርጅቱ እንዲደርሰው ተደርጓል፡፡

**ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፡-**

- ወደፊት ፕሮጀክቱ በታቀደለት ዕቅድ መሰረት እንዲቀጥል የክፍያ መዘግየት ትኩረት የሚፈልግ ጉዳይ ነው፣
- ምንም እንኳን የካሳ ክፍያ ጥያቄዎች ዘግይተው ወደ ሚ/ር መ/ቤቱ የሚደርስ ቢሆንም የካሳ ክፍያ ጥያቄ በወቅቱ በሚ/ር መ/ቤቱ በኩል መልስ ሊሰጥበት የሚገባ ነው፣

- የስራ ተቋራጭ የአቅም ውስንነት እና ከዋናው መስሪያ ቤት ጋር ተናቦ የመስራት ችግሮች እንዲፈቱ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፣
- የዞኑና የወረዳ አስተዳደር ለስራው የሚያሳየው ትኩረት አናሳ መሆን ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡

## 12. የወይቦ ግድብና ተያያዥ ስራዎች የመስኖልማትፕሮጀክት

**መግቢያ፡-**

የወይቦ ግደብ ናተያያዥ ስራዎች መስኖ ልማት ፕሮጀክት የሚከናወነው በደ/ብ/ብ/ህ/ክልላዊ መንግስት ወላይታ ሶዶ ዞን በቦሎሶ ሶሬ ወረዳ ወይቦ ወንዝ ላይ ሲሆን 660 ሜት ርዝመት (crest length) 33 ሜትር ከፍታ እንዲሁም 60 ሚሊዮን ሜ. ኪዩብ ውሃ የመያዝ አቅም ያለው ግድብ በመገንባት የቦሎሶ ሶሬን ና የቦሎሶ ቦምቤ ወረዳ ያካተተ 11 ቀበሌዎች ወስጥ 3230 ሺ.ህ ሄክታር መሬት በመስኖ እንዲያለማ ማድረግ ሲሆን በተጨማሪም የፕሮጀክቱ ቀዳሚ ዓላማ በሀገርም ሆነ በክልል ደርጃ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣የሥራ እድል መፍጠርና ድህነትን መቀነስ ነው፡፡እንዲሁም የወይቦ ግድብና ተያያዥ ስራዎች ግንባታፕሮጀክት  በ2 ሎት የተከፈለ ሲሆን ሎት-1 ና ሎት-2  ሲሆኑ ሎት1 የግድብ ተያያዥ ስራዎችንን ሎት2፤የ ቀኝ ና የግራ መስኖ አውታሮች ያካተተ ነው።

**የፕሮጀክቱ ዓላማ፡-**

የወይቦ መስኖ ልማት ፕሮጀክትን በመተግበር ረገድ ያለው ቀዳሚ ዓላማ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ የሥራ እድል መፍጠርና ድህነትን መቀነስ ናቸው፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግብ፡-**

- የወይቦ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ስራን አስጀምሮ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሎት-1፡ 30% እንዲሁም ሎት-2፡ 57% ለማከናወን ታቅዷል፡፡

**የፕሮጀክቱ የግማሽ ዓመት አፈጻጸም**

- እስከ ሁለተኛው ሩብ አመት መጨረሻ ድረስ የወይቦ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት (ሎት-1) 7.50 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 0.40 በመቶ ወይም የዕቅዱን 5.33% ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህም አጠቃላይ ፕሮጀክቱን 0.40% ማድረስ ተችሏል፡፡
- እስከ ሁለተኛው ሩብ አመት መጨረሻ ድረስ የወይቦ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት (ሎት-2) 14.25 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 2.92 በመቶ ወይም የዕቅዱን 20.49% ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህም አጠቃላይ ፕሮጀክቱን 2.92% ማድረስ ተችሏል፡፡

**ግቦቹን ለማሳካት የተከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፡-**

**ሎት-1፡-**

- የካምፕ ግንበታ ስራ፡፡

**ሎት-2፡-**

- የካምፕ ግንበታ ስራ፣
- የዲዛይን ማሻሻያ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

**በሩብ ዓመት የተፈጠረ የሥራ ዕድል**

| የፕሮጀክቱ ስም | የሥራ ዕድል ተጠ.ቃሚ የሆኑ ዜጎች | | | | | | | | | የተቀጠረ ተቋራጭ ድርጅት ብዛት | የተቀጠረ አማካሪ ድርጅት ብዛት | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከ18-35 ዓመት | | | ከ35 ዓመት በላይ | | | ድምር | | | | | |
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | | | |
| የወይቦ መስኖ ልማት ፕሮጀክት | 90 | 79 | 169 | 15 | 1 | 16 | 105 | 80 | 185 | 1 | 1 | 2 |

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** በግማሽ ዓመቱ ውስጥ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ ብር 180.0 ሚሊዮን ብር ታቅዶ 67.04 ሚሊዮን ብር ወይም የዕቅዱን 37.2 በመቶ ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ ውሏል፡፡

**ያጋጠመ ችግር፡-**

**ሎት-1፡-**

- በተቋራጭ ድርጅቱ ድክመት ምክንያት የካምፕ ስራ አፈጻፀም ዝቅተኛ መሆን፣
- በቅየሳ ጊዜ ቀድሞ የተቀመጠው ቢንች ማረክ አለመግጠም ችግር፣
- የወስን ማሰከበር ስራ ቀድሞ ያለ መጀመር፣ የውሰን ማሰከበር እና የሀብት ቆጠራ ስራ በፍጥነት ማከናወን አለመቻል፣
- ለቅየሳ ስራ አካባቢው ምቹ ያለመሆን፡፡

**ሎት-2፡-**

- የዲዛይን ማሻሻያ ስራ ማጋጠሙ እና ይህም ጊዜ መውሰዱ፣
- በቅየሳ ጊዜ ቀድሞ የተቀመጠው ቢንች ማረክ አለመግጠም ችግር፣
- የወስን ማሰከበር ስራ ቀድሞ ያለ መጀመር፣ የውሰን ማሰከበር እና የሀብት ቆጠራ ስራ በፍጥነት ማከናወን አለመቻል፣
- ለቅየሳ ስራ አካባቢው ምቹ ያለመሆን፡፡

**የተወሰደ መፍትሄ፡-**

**ሎት-1፡-**

- ተቋራጭ ድርጅቱ የካምፕ ስራውን በፍጥነት እንዲጀምርና እንዲያጠናቀቅ በአማካሪ ድርጅቱ በኩል በደብዳቤ እንዲገለፅለት ተደርጓል እንዲሁም በመስክ ላይ በሚደረጉ የሦስትዮሽ ስብሰባ ላይ ጉዳዩ ውይይት እንዲደረግበት ተደርጓል፣
- የቅየሳ ሥራው እንዲቀጥል የቤንች ማርክ እንደ አዲስ እንዲቀመጥ ተደርጓል፣
- የውሰን ማስከበር ሰራና የሀብት ቆጠራ ስራ በፍጥነት እንዲጀመር ጥረት እየተደረገ ይገኛል፣
- የቅየሳ ባለሙያዎች ቁጥር እንዲጨምር በማድረግ ችግሩን ለመፍታት ጥረት ተደርጓል፡፡

**ሎት-2፡-**

- የዲዛይን ማሻሻያ ሥራውን ለማጠናቀቅ የቅየሳ ባለሙያዎችን ቁጥር እንዲጨምር በማድረግ የዲዛይን ማሻሻያ ሥራው በፍጥነት እንዲጠናቀቅ ጥረት ተደርጓል፣
- የቅየሳ ሥራው እንዲቀጥል የቤንች ማርክ እንደ አዲስ እንዲቀመጥ ተደርጓል፣
- የውሰን ማስከበር ሰራና የሀብት ቆጠራ ስራ በፍጥነት እንዲጀመር ጥረት እየተደረገ ይገኛል፣
- የቅየሳ ባለሙያዎች ቁጥር እንዲጨምር በማድረግ ችግሩን ለመፍታት ጥረት ተደርጓል፡፡

**ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፡-**

- የመሬት ካሳ ቶሎ ተሰርቶ እንዲቀርብ ግፊት ማድረግ፣
- የወሰን ማስከበር ስራ ከሚሰራው ስራ እየቀደምን እንዲሰራ ጥረት ማድረግ፣
- ከተቋራጭ እና አማካሪ ድርጅቶች የሚቀርቡ ጥያቄዎች በፍጥነት ምላሽ እንዲያገኙ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል፣
- የዲዛይን ማሻሻያ ስራዎች በአማካሪ ድርጅቱ በኩል በፍጥነት እንዲጠናቀቅ ግፊት ማድረግ፡፡

**በፀጥታ ችግር ምክንያት በዕቅድ መሰረት ግንባታ ሥራዎች በበጀት አመቱ ያልተከናወኑ ፕሮጀክቶች፡-**

- የዛሬማ ሜይዴይ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት፣
- የካዛ መስኖ ልማት ፕሮጀክት፣
- አንገር የመስኖ ልማት ፕሮጀክት፣
- ኬጦ መስኖ ልማት ፕሮጀክት (በአከባቢው ላይ የተወሰነ የፀጥታ መሻሻል በመኖሩ ለተቋራጭ ድርጅቱ የግንባታ ቦታ ማስረከብ ተችሏል፡፡ እንዲሁም የዲዛይን ማሻሻያዎችን ለማከናወን እንዲረዳ የቅየሳ ሥራዎች በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡)

በዕቅድ ተይዞ የጨረታ ሂደት ባለመጠናቀቁ ሥራው ያልተጀመረ ፕሮጀክት፡-

1. የመገጭ መስኖ ልማት ፕሮጀክት (የእርሻ ውስጥ ግንባታ ሥራዎች)

## ሀ2. የመስኖ ጥናትና ዝርዝር ዲዛይን ፕሮጀክቶች

### 1. የሴጎ የመስኖ ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት

ይህ ፕሮጀክት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ከአርባ-ምንጭ ከተማ 24 ኪ.ሜ. ላይ የሚገኝ ሲሆን 5,000 ሄክታር መሬት ለማልማት ታሳቢ ተደርጎ የሚከናወን ነው፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግብ፡-** የፕሮጀክቱን ጥናትና ዲዛይን ቀሪ 26 በመቶ የሚሆነውን ሥራ በማከናወን በዓመቱ መጨረሻ 100% ማጠናቀቅ ነው፡፡

**የፕሮጀክቱ የ6 ወራት አፈጻጸም፡-**

ሴጎ የአዋጭነት ጥናትና ዝርዝር ዲዛይን ፕሮጀክትን በ6 ወራት 22 ከመቶ ለማከናወን ታቅዶ 20.0 ከመቶ ወይም የዕቅዱን 90.9 ከመቶ ተከናውኗል፡፡ በዚህም አጠቃላይ አፈጻጸሙ በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 74 ከመቶ ወደ 94 ከመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** በበጀት ዓመቱ 20.0 ሚሊዮን ብር ወጪ ለማድረግ የታቀደ ቢሆንም ወጪ የሆነ ገንዘብ የለም፡፡

### 2. የጊሎ መስኖ ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት

የጊሎ መስኖ ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት በጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሚገኝ ሲሆን 20,000 ሄክታር መሬት ለማልማት ታሳቢ ተደርጎ የሚከናወን ነው፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግብ፡-** የፕሮጀክቱን ጥናትና ዲዛይን ቀሪ 71 በመቶ የሚሆነውን ሥራ በማከናወን በዓመቱ መጨረሻ 100% ማጠናቀቅ ነው፡፡

**የ6 ወራት አፈጻጸም፡-**

ጊሎ የግድብና የአዋጭነት ጥናትና ዝርዝር ዲዛይን የመስኖ ልማት ፕሮጀክትን በግማሽ ዓመቱ ውስጥ 5 ከመቶ ለማከናወን ቢታቀድም ህብረተሰቡ ችግር በመፍጠሩ አልተከናወነም፡፡

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** በበጀት ዓመቱ 20.0 ሚሊዮን ብር ወጪ ለማድረግ የታቀደ ቢሆንም ወጪ የሆነ ገንዘብ የለም፡፡

**ያጋጠሙ ችግሮች፡** ህብረተሰቡ ፕሮጀክቱን ባለመቀበሉ ምክንያት ተቋርጧል፣

**የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች፡** ችግሩ ለክልሉ አመራሮች እንዲያውቁት ተደር[1]ል። በመሆኑም መፈታት ያለበት በክልሉ ይሆናል።

### 3. የአንገረብ መስኖ ልማት ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት

የአንገረብ መስኖ ልማት ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት የሚገኙ ሲሆን 50,000 ሄክታር መሬት ለማልማት ታሳቢ የያደረገ ፕሮጀክት ነው፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግብ፡-** የፕሮጀክቱን ጥናትና ዲዛይን በዓመቱ መጨረሻ 100% ማጠናቀቅ ነው፡፡

**የፕሮጀክቱ የ6 ወራት አፈጻጸም፡-** በ6 ወራት ፕሮጀክቱን 26 ከመቶ ለማከናወን ታቅዶ 10.0 ከመቶ ወይም የዕቅዱን 38.5 ከመቶ ማከናወን ተችሏል፡፡

***ያጋጠመ ችግር፡*** የድጋሚ ጨረታ ሂደት በዝግጅት ምዕራፍ ላይ መገኘቱ፣

**የተወሰደ የመፍትሔ እርምጃ፡** የድጋሚ ጨረታ ሂደት ዝግጅት ለማፋጠን ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

## 4. ሞርሞራ መስኖ ልማት ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት

ይህ ፕሮጀክት በደቡብ ህዝቦችና ብሄረሰቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት የሚገኝ ሲሆን 29,000 ሄክታር መሬት ለማልማት ታሳቢ ታሳቢ የያደረገ ፕሮጀክት ነው፡፡

ሲከናወን የነበረ ሲሆን በበጀት እጥረት ምክንያት በዝውውር ወደ መስኖ ልማት ኮሚሽን የመጣ ነው፡፧

**የበጀት ዓመቱ ግብ፡-** የፕሮጀክቱን ጥናትና ዲዛይን በዓመቱ መጨረሻ 100% ማጠናቀቅ ነው፡፡

**የፕሮጀክቱ የ6 ወራት አፈጻጸም፡-** በ6 ወራት ፕሮጀክቱን 26 ከመቶ ለማከናወን ታቅዶ 10.0 ከመቶ ወይም የዕቅዱን 38.5 ከመቶ ማከናወን ተችሏል፡፡

***ያጋጠመ ችግር፡*** የድጋሚ ጨረታ ሂደት በዝግጅት ምዕራፍ ላይ መገኘቱ፣

**የተወሰደ የመፍትሔ እርምጃ፡** የድጋሚ ጨረታ ሂደት ዝግጅት ለማፋጠን ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

## 5. ወይጦ መስኖ ልማት ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት

ይህ ፕሮጀክት በደቡብ ህዝቦችና ብሄረሰቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት የሚገኝ ሲሆን 29,000 ሄክታር መሬት ለማልማት ታሳቢ የያደረገ ፕሮጀክት ነው፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግብ፡-** የፕሮጀክቱን ጥናትና ዲዛይን በዓመቱ መጨረሻ 100% ማጠናቀቅ ነው፡፡

**የፕሮጀክቱ የ6 ወራት አፈጻጸም፡-** በ6 ወራት ፕሮጀክቱን 26 ከመቶ ለማከናወን ታቅዶ 10.0 ከመቶ ወይም የዕቅዱን 38.5 ከመቶ ማከናወን ተችሏል፡፡

***ያጋጠመ ችግር፡*** የድጋሚ ጨረታ ሂደት በዝግጅት ምዕራፍ ላይ መገኘቱ፣

**የተወሰደ የመፍትሔ እርምጃ፡** የድጋሚ ጨረታ ሂደት ዝግጅት ለማፋጠን ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

## 6. የቡልደሆ ግድብና መስኖ ልማት ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት

ይህ ፕሮጀክት በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት የሚገኝ ሲሆን 20,000 ሄክታር መሬት ለማልማት ታሳቢ ተደርጎ የሚከናወን ነው፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግብ፡-** የፕሮጀክቱን ጥናትና ዲዛይን በዓመቱ መጨረሻ 100% ማጠናቀቅ ነው፡፡

**የፕሮጀክቱ የ6 ወራት አፈጻጸም፡-** በ6 ወራት ፕሮጀክቱን 26 ከመቶ ለማከናወን ታቅዶ 15.0 ከመቶ ወይም የዕቅዱን 57.7 ከመቶ ማከናወን ተችሏል፡፡

**ያጋጠመ ችግር፡** በጨረታ ሂደት በዝግጅት ምዕራፍ ላይ መገኘቱ፣

**የተወሰደ የመፍትሔ እርምጃ፡** የጨረታ ሂደት ዝግጅትን ለማፋጠን ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

## 7. የታችኛው ገናሌ ግድብና መስኖ ልማት ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት

ይህ ፕሮጀክት በኦሮሚያና በሶማሊ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት የሚገኝ ሲሆን በድምሩ 55,000 ሄክታር ማለትም በሎት አንድ 15,000 ሄክታር በኦሮሚያ ክልል የሚተገበር ሲሆን በቀጥታ ግዥ ሂደት የውል ስምምነቱ ተፈጽሞ ሥራው ተጀምሯል፡፡ ሎት ሁለት 40,000 ሄክታር ሲሆን የውል ስምምነቱ ተፈጽሟል፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግብ፡-** የፕሮጀክቱን ጥናትና ዲዛይን በዓመቱ መጨረሻ ቀሪ 90% ማጠናቀቅ ነው፡፡

**የፕሮጀክቱ የ6 ወራት አፈጻጸም፡-** በ6 ወራት ፕሮጀክቱን 25 ከመቶ ለማከናወን ታቅዶ 25 ከመቶ ወይም የዕቅዱን 100 ከመቶ ማከናወን ተችሏል፡፡

## 8. የወይብ ግድብና መስኖ ልማት ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት

ይህ ፕሮጀክት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት የሚገኝ ሲሆን 13,653 መሬት ለማልማት ታሳቢ ተደርጎ የሚከናወን ነው፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግብ፡-** የፕሮጀክቱን ጥናትና ዲዛይን በዓመቱ መጨረሻ ቀሪ 90% ማጠናቀቅ ነው፡፡

**የፕሮጀክቱ የ6 ወራት አፈጻጸም፡-** በ6 ወራት ፕሮጀክቱን 45 ከመቶ ለማከናወን ታቅዶ 32 ከመቶ ወይም የዕቅዱን 71.1 ከመቶ ማከናወን ተችሏል፡፡

**ያጋጠመ ችግር፡** በጨረታ ሂደት በዝግጅት ምዕራፍ ላይ መገኘቱ፣

**የተወሰደ የመፍትሔ እርምጃ፡** የጨረታ ዝግጅት ሂደትን ለማፋጠን ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

## 9. ኤረር ግድብና መስኖ ልማት ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት

ይህ ፕሮጀክት በሀረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት የሚገኝ ሲሆን 13,653 መሬት ለማልማት ታሳቢ ተደርጎ የሚከናወን ነው፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግብ፡-** የፕሮጀክቱን ጥናትና ዲዛይን በዓመቱ መጨረሻ 100% ማጠናቀቅ ነው፡፡

**የፕሮጀክቱ የ6 ወራት አፈጻጸም፡-** በ6 ወራት ፕሮጀክቱን 22 ከመቶ ለማከናወን ታቅዶ 5 ከመቶ ወይም የዕቅዱን 18.5 ከመቶ ማከናወን ተችሏል፡፡

**ያጋጠመ ችግር፡** የጨረታ ሰነድ ለማዘጋጀት የሥራ ቢጋር በዝግጅት ሂደት ላይ መሆኑ፣

**የተወሰደ የመፍትሔ እርምጃ፡** የጨረታ ዝግጅት ሂደትን ለማፋጠን ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

## 10. ራሚስ ግድብና መስኖ ልማት ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት

ይህ ፕሮጀክት በሀረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት የሚገኝ ሲሆን 13,653 መሬት ለማልማት ታሳቢ ተደርጎ የሚከናወን ነው፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግብ፡-** የፕሮጀክቱን ጥናትና ዲዛይን በዓመቱ መጨረሻ 100% ማጠናቀቅ ነው፡፡

**የፕሮጀክቱ የ6 ወራት አፈጻጸም፡-** በ6 ወራት ፕሮጀክቱን 12 ከመቶ ለማከናወን ታቅዶ 10 ከመቶ ወይም የዕቅዱን 83.3 ከመቶ ማከናወን ተችሏል፡፡

**ያጋጠመ ችግር፡** የጨረታ ሰነድ ለማዘጋጀት የሥራ ቢ.ጋር በዝግጅት ሂደት ላይ መሆኑ፣

**የተወሰደ የመፍትሔ እርምጃ፡** የጨረታ ዝግጅት ሂደትን ለማፋጠን ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

## 11. ዋልጋ ግድብና መስኖ ልማት ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት

ይህ ፕሮጀክት በደቡብ ህዝቦችና ብሄረሰቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት የሚገኝ ሲሆን 13,653 መሬት ለማልማት ታሳቢ ተደርጎ የሚከናወን ነው፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግብ፡-** የፕሮጀክቱን ጥናትና ዲዛይን በዓመቱ መጨረሻ 100% ማጠናቀቅ ነው፡፡

**የፕሮጀክቱ የ6 ወራት አፈጻጸም፡-** በ6 ወራት ፕሮጀክቱን 29 ከመቶ ለማከናወን ታቅዶ 10 ከመቶ ወይም የዕቅዱን 34.5 ከመቶ ማከናወን ተችሏል፡፡

**ያጋጠመ ችግር፡** የጨረታ ሰነድ ለማዘጋጀት የሥራ ቢ.ጋር በዝግጅት ሂደት ላይ መሆኑ፣

**የተወሰደ የመፍትሔ እርምጃ፡** የጨረታ ዝግጅት ሂደትን ለማፋጠን ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

## 12. ጋሙና ግድብና መስኖ ልማት ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት

ይህ ፕሮጀክት በደቡብ ህዝቦችና ብሄረሰቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት የሚገኝ ሲሆን 13,653 መሬት ለማልማት ታሳቢ ተደርጎ የሚከናወን ነው፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግብ፡-** የፕሮጀክቱን ጥናትና ዲዛይን በዓመቱ መጨረሻ 100% ማጠናቀቅ ነው፡፡

**የፕሮጀክቱ የ6 ወራት አፈጻጸም፡-** በ6 ወራት ፕሮጀክቱን 29 ከመቶ ለማከናወን ታቅዶ 15 ከመቶ ወይም የዕቅዱን 51.7 ከመቶ ማከናወን ተችሏል፡፡

**ያጋጠመ ችግር፡** የጨረታ ሰነድ ለማዘጋጀት የሥራ ቢ.ጋር በዝግጅት ሂደት ላይ መሆኑ፣

**የተወሰደ የመፍትሔ እርምጃ፡** የጨረታ ዝግጅት ሂደትን ለማፋጠን ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

## 13. ጉደር ግድብና መስኖ ልማት ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት

ይህ ፕሮጀክት በደቡብ ህዝቦችና ብሄረሰቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት የሚገኝ ሲሆን 13,653 መሬት ለማልማት ታሳቢ ተደርጎ የሚከናወን ነው፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግብ፡-** የፕሮጀክቱን ጥናትና ዲዛይን በዓመቱ መጨረሻ 100% ማጠናቀቅ ነው፡፡

**የፕሮጀክቱ የ6 ወራት አፈጻጸም፡-** በ6 ወራት ፕሮጀክቱን 29 ከመቶ ለማከናወን ታቅዶ 15 ከመቶ ወይም የዕቅዱን 51.7 ከመቶ ማከናወን ተችሏል፡፡

**ያጋጠመ ችግር፡** የጨረታ ሰነድ ለማዘጋጀት የሥራ ቢ.ጋር በዝግጅት ሂደት ላይ መሆኑ፣

**የተወሰደ የመፍትሔ እርምጃ፡** የጨረታ ዝግጅት ሂደትን ለማፋጠን ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

## 14. ዜንቲ ግድብና መስኖ ልማት ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት

ይህ ፕሮጀክት በደቡብ ህዝቦችና ብሄረሰቦች ብሐራዊ ክልላዊ መንግሰት የሚገኝ ሲሆን 13,653 መሬት ለማልማት ታሳቢ ተደርጎ የሚከናወን ነው፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግብ፡-** የፕሮጀክቱን ጥናትና ዲዛይን በዓመቱ መጨረሻ 100% ማጠናቀቅ ነው፡፡

**የፕሮጀክቱ የ6 ወራት አፈጻጸም፡-** በ6 ወራት ፕሮጀክቱን 29 ከመቶ ለማከናወን ታቅዶ 15 ከመቶ ወይም የዕቅዱን 51.7 ከመቶ ማከናወን ተችሏል፡፡

**ያጋጠመ ችግር፡** የጨረታ ሰነድ ለማዘጋጀት የሥራ ቢ.ጋር በዝግጅት ሂደት ላይ መሆኑ፣

**የተወሰደ የመፍትሔ እርምጃ፡** የጨረታ ዝግጅት ሂደትን ለማፋጠን ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

## 15. አሱኖ ግድብና መስኖ ልማት ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት

ይህ ፕሮጀክት በደቡብ ህዝቦችና ብሄረሰቦች ብሐራዊ ክልላዊ መንግሰት የሚገኝ ሲሆን 13,653 መሬት ለማልማት ታሳቢ ተደርጎ የሚከናወን ነው፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግብ፡-** የፕሮጀክቱን ጥናትና ዲዛይን በዓመቱ መጨረሻ 100% ማጠናቀቅ ነው፡፡

**የፕሮጀክቱ የ6 ወራት አፈጻጸም፡-** በ6 ወራት ፕሮጀክቱን 29 ከመቶ ለማከናወን ታቅዶ 15 ከመቶ ወይም የዕቅዱን 51.7 ከመቶ ማከናወን ተችሏል፡፡

**ያጋጠመ ችግር፡** የጨረታ ሰነድ ለማዘጋጀት የሥራ ቢ.ጋር በዝግጅት ሂደት ላይ መሆኑ፣

**የተወሰደ የመፍትሔ እርምጃ፡** የጨረታ ዝግጅት ሂደትን ለማፋጠን ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

## 16. ሎካ አባያ ግድብና መስኖ ልማት ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት

ይህ ፕሮጀክት በሲዳማ ብሐራዊ ክልላዊ መንግሰት የሚገኝ ሲሆን 13,653 መሬት ለማልማት ታሳቢ ተደርጎ የሚከናወን ነው፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግብ፡-** የፕሮጀክቱን ጥናትና ዲዛይን በዓመቱ መጨረሻ 100% ማጠናቀቅ ነው፡፡

**የፕሮጀክቱ የ6 ወራት አፈጻጸም፡-** በ6 ወራት ፕሮጀክቱን 27 ከመቶ ለማከናወን ታቅዶ 15 ከመቶ ወይም የዕቅዱን 55.6 ከመቶ ማከናወን ተችሏል፡፡

**ያጋጠመ ችግር፡** የጨረታ ሰነድ ለማዘጋጀት የሥራ ቢ.ጋር በዝግጅት ሂደት ላይ መሆኑ፣

**የተወሰደ የመፍትሔ እርምጃ፡** የጨረታ ዝግጅት ሂደትን ለማፋጠን ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

## 17. አይማ ግድብና መስኖ ልማት ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት

ይህ ፕሮጀክት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት የሚገኝ ሲሆን 13,653 መሬት ለማልማት ታሳቢ ተደርጎ የሚከናወን ነው፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግብ፡-** የፕሮጀክቱን ጥናትና ዲዛይን በዓመቱ መጨረሻ 100% ማጠናቀቅ ነው፡፡

**የፕሮጀክቱ የ6 ወራት አፈጻጸም፡-** በ6 ወራት ፕሮጀክቱን 18 ከመቶ ለማከናወን ታቅዶ 5 ከመቶ ወይም የዕቅዱን 27.8 ከመቶ ማከናወን ተችሏል፡፡

**ያጋጠመ ችግር፡** የጨረታ ሰነድ ለማዘጋጀት የሥራ ቢጋር በዝግጅት ሂደት ላይ መሆኑ፣

**የተወሰደ የመፍትሔ እርምጃ፡** የጨረታ ዝግጅት ሂደትን ለማፋጠን ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

## 18. ደቡብ ጎዴ ግድብና መስኖ ልማት ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት

ይህ ፕሮጀክት በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት የሚገኝ ሲሆን 13,653 መሬት ለማልማት ታሳቢ ተደርጎ የሚከናወን ነው፡፡

**የበጀት ዓመቱ ግብ፡-** የፕሮጀክቱን ጥናትና ዲዛይን በዓመቱ መጨረሻ 100% ማጠናቀቅ ነው፡፡

**የፕሮጀክቱ የ6 ወራት አፈጻጸም፡-** በ6 ወራት ፕሮጀክቱን 18 ከመቶ ለማከናወን ታቅዶ 15 ከመቶ ወይም የዕቅዱን 83.3 ከመቶ ማከናወን ተችሏል፡፡

**ያጋጠመ ችግር፡** የጨረታ ሰነድ ለማዘጋጀት የሥራ ቢጋር በዝግጅት ሂደት ላይ መሆኑ፣

**የተወሰደ የመፍትሔ እርምጃ፡** የጨረታ ዝግጅት ሂደትን ለማፋጠን ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

## 19. የአድአ በቾ የከርሰምድር መስኖ ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክት

ይህ ፕሮጀክት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት የሚገኝ ሲሆን 5,000 ሄክታር መሬት ለማልማት ታሳቢ ተደርጎ የሚከናወን ነው፡፡

ፕሮጀክቱ በኮሪያ ባንክ የብድር ስምምነት የሚከናወን ሲሆን የጨረታ ሂደቱ የቴክኒክና የፋይናንስ ግምገማው ተከናውኖ የውለታ ስምምነት ከአማካሪው ድርጅት ጋር ተፈጽማል፡፡

**የፕሮጀክቱ የ6 ወራት አፈጻጸም፡-** በ6 ወራት ፕሮጀክቱን ከዕቅድ ውጪ 37 ከመቶ ማከናወን ተችሏል፡፡

**ማስታወሻ፡-** በአካባቢያቸው በነበረ የፀጥታ ችግር ምክንያት የተርካን፣ የሽንፋ፣ የታችኛዉ በለስና የሚሌ ግድብና ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክቶችን በግማሽ ዓመቱ ውስጥ ማከናወን ባለመቻሉ አፈጻጸማቸውን በሪፖርቱ ውስጥ ማካተት አልተቻለም፡፡

**ማስታወሻ፡-** በአካባቢያቸው ባለ የፀጥታ ችግሮች ምክንያት ስራዎች ባለመከናወናቸው በመስኖ ግንባታ ዘርፍ የዛሪማ፣ የአንገር እና የኬጦ አፈጻጸም እንዲሁም በመስኖ ጥናትና ዲዛይን ረገድ የተርካን፣ የታችኛው በለስ፣ የሽንፋና የሚሌ አፈጻጸም በሪፖርቱ ውስጥ አልተካተተም፡፡

## ለ. ንዑስ ፕሮግራም ሁለት፡ የመስኖ ቴክኖሎጂና አቅም ግንባታ ንዑስ ፕሮግራም

### መግቢያ

የመስኖ ውሃ አቅርቦት (Irrigation Water Supply) ለሃገሪቷ ከሚሰጠዉ አያሌ ጥቅምና አበርክቶ አንጻር ሲታይና ሲለካ እንዲሁም መልማት ከሚችለዉ የሃገሪቷ አቅም ጋር ሲወዳደር እጅግ በጣም ወደኋላ የቀረና ዝቅተኛ ነዉ፡፡ ይህ የመስኖ ዉሃ አቅርቦት (Irrigation Water Supply) ዘርፍ በሀገሪቷ ላይ የሚከሰተውን ተመላላሽ ድርቅ (Recurrent Drought) ተቋቁሞ በአለም ላይ የተጋረጠዉን የአየር ንብረት ለዉጥ ፈተና (Climate Change) በመመከት የሚጠበቅበትን ዘርፈ ብዙ አሰተዋጽዖና ግልጋሎት ለሐገሪቷ ማበርከት እንዲችልና በዉሱንና በአነስተኛ የግዜ፣ የጉልበትና የገንዘብ ወጪ ግብአት በመጠቀም የመስኖ ዉሃ የአቅርቦት (Irrigation Water Supply) ልማቱን አቅሙ የዳበረና በቴክኖሎጂ የታገዘ በማድረግ አገሪቷ ለወጠነችዉ ከፍ ያለ የምጣኔ ሃብት እድገት በፍጥነትና በጥራት ስኬታማና እዉን እንዲሆን ማድረጉ እጅግ አስፈላጊና ጠቃሚ እንደሚሆን እሙን ነዉ፡፡

በመሆኑም የመስኖ ውሃ አቅርቦት (Irrigation Water Supply) ልማትን በተሳለጠና ዉጤታማ በሆነ መንግድ ለማከናወን በዘርፉ ያሉትን ዋና ዋና የስራ ሂደቶችንና የአሰራር ስርአቶችን እንዲሁም ቁልፍ ተግባራትን (Coar Work Processes) ለይቶ ጊዜ ጉልበትና ወጪ ቆጣቢ (Time Cost and Labour Efficient and Effective) እንዲሆኑ አሰራሮችን ማዘመን፣ በቴክኖሎጂ መደገፍና አቅማቸዉን መገንባት እጅግ ጠቃሚና አስፈላጊ ነዉ፡፡ እንዲሁም የመስኖ ውሃ አቅርቦት (Irrigation Water Supply) የሚተገብሩ አካላትን ለይቶ በክህሎትና በእዉቀት የበቁ ማድረጉ እጅግ ጠቃሚና ጊዜ የማይሰጠዉ ነዉ፡፡ በመሆኑም ይህንን ጠቅላላ ሀሳብ ተግባራዊ ለማድረግ እንዲያስችልና አላማዉንና ዝርዝር ተግባራቱን ተንትኖ በማቅረብ ስኬታማ እንዲሆኑ ለማድረግ አስፈላጊዉን የገንዘብና የጊዜ ወጪዉን አካቶ ይህ የመስኖ ልማት የቴክኖሎጂና የአቅም ግንባታ ፕሮጀክት በትግበራ ላይ ይገኛል፡፡

### ሀ. የካፒታል ፕሮጀክት የ6 ወራት አፈጻጸም

በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት የፕሮጀክቱን 10 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ

የተከናወነው 0.8 በመቶ ነው፡፡ ለክንዉኑ ዝቅተኛ መሆን ምክንያቶች የበጀት ዘግይቶ መምጣት፣ የመንግስታዊ የመዋቅር ለዉጥ ሂደት እና የሰዉ ሐይል እጥረት ናቸው፡፡

**ለ. የመደበኛ ሥራዎች የ6 ወራት አፈጻጸም፡-**

- 4 የተሸሻሉ የመስኖ ቴክኖሎጂዎች ተመርጠዉ ቴክኖሎጂዎቹን ለማስተዋወቅና ወደ ትግበራ ለማስገባት ፕሮፖዛል ለበላይ አመራሩ ዉሳኔ እንዲሰጥበት ቀርቧል፡፡ (ቶፖግራፊ፣ ጂኦሎጂ፣ አፈርና ኢ-ፐሮክዩርመንት ዙሪያ እንዲሁም የመልሶ ሰፈራና የካሳ ቴክኖሎጂዎች)
- የ4 ነባር የመስኖ ፕሮጀክቶች የውሃ አጠቃቀም ውጤታማነት ጥናት ፕሮፖዛል ተዘጋጅቶ ወደ ጥናት እንዲገባ ጥረት ቢደረግም በስምሪት አሰራር ምክንያት መኪና ሳይገኝ ቀርቶ ስራዉን መስራት አልተቻለም፡፡ (ቆጋ፣ የላይኛዉ፣ መካከለኛዉና ታችኛዉ አዋሽ)
- የመስኖ ፕሮጀክቶች በቀነሰ ጊዜና በቀነሰ ገንዘብ ተጠናቀዉ ወደስራ እንዲገቡ ለማስቻል በዋና የስራ ሒደቶች ላይ የመደበኛ የአሰራር ስርአት ለመቅረጽ ኮሚቴ ተዋቅሮ እንዲሰራ ጥረት ቢደረግም በመዘግየቱ ለዚሁ ስራ እንዲሁም በዘርፉ ሙያና ልምድ ባላቸዉ ሰዎች የተቋሙን ተለዋጭ መዋቅር ለማሰራት እንዲያስችል አማካሪ ለመቅጠር የሚያስችል ቢጋር ተዘጋጅቶ ተጠናቋል፡፡
- የጥናትና የኢንጂነሪንግ ዲዛይን ማኑዋል የሚያዘጋጅ አማካሪ እንዲሁም የአምስት አመት የመስኖ ቴክኖሎጂ መረጣ ማኑዋል በማዘጋጀት የአምስት አመት የመስኖ ቴክኖሎጂዎች የሚመርጥ አማካሪ ለመቅጠር ቢጋር ዝግጅት ተጀምሯል፡፡
- ከጠቅላላው የመስኖ በጀት ፍላጎት የልማት አጋሮች ድርሻ ለመጨመር 3 የተዘጋጁ የድጋፍና ብድር መጠየቂያ ፕሮፖዛሎች ተዘጋጅተዉ አልቀዉ ገንዘብ ሚንስትርን ለመጠየቅ ዝግጅት ላይ ነን፡፡
- የተቋሙን የ 15 ዓመት ስትራቴጂ፣ ሮድ ማፕ/ማስተረ ፕላን ለማዘጋጀት የሚያስችል ቢጋር እየተዘጋጀ ይገኛል፡፡
- በፋሲሊቲ የተሟላና የተጠናከረ ተቋማዊ አሰራር ለመፍጠር የዉስጥ አሰራርን አዉቶሜት ለማድረግ ከ INSA ጋር የቅድመዝግጅት ስራ የመጨረስን ቢሆንም አሁን ላይ ከሌሎች ተቋማት ጋር ለመስራት ዘርፉ ላይ የተሰማሩትን ተቋማት እየለየን ነዉ፡፡
- በመስኖ ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሙያዎችና የመስኖ ተጠቃሚ ማህበራት ኮሚቴ አባላት የተገነባ አቅም ለመፍጠር 3 የስልጠና ፕሮፖዛሎች ተዘጋጅተዉ ለበላይ አመራሩ ለዉሳኔ ቀርበዋል፡፡
- ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር የተሳሰረ የመስኖ ልማት ለመፍጠር 4 መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ተለይተዉ ትስስር ለመፍጠር ወደስራ እየተገባ ነዉ፡፡

**የበጀት አጠቃቀም፡-** ለበጀት ዓመቱ ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ 10.0 ሚሊዮን ቢታቀድም ወጪ የሆነ ገንዘብ የለም፡፡ ለመደበኛ በጀት ደግሞ ለዓመቱ 3.0 ሚሊዮን ብር ታቅዶ 0.886 ሚሊዮን

ብር ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ ውሏል፡፡ በአጠቃላይ ለንዑስ ፕሮግራሙ ለበጀት ዓመቱ 13.0 ሚሊዮን ብር ታቅዶ መጠቀም የተቻለው 886,263 ብር ነው፡፡

**በአፈጻጸም ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች/ተግዳሮቶች**

- ለቴክኖሎጂ ልማትና ማስፋፋት እንዲሁም የአቅም ግንባታ ስራዎች ትኩረት አለመሰጠት
- ዉሳኔ ለመስጠት መዘግየት
- የሰዉ ሐይል እጥረት
- የተሽከርካሪ እጥረት
- የመኪና ስምሪት ችግር

**የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች**

- ለቴክኖሎጂ ልማትና ማስፋፋት እንዲሁም የአቅም ግንባታ ስራዎች ትኩረት መስጠት
- በቶሎ የሰዉ ሐይል ቅጥር መፈፀም
- ለዉጭ ሐገር የልምድ ልዉዉጥና አጭር ጊዜ ስልጠና የዉጭ ምንዛሪ LC መክፈት
- የመኪና ስምሪት ችግር እንዲቀርፉ በደብዳቤ ማሳወቅ

**ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች**

የተቋማዊና የዘርፉ አፈጻጸም ስር ነቀል ለዉጥ እንዲያመጣና ከተለመደዉ ልማዳዊ አሰራር ለማላቀቅ የሰዉ ሃይልንና የተቋማት አቅምን መገንባትና አሰራሮችን በቴክኖሎጂ መደገፍ በሁሉም የበላይ አመራሮችና በፌደራልና በክልል የመስኖ ልማት ተቋማት ደረጃ ቅድሚያ ተሰጥቶት ሊሰራበት የሚገባ ነዉ፡፡ አቅምን መገንባትና አሰራሮችን በቴክኖሎጂ ማዘመን ለተቋሙ ከፍ ያለ ሚና ያለዉና አሁን ያሉ የተቋሙ የስራ አፈጻጸሞችን እመርታዊ ለዉጥ እንዲያስገኙ (Transform እንዲያደርጉ) የሚረዳና ዋና ዋና ስራዎች የሚፈጁት ግዜና ገንዘብ ሙሉ ለሙሉ እንዲቀንሱና ከጥራት አኳያ ሲታይ በከፍተኛ ሁኔታ እንዲጨምሩ ሊረዳ የሚችል መሆኑን በሁሉም ፈፃሚና አስፈፃሚ ዘንድ ግንዛቤ መያዙ የሰዉ ኃይል ቅጥር

## መ. ንዑስ ፕሮግራም ሶስት፡ የአካባቢና ማህበረሰብ ጉዳይ ንዑስ ፕሮግራም

**መግቢያ**

የአካባቢና ማህበረሰብ ልማት ዳይሬክቶሬት የመስኖና ድሬኔጅ ልማቱን ለማሳደግ በሚደረገዉ ጥረት ከመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ ማህበራዊና አካባቢያዊ ተጽኖዎችን በመከላከል ወይም በመቀነስ ካልተቻለም በማካካስ እና በመቆጣጠር እንዲሁም የመስኖ ዉሀ ተጠቃሚ ማህበራትን በማቋቋምና በማደራጀት የአርሶ አደሩን የመስኖ ልማት ተጠቃሚነት

በማሳደግ የበኩሉን ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡ በዚህም ረገድ በ2014 በጀት ዓመት 6 ወራት የተከናወነ የስራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ቀጥሎ በተመለከተዉ ሁኔታ ቀርቧል፡፡

**ዓላማ፡-** የመስኖና ድሬኔጅ ልማቱን ለማሳደግ በሚደረገዉ ጥረት የሚከሰቱ ማህበራዊና አካባቢያዊ ተጽኖዎችን በመከላከል ወይም በመቀነስ ካልተቻለም በማካካስ እና በመቆጣጠር እንዲሁም የመስኖ ዉሀ ተጠቃሚ ማህበራትን በማቋቋምና በማደራጀት አርሶ አደሩን በመስኖ ልማት ተጠቃሚነት ማሳደግ፡፡

## የ2013 በጀት ዓመት ግቦች

- ለኮሚሽኑ፣ የክልል ባለሙያዎች እና የፕሮጀክት አካባቢ ማህብረሰብ ተወካዮች የተከናወነ 1000 የአቅም ግንባታ ስራ፣
- ፕሮጀክቶች ከሚገነቡበት ስፍራ ለሚነሱ 200 የልማት ተነሺዎች በወቅቱ የተከፈለ የካሳ ክፍያ፣ የመልሶ ማቋቋምና የወሰን ማስከበር የድጋፍ ስራ፣
- በተገነቡና በተጠናቀቁ የመስኖ ፕሮጀክቶች የተቋቋሙ 120 የመስኖ ዉሀ ተጠቃሚዎች ማህበራት እና የተደረጉ ድጋፎች፣
- በተገነቡና እየተገነቡ ባሉ 8 ፕሮጀክቶች የተካሄደ የአካባቢ እና ማህበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ እና የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎች፣
- 8 የአካባቢና ማህበረሰብ የጥናት ዶክመንቶችን ጥራት በመገምገም ፕሮጀክቶቹ በዚሁ ሰነድ መሰረት መተላለፋቸዉን ማረጋገጥ፣

## የመጀመሪያው 6 ወራት ዕቅድ አፈጻጸም

- የአካባቢና ማህበረሰብ የልማት ተጽዕኖዎችን አጠናን ዘዴዎችን እና የመስኖ ዉሃ ተጠቃሚ ማህበራትን እንዲሁም የካሳ አሰራርን በተመለከተ ለሚመለከታቸዉ ለኮሚሽኑ ባለሞያዎች እና ለክልል ባለሞያዎች እንዲሁም ለወረዳ የካሳ ገማች ኮሚቴዎች ስልጠና ለመስጠት በሚለዉ ለ515 ባለሞያዎች ታቅዶ ለ445 ሰዎች ተሰጥቷል፡፡ እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመትም ለ600 አካላት ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ530 (88.3%) ተከናዉኗል፡፡
- የመስኖ ልማት ከሚከናወንባቸዉ ፕሮጀክቶች አካባቢ የሚገኙ የማህበረሰብ አካላት በተገቢዉ መንገድ የካሳ ግምት እንዲተሰራላቸዉ ፣ ከወሰን ማስከበር ጋር ተያይዞ ያጋጥሙ ችግሮች እንዲፈቱ፣ አኗኗራቸዉ ከልማት ጋር የሚጣጣም እንዲሆን መደረጉን ማጥናትና የደረሱ አዎንታዊ እና አሉታዊ ተጽዕኖዎችን በመገምገም ለሚመለከተዉ ክፍል ሪፖርት ማድረግ የሚለዉ በዚህ ሩብ ዓመት ለ1578 ሰዎች ታቅዶ ለ1064 ግለሰቦች

ተከናዉኗል፡፡ እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመትም ለ1800 ክፍያ ለመክፈል ታቅዶ ለ1286 (71.4%) ተከናዉኗል፡፡

- በሩብ ዓመቱ 30 የመስኖ ዉሀ ማህበራትን ለማደራጀት ታስቦ ለስልጠናና ለግንዛቤ ማስጨበጫ የሚዉል ገንዘብ ማን የሚሸፍን አካል ባለመገኘቱና ክልሎች የሰጡት ትኩረት አናሳ በመሆኑ ሳይከናወን ቀርቷል፡፡
- በ3 ፕሮጀክቶች የመስኖ ልማት ስራዎች በአካባቢና ማህበረሰብ ላይ የሚያደርሱትን አዎንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖዎች ማጥናት፣ የተጠኑትን ሰነዶችና መሬት ላይ ያለዉን ትክክለኛ ሁኔታ በመለየት በልማት ፕሮጀክቶች በአካባቢ ላይ እየደረሱ ያሉ ተጽዕኖዎች ካሉ እንዲሻሻሉ ድጋፍ ማድረግ በሚለዉ በ3 ፕሮጀክቶች 100% ተከናዉኗል፡፡ እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመትም በ5 ፕሮጀክቶች ለማጥናት ታቅዶ ለ5 (100%) ተከናዉኗል፡፡
- በአማካሪ ተዘጋጅተዉ የሚቀርቡን የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች የአካባቢ ተፀዕኖና የማህበረሰብ ልማት 4 የጥናት ሰነዶች ብቃትና ጥራትን ለመገምገም እና ለማስተካከል ለአካባቢ እና አየር ንብረት ለዉጥ ዳይሬክቶሬት እና ለሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት ሪፖርት ማድረግ፣ በሚለዉ 3 ተከናዉኗል፡፡ እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመትም 6 የጥናት ሰነዶችን ለማየትና ለማስተካከል ታቅዶ 5 (88.3%) ተከናዉኗል፡፡
- በሩብ ዓመቱ 2 ፕሮጀክቶች በአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ሰነድ መሰረት መገንባታቸዉ ለማረጋገጥ ታቅዶ በ2ቱመተ ተከናዉኗል፡፡ እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመትም በ4 ፕሮጀክቶች ግምገማ ለማድረግ ታቅዶ በ4ቱም (100%/)ተከናዉኗል፡፡
- በየፕሮጀክቶቹ በካሳ ቴክኒክ ኮሚቴ ተሰርተዉ ለሚቀርቡ 15 የካሳ ሰነዶች በሚገባ በማረጋገጥ ክፍያ እንዲፈጸም ከማድረግ አኳያ የ14 ተከናዉኗል፡፡ እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመትም 18 የካሳ ሰነዶችን ለማረጋገጥ ታቅዶ የ17 (94.4%) ተከናዉኗል፡፡

በ6 ወራት ታቅዶ ያልተከናወነ ተግባር፡- 30 የመስኖ ዉሀ ተጠቃሚ ማህበራትን ማቋቋምና ማደራጀት ያልተሳካ ዕቅድ ነዉ፡፡

**አጠቃላይ የስራ ሂደት አፈጻጸም፡-** የአካባቢና ማህበረሰብ ልማት ዳይሬክቶሬት የ6 ወራት አፈጻጸም 75% ነው፡፡

### ***ያጋጠሙ ችግሮች***

- የመስክ ትራንስፖርት (የመኪና እጥረት) ወይም አለመገኘት፣
- የባለሞያ ቁጥር ማነስ፣
- በወረዳዎች የካሳ ክፍያ ጥራቱን ጠብቆ ቶሎ ተሰርቶ አለመምጣት፣
- የካሳ ክፍያ ሂደት መጓተት፣ በገንዘብ ሚኒስቴር የገንዘብ ዝዉዉር መጓተት፣

**የተወሰደ የመፍትሄ እርምጃ**

- በኪራይ በተገኘዉ ትራንስፖርት፣ ከሌሎች ዳይሬክቶሬቶች ባለሞያ ጋር፣ ስራን ለመከታተል ምቹ ባይሆንም በመቀኛጀት መስራት፣
- ከወረዳ አስተዳዳሪዎች፣ ከካሳ ገማች ኮሚቴ ከአማካሪና ተቋራጮች ጋር የጋራ ዉይይት በማድረግ በቀጣይ ችግሮቹ እንዳይደገሙ ባለቤት የመስጠት እና ክትትል የማጠናከር ስራ እየተሰራ ነዉ፡፡
- በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል ያለዉ ሁኔታ ከሀገር ተጨባጭ ሁኔታም ጋር ስለሚያያዝ በጊዜ ሂደት የሚፈታ ሆኖ በበላይ ሀላፊዎች ጭምር በሚደረግ ጥረት የሚፈታ ይሆናል፡፡

**ለወደፊት መፍትሄ የሚሹ ጉዳዮች**

- በሚመለከተዉ የስራ ክፍል በኩል የመኪኖችን የመስክ ተሽከርካሪዎች ተሟልተዉ/ ተገዝተዉ ከዳይሬክቶሬቱ ወደ ፕሮጀክቶች ለሚሰማሩ ባለሞያዎች ተገቢዉ መጠንና ስምሪት በመስጠት ለስራ ማዘጋጀት፣
- በ2014 3ኛ ሩብ ዓመት ዳይሬክቶሬቱ ስራዉን የበለጠ ለማከናወንና ዕቅዱን ሙሉ ለሙሉ ለማሳካታ በወረዳ ተሰርቶ የሚመጣዉ የካሳ ክፍያ ትኩረት እንዲሰጠዉ እንዲሁም የመስኖ ዉሀ ተጠቃሚ ማህበራትን ለማቋቋመወ የበለጠ መስራት ፡፡
- ከአሁኑ በተሻለ ባለሞያዎችን በሚሟላት በሁሉም ፕሮጀክቶች የአካባቢና ማህበረሰብ ባለሞያ መድቦ ክትትል ማድረግ

## ፕሮግራም 3፡ የመስኖ መሠረተ ልማት አስተዳደር ፕሮግራም

**መግቢያ**

የመስኖ መሰረተ ልማት አስተዳደር ዳሬክቶሬት ታሳቢ ተደርጎ መደራጀት ያስፈለገበት ዋናው ዓላማ መንግስት ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ ያፈሰሰባቸው ትላልቅና መካከለኛ የመስኖ ግድቦችና የመሰረተ ልማት አዉታሮች በጥናት ወቅት የተቀመጠላቸውን የአገልግሎት ዘመን ሳይደርስ ለብልሽት ስለሚጋለጡ በተቀናጀ መልክ ማስተዳደርና አስፈላጊውን ጥገና በወቅቱ ማድረግ በማስፈለጉ ነው፡፡

*የፕሮግራሙ የ2014 በጀት ዓመት ውጤቶችና ግቦች*

በፕሮግራሙ በ2014 በጀት ዓመት የሚከናወኑት የ2 የመስኖ ጥገና ፕሮጀክቶችና በመደበኛ ሥራዎች በተለያዩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚካሄዱት የመስኖ መሠረተ ልማት አስተዳደር ሥራዎች ናቸው፡፡

**የመስኖ መሰረተ-ልማት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የ2014 በጀት ዓመት ግቦች**

- ጥገና የተደረገላቸው የመስኖ መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች በቁጥር 2፣

- የውሃ አጠቃቀማቸው ከ30% ወደ 70% የደጉና ውጤታማ የሆኑ የመስኖ ፕሮጀክቶች በቁጥር 4፣
- ጥገና ተደርጎላቸው በሙሉ አቅማቸው እንዲሰሩ የተደረጉ ፕሮጀክቶች በቁጥር 4፣
- በመስኖ ውሀ ተጠቃሚዎች ማህበራት የተሸፈነ የመስኖ መሰረተ ልማት የጥገና ወጭ(አሁን ካለበት 0% ወደ 5%) 5 በመቶ፣
- በ2 የመስኖ አስተዳደር ማዕከላት ስር በሚገኙ 9 የመስኖ ልማት ንዑስ ማዕከላት የተዘረጋ ፍትሃዊ የመስኖ ውሃ ስርጭት ስርዐት 100 በመቶ፣
- በመስኖ ሥራ አቅማቸው በስልጠና ያደገ ባለሙያዎች በቁጥር 150፣
- በመስኖ ሥራ አቅማቸው በስልጠና ያደገ የመስኖ ተጠቃሚ ማህበራት በቁጥር 150፣

**የበጀት ዓመቱ የ6 ወራት አፈጻጸም**

**ሀ. የካፒታል ፕሮጀክቶች አፈጻጸም**

- የጎዴ መስኖ ልማት ጥገና ፕሮጀክት ስራ በሁለተኛው ሩብ ዓመት የፊዚካል ስራ ዕቅድ 5 በመቶ ለመስራት ታቅዶ ስራው አልተከናወነም፡፡
- የራያ ቆቦ መስኖ ልማት ጥገና ፕሮጀክት ስራ በ6 ወራት ውስጥ ዕቅድ ስለሌው የተከናወነ ስራ የለም፡፡

**ለ. የመደበኛ ሥራዎች** አፈጻጸም

- የመስኖ ልማት በሚከናወንባቸው የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ፍትሃዊ የመስኖ ውሃ ስርጭት 50% ለማከናወን ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት 100% ተከናውኗል፡፡
- በበጀት ዓመቱ የመስኖ መሰረተ ልማት ማዕከላትና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የስራ እንቅስቃሴያቸውን የክትትልና የግምገማ ስራ 50% ለማከናወን ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት 100% ተከናውኗል፡፡
- በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ስር የሚገኙ የመስኖ ውሃ ማሰራጫ ዋና ቦይዎች፣ የድሬይኔጅ ውሃ ማስወገጃ ቦዮችና የውሃ ውቅሮች (structure) የጥገና ስራዎች ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በ3ኛ ሩብ ዓመት ለማከናወን የተያዘ ቢሆንም በ2ኛ ሩብ ዓመት 15% ተከናውኗል፡፡
- የመደበኛ ስራዎች የ6 ወራት አፈጻጸም 100% ነው፡፡

**የበጀት አጠቃቀም፡-**

- ካፒታል ፕሮጀክቶች፡- ለበጀት ዓመቱ 6 ወራት ለጎዴ መስኖ ልማት ጥገና ፕሮጀክት 206 ሚሊዮን ብር ቢታቀድም ወጪ የሆነ ገንዘብ የለም፡፡ በሌላ በኩል ለራያ ቆቦ መስኖ ልማት ጥገና ፕሮጀክት 6 ሚሊዮን ብር ታቅዶ 5.95 ሚሊዮን ብር ወጪ ሆኗል፡፡
- መደበኛ በጀት አጠቃቀም፡ በ6 ወራት 1.66 ሚሊዮን ብር ወጪ ሆኖ ስራ ላይ ውሏል፡፡

**በስራ ላይ ያጋጠሙ ችግሮች**

- የማዕከላትና ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሰራተኞች በሙሉ አቅማቸው ለማሰራት የቢሮ፣ የሰርቪስ መኪና እና የቢሮ መገልገያ ዕቃዎች ያለመሟላት፣
- ቢሮዎች በአስቸኳይ ባለመሰጠታቸው የቢሮ ጥገና ማድረግ ያለመቻል፣
- ካሽ ፍሎው በተፈለገው ጊዜና ልክ ያለመገኘት፣
- ለቆጋ የባንክ ሂሳብ ደብተር ለማስከፈት ረዥም ጊዜ መውሰድ፣
- የጎዴ መስኖ ጥገና ፕሮጀክት ተቋራጭ ድርጅት ቶሎ ወደ መስክ ያለመግባት
- የጎዴ የግንባታ ቁጥጥር ለማከናወን የአማካሪ ቅጥር መዘግየት፣

**የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች**

- የተፋሰስ ልማት ባለስልጣን የቢሮ፣ የሰርቪስ መኪና እና የቢሮ መገልገያ ዕቃዎች እንዲያስረክብ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በደብዳቤ የተጠየቀ ሲሆን ከተፋሰስ ልማት ባለስልጣን ኃላፊዎች ጋር በመስክ በመዘዋወር ያሉትን ንብረቶችና ቢሮዎች እንዲያካፍሉ ካልሆነም ሰራተኞቹን ወደ እራሱ እንዲመልስ ሪፖርት ለሚ/ሩ መ/ቤት ጥያቄ ቀርቧል፡፡
- የጎዴ አማካሪ ቅጥር እንዲፋጠን ከግዥና ኮንትራት አስተዳደር ዳይሬክተር ጋር ውይይት ተደርጓል፡፡
- የጎዴ ተቋራጭ ድርጅት የቅድሚያ ክፍያ ሂደት እንዲጠናቀቅ ተደርጓል፡፡
- የቆጋ የባንክ ሂሳብ ደብተር እንዲከፈት ተደርጓል፡፡

**ትኩረት የሚሹ ጉዳዬች፡-** ከማዕከላትና የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ሰራተኞችና ከውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር ጋር በመነጋገር የሃብት ክፍፍል ጉዳይ በአስቸኳይ መፍትሄ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

## የተማሩ ወጣቶች መስኖ ልማት ፕሮግራም

**መግቢያ**

በአገራችን ከጊዜ ወደ ጊዜ ከዩኒቨርሲቲዎች ተመርቀው ሥራ አጥ የሆኑ ወጣቶች ቁጥር እያደገ ይገኛል፡፡ ይህን ችግር ለመቅረፍ መንግስት የሚቻለውን ሁሉ ጥረት በማድረግ ላይ ቢሆንም የችግሩ መጠን ከፍተኛ በመሆኑ ምክንያት የመስኖ ልማት ኮሚሽን የበኩሉን ለመወጣት እንዲያስችለው እነዚህኑ የተማሩ ወጣቶች በኮሜርሻል መስኖ ልማት በማሰማራት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ

በበጀት ዓመቱ ዕቅድ ይዞ እንቅስቃሴ በማደረግ ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ለተደራጁ ምሩቃን ወጣቶች የመስኖ መሬት እና ቴክኖሎጂ በማቅረብ በተቀናጀ የመስኖ ልማት ፕሮግራም ላይ ተሳታፊ በማድረግ፣ ምልመላና ስልጠና በመስጠት፣ ግብዓት በማቅረብና ገበያ ተኮር የመስኖ ሥራ በመስራት ቀደም ሲል የመስኖ አውታር ከተዘረጋላቸው የመስኖ መሬቶችና ወደፊት ከሚገነቡ ውሃ ገብ የመስኖ መሬቶች ለተማሩ ወጣቶች እንዲያዝ ለማድረግ እየተሰራ ይገኛል፡፡

## በመጀመሪያው 6 ወራት የተከናወኑ ዝርዝር ተግባራት

### 1. በአማራ ክልል ጣና በለስ ፕሮጀክት

- በአማራ ብሄራዊ ክ/መንግስት ከጃዊ ስኳር ልማት ፕሮጀክት ዉስጥ 3240 ሄክታር መሬት ለወጣቶች መስኖ ልማት እንዲዉል የተወሰነ ቢሆንም እስካሁን ድረስ ከስኳር ኮርፖሬሽን በተገኘ 740 ሄ/ር መሬት ላይ የመሰረተ ልማት ጥገና ስራ ተሰርቷል፡፡

**የመሰረተ ልማት ዝግጅትን በተመለከተ**

በጣና በለስ የወጣቶች መስኖ ፕሮግራም የሚከናወኑት ግንባታዎች የወጣቶች ግዜያዊ ማረፊያ ካምፕ ግንባታ እና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ጥልቅ ጉድጓዶችን የማልማት ስራዎች ናቸው፡፡

የወጣቶች ግዜያዊ መጠለያ ካምፕ እና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ግንባታን በተመለከተ ቀደም ብሎ በተሰጠ ውል መሰረት ኮንትራክተሩ የአማራ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ ሲሆን አማካሪው የአማራ ዲዛይን እና ቁጥጥር ኢንተርፕራይዝ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህ መሰረት ሁለቱን ግንባታዎች ለማከናወን ቫትን ጨምሮ ለኮንትራክተር ብር 87,316,975.64 እንዲሁም ለአማካሪ 11,600,000.00 ሚሊዮን ብር ውል ተይዞ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡

**የካምፕ ግንባታ ስራ አፈጻጸም፡** በ2014 በጀት ዓመት እቅድ መሰረት ለ798 ወጣቶች መጠለያ የሚሆኑ 12 ብሎክ የካምፕ ግንባታ ስራን ማስጀመር በእቅድ የተያዘ ተግባር ሲሆን በ6 ወር ውስጥ 20% ለመስራት ታቅዶ 29.89% በመቶ ለማከናወን ተችሏል፡፡

### የመጠጥ ውሃ አቅርቦት አፈጻጸም

- በፕሮጀክት ሳይቱ 3 ባለ 200 ሜትር ጥልቅ የመጠጥ ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ስራን በማጠናቀቅ ለወጣቶች የመጠጥ ውሃ ተደራሽ ማድረግ በእቅድ የተያዘ ተግባር ሲሆን አፈጻጸሙ 76% የደረሰ ሲሆን Water Supply System አፈጻጸም ዝቅተኛ ነው፡፡ በመሆኑም በ6 ወር ውስጥ በአጠቃላይ የመጠጥ ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ የፊዚካል ስራ አፈጻጸሙ 28.14% ማድረስ ተችሏል፡፡

### የተፈጠረ የስራ እድል እና በተግባር ወደ ስራ የገቡ ወጣቶች አፈጻጸም

- ለወጣቶች አስፈላጊውን ድጋፍ እና ክትትል በማድረግ በክልሉ ስልጠና የውሰዱ 798 ወጣቶችን ወደ ስራ እንዲገቡ ማስቻል በእቅድ የተያዘ ተግባር ሲሆን በክረምቱ ወቅት ከተለየው መሬት 180 ሄ/ር መሬት በአኩሪ አተር በማልማት እነዚሁ ወጣቶቹ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

## 2. የጊዳቦ የወጣቶች መስኖ ልማት ፕሮጀክት

በኦሮሚያ ክልል የሚተገበረው የወጣች መስኖ ልማት ፕሮጀክት በጊዳቦ ግድብ በስተግራ በኩል እየተገነባ ባለው 12.19 ኪ.ሜ ርዝመት ባለው ዋና ካናል ከሚለማው 8000 ሄ/ር የመስኖ መሬት ውስጥ 5000 ሄ/ር ላይ በወጣቶች እንዲሁም የተቀረው 3000 ሄ/ር መሬት በማህበረሰቡ እንደሚለማ ታስቦ በግንባታ ሂደት ላይ ያለ ፕሮጀክት ነው፡

**መሬት ዝግጅትን በተመለከተ፡** ለወጣቶች እንዲለማ ከተወሰነው 5000 ሄ/ር ውስጥ እስካሁን ከ3ኛ ወገን ነጻ የሆነ 1050 ሄ/ር መሬት ዝግጁ ሆኗል፡፡ ይሁንና በመጀመሪያ ዙር በወጣች የሚለማ እና ለስራ ዝግጁ የሆነ 700 **ሄ/ር** መሬት ሲሆን ለተሳታፊዎች ማረፊያ የሚሆን ካምፕ እና መጠጥ ውሃ አቅርቦትም ስራ በመጠናቀቅ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡

### የመሰረተ ልማት ዝግጅትን በተመለከተ

የግድቡ የእናት ስራ እና የዋና ቦይ ግንባታ ስራዎች በሚኒስቴሩ ግንባተ ክትትል ስር እየተከናወኑ ክትትል እና ቁጥጥር የሚደረግላቸው ሲሆን አፈጻጸማቸው (የዋናው ቦይ) የካናል አርማታ ሙሌት ስራ ከአጠቃላይ 12.21 ኪ.ሜ ውስጥ 8.6 **ኪ.ሜትሩ** ሙሉ ለሙሉ የተጠናቀቀ ሲሆን ቀሪው 3.61 ኪ.ሜ በስራ ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ለወጣቶች የተለየውን 700 ሄ/ር መሬት ሊያለማ የሚችለው የዋና ካናል ግንባታ ሙሉ ለሙሉ የተገነባ በመሆኑ ወጣቶቹ ስራ መጀመር ያስችላቸዋል

### የካምፕ ግንባታ ስራ አፈጻጸም

- በኮንትራት የተያዘው 12 ብሎክ የመጠለያ ካምፕ ግንባታ ሲሆን አንዱ ብሎክ 30.5 ሜ x 8.7 ሜ. ስፋት ያለው እና እያንዳንዳቸው 4.5 ሜ. x 3.65 ሜ.ስፋት ያለቸው 12 የመኖሪያ ክፍሎች (Room) ያሉት ነው፡፡ በተጨማሪም Kitchen, Dining room, Toilet አገልግሎት የሚሰጡ ተጨማሪ ግንባታዎችን ያካተተ ነው፡፡ በዚህ መሰረት አጠቃላይ የካምፕ ግንባታ ስራው 86.63% ተጠናቋል
- በተጓዳኝ የማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ግንባታ (ት/ቤት፣ ጤና ኬላ ወዘተ…) ስራዎች ሙሉ ለሙሉ የተጠናቀቁ እና ርክክብ የተፈጸመላቸው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

### የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ስራ አፈጻጸም

- በኮንትራቱ መሰረት ለፕሮጀክቱ 3 ጥልቅ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት የሚሰጡ ጉድጓዶችን ቆፍሮ

አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ነው፡፡ በዚህ መሰረት፡- የ3 ጉድጓዶች ቁፋሮ የተጀመረ ሲሆን የመጀመሪያ የባለ 200 ሜትር ጥልቅ ጉድጓድ *Drilling construction፣ pumping test* እና ተያያዥ የሲቪል ስራዎች ስራ ሙሉ ለሙሉ ተጠናቋል፡፡ አጠቃላይ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ፊዚካል ስራው 75% ተጠናቋል

***የተፈጠረ የስራ እድል እና ተሳታፊ ወጣቶች ሁኔታ፡-*** ቀደም ሲል ስልጠና ከወሰዱ ወጣች መካከል 492 የሚሆኑት የተሟላ መረጃ ያላቸው እና የመደራጀት ሂደት ጨርሰው እና የባንክ አካውንት ከፍተው (ብር 1.5 ሚሊዮን) በሲንቄ ባንክ ቁጠባ መጀመር ችለዋል፡፡

## 3. በአፋር ክልል የተንዳሆ ሳይት

### የመሬት መሰረተ ልማት ዝግጅት አፈጻጸም

- በአፋር የተንዳሆ የወጣቶች መስኖ ፕሮጀክት በዱፑቲ ወረዳ የሚገኝ ሲሆን ለፕሮግራሙ ማስተግበሪያነት የሚውለው 6000 ሄ/ር መሬት በከፍተኛ ሁኔታ በጥቅጥቅ ቁጥቋጦ የተወረረ በመሆኑ ምንጣሮ ስራ እና የካናል ጥገና ስራ እንዲካሄድ ከኢትዮጵያ ውሃ ስራዎች ኮርፖሬሽን ጋር የ269,961,512.5 ብር ኮንትራት ተይዞ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡
- አፈጻጸሙን በተመለከተም በ PC-1: 717 .3 **ሄ/ር፣** PC-2: **3,622.95** ሄ/ር እና **PC-3: 451.68 ሄ/ር** በአጠቃላይ **4791.93 ሄ/ር** መሬት ላይ የሚገኝ ቁጥቋጦ ተመንጥሯል፡፡

### የካናል ጥገና አፈጻጸም

- በ6 ወር ውስጥ ምንጣሮ ከተካሄደለት መሬት ውስጥ 3,952.85 ሄ/ር የሚያለማ  የካናል ጥገና እና ተያያዥ ግንባታዎችን ጠግኖ ማዘጋጀት ሌላኛው ተግባር ሲሆን በተደረገ የኮንትራት ማራዘሚያ የዋጋ ማስተካከያ ሳይደረግ አሁን ባለው ኮንትራት ውስጥ ባለው በጀት ብቻ ቀሪ ስራዎች እንዲከናወኑ በተወሰነው መሰረት 420 **ሄ/ር** ሊያለማ የሚችል ካናል ጠገነ ተሰርቶ የተጠናቀቀ ሲሆን ይህንኑ መሬት ባለሀቶች እያለሙትም ይገኛል፡፡
- እስካሁን ድረስ ያለው የስራ አፈጻጸምን በተመለከተም አጠቃላይ የፊዚካል ስራው አፈጻጸም 64.5% እንዲሁም የፋይናንሻል ስራ አፈጻጸም 62.3% ደርሷል፡፡
- ወጣቶችን ወደ ስራ ማስገባት እና ተጨማሪ ወጣቶችን መልምሎ እና አሰልጥኖ የተዘጋጀውን መሬት እንዲያለሙ ማድረግ ስራ በቀጣይ የተያዘ ዋና ተግባር ሲሆን መሬቱ ግን ጥቅም ሳይሰጥ ጠሙን ከሚያድር በሚል መግባባት በግዜያዊነት በክልሉ በሚገኙ አልሚዎች 746.5 የሚሆን ሄክታር ወደ በስንዴ ሰብል ተሸፍኖ ወደ ልማት ገብቷል፡፡

### የሶማሌ ክልል የወጣቶች መስኖ ፕሮጀክት ክንውን

- በሁለተኛው ሩብ ዐመት ላይ በተደረገ የእቅድ ክለሳ መሰረት ቀደም ሲል በሶማሊ ክልል የወጣቶች መስኖ ፕሮጀክት ተብለው የተያዙትን የሺንሌ እና ምእራብ ጎዴ ፕሮጀክቶች

በመደበኛው የፕሮጀክት ማእቀፍ እንዲያዙና በመስኖ መሰረተ ልማትት ግንባታ ክትትል ዳይሬክቶሬት ስር ክትትል እንዲደረግባቸው አስተላለፈናል፡፡

- በመሆኑም በክልሉ ወጠቶች መስኖ ፕሮጀከት ስር ክትትል የሚደረግለት የፋፈን ፕሮጀክት ሲሆን በ6 ወር ውስጥ 100 ሄ/ር የመሬት ዝግጀት እና ይህንኑ መሬት ሊያለማ የሚችል የጉድጓድ ውሃ ተጨማሪ የdesign ማስተካከያዎች, water supply electromechanical works ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡

## የመሬት ዝግጅተን በተመለከተ

- በጉርሱም ወረዳ በፋፈን ዞን ለሚተገበረው የወጣቶች መስኖ ፕሮጀክት 100 ሄ/ር የመስኖ መሬት የምንጣሮ ስራ እንዲሰሁም የ5 ጥልቅ ጉድጓዶች ቁፋሮ የተከናወነ ሲሆን የፓምፕ ግዢ ጣያቄዎችን ለሚመለከተው አካል አሳውቀናለል፡፡
- በተጨማሪም ከላይ ለተጠቀሱት ለአምስት የውሃ ጉድጓዶች የሚሆን የኤሌክትሪክ ክፍያ 7,942,026.15 እንዲፈጸም ተደርጓል፡፡
- በተጨማሪም በፋፈን ሳይት የ1000 ሄር መሬት ዝግጅት፣ የካምፕግንባታ እና የመጠጥ ውሃ ጉድጓድ ቢጋር (ToR) ተዘጋጅቶ በኮንትራት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በሂደት ላይ ይገኛል፡፡

## 4. የሲዳማ ጊዳቦ መስኖ ልማት ፕሮጀክት

የጊዳቦ መስኖ ፕሮጀክት በሲዳማ ክልል በኩልም ከሚያለማው 5000 ሄ/ር መሬት ውስጥ 3000 ሄ/ር መሬት በወታቶች የሚለማ እንደሆነ ይታወቃል፡፡

በዚህም መሰረትበ6 ወር ውስጥ ለወጣቶች የሚሆኑ 12 ብሎክ የካምፕ ግንባታ ስራን እና 2 ጥልቅ የመጠጥ ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ስራን ውለታ መዋዋል በእቅድ የተያዘ ሲሆን ክልሉ ለይቶ ያቀረበውን 2880 ሄ/ር መሬት መሰረት በማድርግ መሬቱን በተባጭ በማጥናት የሚያስፈልጉ የመስኖ መሰረተ ልማቶች፣ አግሮኖሚ እና መሰል ጥናቶችን የማስጠናት እንዲሁም ለካምፕ እና የመጠጥ ውሃ ሳይት ሎኬሽን የመለየት ስራዎች ተከናውዋል፡፡

## 5. የጋምቤላ የወጣቶች መስኖ ፕሮጀክት

በጋመምቤላ ክልል ቀደም ሲል የወጣቶች መስኖ ፕሮጀክት ያልተያዘ በመሆኑ ክልሉ ባቀረበው ጥያቄ መሰረት የወጣቶች መስኖ ፕሮጀክት ማስጀመር በ2014 እቅድ ተይዟል፡፡ በዚህ መሰረት በ6ወር ውስጥ ክልሉ ለፕሮግራሙ ስተግበሪያነት የሚውል መሬት እና ተያያዝ ጉዳዮችን ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ንዲያሳውቅ በደብዳቤ የተጠየቀ ሲሆን ምላሽ በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን፡፡

## 6. የጌደብ የወጣቶች መስኖ ልማት ፕሮጀክት

በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ከጣና በለስ ፕሮጀክት በተጨማሪ በወጣቶች መስኖ የሚለማ መሬት በምስራቅ ጎጃም ጌደብ የመስኖ ዊር ላይ እንዲተገበር መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡ በዚህ መሰረት በ6ወር ውስጥ፡-

- ከክልሉ አመራሮች እና ባለድርሻ አካላት ጋር ውይቶችን የማካሄድ ስራ
- እንዲሁም በሳይቱ በወጣቶች ሊለማ የሚችል ተጨባጭ አሃዛዊ መረጃ፣ ተያያዥ መረጃዎችን የማሰባሰብ ስራዎች በመሰራት ላይ ይገኛሉ

### ያጋጠሙ ችግሮች እና የተሰጡ መፍትሄዎች

### በጣና በለስ ያጋጠሙ ችግሮች

- በፕሮጀክቱ አፈጻጸም ላይ በዋናነት በግዜ ሰሌዳ አለመመራት ጋር የተያያዙ መዘግየቶች መኖራቸው
- ኮንትራክተሩ በወቅቱ master schedule አለማስገባቱን ተከትሎ የክትትል እና የቁጥጥር ስራው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ መፍጠሩ ፡፡
- ኮንትራክተሩ በሙሉ አቅሙ አለመግባት እና በሚፈለገው ግዜ ስራውን ሰርቶ ያለማጠናቀቅ፤
- የመኖሪያ ካምፕ ግንባታ ጋር በተያያዘ በወቅቱ ዲዛይን ተሰርቶ ወደ ስራ አለመገባቱ በፕሮግራሙ ትግበራ ላይ መዘግየትን የፈጠረ ሲሆን የመጠጥ ውሃ አቅርቦትም ከቁፋሮ ስራ ውጭ ያለው የwater supply system አለመሰራቱ፤
- ከስኳር ኮርፖሬሽን ጋር ያለው ተጨማሪ መሬት የማግኘት ጉዳይ እስኪፈታ ክልሉ ሌላ ተለዋጭ መሬት የመለየት ስራ እየሰራ ይገኛል፡፡
- ከመሬት ጋር የተያያዘውን ችግር ለመፍታት ከሚመለከታቸው የክልል እና የፍደራል ባለድርሻ አካላት ጋር አፋጣኝ የውይይት መድረክ ለመፍጠር ቀጠሮ ተይዟል፡፡

### በጊዳቦ ኦሮሚያ ያጋጠሙ ችግሮች

- ለፕሮግራሙ እንዲዉል ከተወሰነው 5000 ሄ/ር መሬት ውስጥ 1050 ሄ/ር የተገኘ ቢሆንም ተጨማሪ መሬት አስለቅቆ ለፕሮግራሙ እንዲዉል ማድረግ አለመቻሉ
- በጸጥታ እግር ምክንያት አስፈላጊ የግንባታ ቁሳቁሶች ወደ ሳይት በወቅቱ ማቅረብ አለመቻሉ አጠቃላይ አፈጻጸሙ ላይ መዘግየትን መፍጠሩ (በኮንትራቱ እቅድ መሰረት አጠቃላይ የግንባታ ስራው ሙሉ ለሙሉ አለመጠናቀቁ፤

- በዋናነት ወጣቶቹ ባለው መሬት ተጠቅመው በዝናብ የተወሰነውን ቦታ ማልማት እንዲጀምሩ አለመደረጉ እንደ ተግዳሮት ተወስደዋል

**የተሰጠ መፍትሄ**

- በመሬት ልታ ዙሪያ ከክልል ባለድርሻ አካላት ጋር ላሰለሰ ውይት እየተደረገ በመሆኑ በቀጣይ ተጨማሪ መሬት የሚገኝበት እድል እንደሚኖር ገምግመናል
- ከጸዋታ ችግር ጋር በተያያዘ ከክልሉ ባለድረሻ አካላት በተለይም ከአባያ ወረዳ ጋር በመነጋገር መፍትሄ እየተሰጠው በመሆኑ የግብአት አቅርቦት ችግር መፍታት ተችሏል፡፡

## በአፋር ተንዳሆ ያጋጠሙ ችግሮች

- የመሬት ዝግጅትን በተመለከተ የምንጣሮ ስር የተከናወነ ቢሆንም ርክብክብ ማድረግ አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት የተመነጠረው ቦታ መልሶ አረም እየበቀለመት በመሆኑ ለተጨማሪ ኪሳራ እና መዘግየቶች እየዳረገን መሆኑ
- ለካናል ጥገና ተብሎ የተያዘው በጀት አናሳ በመሆኑ የተመነጠሩትን መሬቶች በሙሉ ወደ ስራ ማስገባት የሚያስችል አለመሆኑ፡፡

**የተሰጠ መፍትሄ**

- ተጨማሪ የበጀት ጥያቄ ቀሪውን 2412.44 ሄ/ር መሬት ዉሃ ገብ እንዲሆን ለካናል እና የመስኖ ውቅሮች ጠገና የተያዘው በጀት ላይ በውለታ ክለሳ ላይ ተካቶ እንዲዝ ቢደረግ የሚል ሃሳብ የቀረበ ሲሆን አሁን ያለው ስራ ሲገባደድ የሚወሰነን ይሆናል
- ከተዘጋጀው መሬት አንጻር ተሳታፊ ወታቶች ቁጥር አናሳ በመሆኑ ተጨማሪ ምልመላ እና ስልጠና ተሰጥቶ ወጣቶችን አደራጅቶ ወደ ስራ ለማስስገባት እንቅስቃሴ ለማሰድረግ እቅድ ተይዟል

**በሶማሌ ክልል ያጋጠሙ ችግሮች**

- በክልሉ ከዘዚህ በፊት ስልጠና ወስደው የነበሩ 1057 ወጣቶችን ስራ ማስጀመር አለመቻል እና ረዥም ግዜ መውሰዱ
- በዋናነትም የመሬት ዘግጅት እና ተያያዥ ስራዎች በተለዩት ሳይቶች ላይ በወቅቱ መጠናቀቅ ባለመቻላቸው

**የተሰጠ መፍትሄ**

- በክልሉ ለወጣቶች መስኖ ፕሮጀክት ከተያዙት ፕሮጀክቶች ውስጥ የሽንሌ እና የጎዴ ፕሮጀክቶች ሰፋፊ ከመሆናቸውም በላይ ግዜ እየወሰዱ በመሆናቸው በ6 ወር ውስጥ ባካሄድነው የእቅድ ክለሳ መሰረት በግንባታ ክትትል እና ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ስረ ክትትል እንዲደረግባቸው መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-** ለፕሮጀክቱ ስራ ማስፈሚያ በ6 ወራት 116.68 ሚሊዮን ብር ታቅዶ 112.98 ሚሊዮን ብር ወይም የእቅዱን 96.8 በመቶ ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ ውሏል፡፡

**ክፍል ሁለት፡- የቆላማ አካባቢዎች ምርምርና ልማት ዘርፍ የ6 ወራት አፈጻጸም**

# ፕሮግራም 4፡ የክልሎችና አርብቶ አደር አካባቢዎች የኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራም የ6 ወራት አፈጻጸም

## የድጋፍና የክትትል እንዲሁም ከክልሎችና ከሌሎች ሴክተሮች ጋር ስላለው ቅንጅታዊ አሠራር

### ➢ የድጋፍና የክትትል አሠራርን በተመለከተ

የኮሚሽኑ መ/ቤት ለበጀት ዓመቱ ያቀዳቸውን ሥራዎች በተሳካ ሁኔታ ለማከናወን የክልሎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የጋራ ጥረት የሚጠይቅ በመሆኑ ተቋሙ የተለያዩ የድጋፍ፣ ክትትልና ግምገማ ስርዓቶችን በመዘርጋት ቀጥሎ በተገለጸው መልኩ ለመተግበር ጥረት አድርጓል:-

- በተቋሙ የሚካሄዱ ፕሮጀክቶች አተገባበር አስመልክቶ በበላይ ሃላፊዎች፣ በፕሮጀክት አስተባባሪዎችና ሌሎች በሚመለከታቸው ባለሙያዎች አማካኝነት ያልተቋረጠ የመስክ ጉብኝትና ክትትል በየጊዜው የሚደረጉ ሲሆን በፕሮጀክቶች ትግበራ ላይ ለሚከሰቱ ችግሮችም ወቅታዊ ምላሽ በመሰጠት ላይ ይገኛል፡፡ የመስክ መሃንዲሶችን በቋሚነት በሁሉም የግንባታ ፕሮጀክቶች ላይ በመመደብ የክትትል እና ቁጥጥር ስራዓቱን ለማጠናከር ጥረት ተደርጓል፡፡ በዋናው መስሪያቤትም የፕሮጀክቶች ክትትል ማድረግ እንዲቻል 4 የክትትል ቲሞችን ማደራጀት ተችሏል፣
- በተቋሙና በክልሎች በጋራ የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ውጤታማ ለማድረግ ከክልሎች፣ከዞኖችና ከወረዳ አስፈፃሚ አመራር አካላት ጋር በቅንጅት የተሠራ ሲሆን ይኸው ቅንጅታዊ አሰራርም ባልተቋረጠ መልኩ በቀጥይ ወራቶች ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡ በግማሽ አመቱ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት እየተከናወኑ የሚገኙ ፕሮጀክቶችን የክልሉ

ከፍተኛ አመራሮች በተገኙበት በሁለት የተለያዩ ጊዜያት ግምገማ ማድረግ የተቻለ ሲሆን የፕሮጀክቶቹን አፈፃፀም ለማሻሻል የሚያስችሉ ሁኔታዎች ላይ የጋር መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡ በተመሳሳይ በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ሥር እየተከናወኑ የሚገኙ ፕሮጀክቶችን በጋራ በመገምገም ፕሮጀክቶች ያጋጠማቸውን ችግሮች ለመፍታት ጥረት ተደጓል፣

- በበጀት ዓመቱ በፕሮጀክቶችና በመደበኛ ሊከናወኑ ከታቀዱ ተግባራት ውስጥ የበጀት ዓመቱ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት የተዘጋጀ ሲሆን አፈፃፀማቸውንም የበላይ ሃላፊዎችና የተቋሙ ሠራተኞች በተገኙበት በጋራ የመገምገም ስራዎች ተከናውኗል፣
- ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተፈጥሮ ሀብት፣ ማዕድንና መስኖ ዘርፍ ቋሚ ኮሚቴ በ2012 በጀት ዓመት አፈጻጸም ላይ በሰጠው ግብረ መልስ መሠረት በጥንካሬ የቀረቡት ይበልጥ ተጠናክረው እንዲቀጥሉና በድክመት የታዩት በዚህ በጀት ዓመት ባለው አፈጻጸም እንዲታረሙ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡
- ከሥራ ክፍሎች የሚቀርቡ የአፈጻጸም ሪፖርቶች ወጥነት እንዲኖራቸው የሪፖርት ማቅረቢያ ፎርማት/ቴምፕሌት እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡
- የዕቅድ፣ ክትትልና ግምገማ መረጃዎችን በማደራጀት በበጀት ዓመቱ ውስጥ ጥያቄ ላቀረቡ መ/ቤቶች የተፈለጉ መረጃዎች ተሰጥተዋል፡፡
- በሚካሄድ የድጋፍ፣ የክትትል እና ግምገማ ስርአት መሠረት ተገልጋይ የሚያነሳቸውን ችግሮች በመለየትና አፋጣኝ ምላሽ በመስጠት ተገልጋዩን የዕቅዱና የትግበራው አካል የማድረግ ስራዎች ተሰርተዋል፣
- በፕሮጀክቶች የግንባታ እንቅስቃሴ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በወቅቱ መፍታት እንዲቻል የቴክኒክ እና ስቲሪንግ ኮሚቴዎች ተቋቁመው ተገቢውን እገዛ ሰጥተዋል፡፡
- በአገር ደረጃ የተፈጠረውን የሲሚንቶ አቅርቦት ችግር ለመቅረፍ በውሃ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር በኩል ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሁለት ጊዜ ደብዳቤ እንዲፃፍ በማድረግ ለፕሮጀክቶቹ ቅድሚያ እንዲሰጥ ጥረት ተደርጓል፣
- ኮቪድ-19 በክልሎች ላይ ሊያሳድር የሚችለውን የምርት እጥረት ጫና ለማቀነስ ለክልሎች 5,910 ከፍተኛ እና መካከለኛ አቅም ያላቸውን ፓምፖች በ692 ሚሊዮን ብር በመግዛት ድጋፍ ተደርጓል፣
- የሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ የኮሚሽኑ፣ የተቋራጭ እና የአማካሪ ድርጅቶች የበላይ አመራሮች በተገኙበት ለሦሰት ጊዜ የሦስትዮሽ ውይይቶችን በሚኒስቴር መ/ቤቱ/በኮሚሽኑ የመሰብሰቢያ አዳራሽ የተደረገ ሲሆን ይህንንም አጠናክሮ ለመቀጠል ታቅዶ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ለሦስተኛ ጊዜ በተካሄደው የሦስትዮሽ ስብሰባ ላይም ሁሉም ተቋራጭ ድርጅቶች በበጀት ዓመቱ ሁሉም

ፕሮጀክቶች የተሻለ አፈፃፀም እንደሚኖራቸው ቃል የገቡ ሲሆን ይህም በኮንትራቱ መሰረት ክትትል እንደሚደረግበት ስምምነት ላይ ተደርሷል፣

- ከተቋራጭ ድርጅቶች ጋር በተደረገው ተደጋጋሚ ውይይቶች በፕሮጀክተች ላይ የሚታየውን ዝቅተኛ አፈፃፀም ማሻሻል እንዲቻል በመስክ ላይ የፕሮጀክት ማኔጅመንት ቲሙን እንዲያስተካክሉ ተደርጓል (ወልመል መስኖ ልማት ፕሮጀክት /ሎት-2/ እና የመገጭ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት)፡፡ እንዲሁም የመገጭ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት የግንባታ ሥራ በሦስት የተለያዩ ፕሮጀክት ማኔጀሮች እንዲመራ ተደርጓል፡፡
- የተቋሙን የሰው ሃይል ፍላጎት ለማሟላት 75 ክፍት መደቦች ላይ ማስታወቂያ ወጥቶ በ54 የስራ መደቦች ላይ የሰው ሃይል ቅጥር ተፈጽሟል፡፡

➢ **ከሌሎች ተቋሞች ጋር ያለው ቅንጅታዊ አካሄድና አፈጻጸም**

- በኮሚሽኑ አማካኝነት በተለያዩ ቦታዎች የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ውጤታማ ለማድረግ ከክልሎች፣ከዞኖችና ከወረዳ አስፈፃሚ አካላት ጋር በጋራ በመመካከር፣ በመደጋገፍና ችግሮችን በጋራ የመፍታት ሥራዎች የተከናወኑ ሲሆን ይኸው ቅንጅታዊ አሰራርም ተጠናክሮ እንዲቀጥል ተደርጓል፣
- ከተቋራጭ፣ ከአማካሪና ከባለድርሻ አካላት ጋር (ክልል፣ወረዳና ቀበሌ ድረስ ያለውን አመራርና ተጠቃሚ ማህበረሰብ በማሳተፍ) በየሶስት ወሩ የምክክርና የግምገማ መድረክ እየተዘጋጀ በፕሮጀክቶች አፈጻጸም ሂደት የሚስተዋሉ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን የመለየትና ጠንካራ ጎኖችን ይበልጥ በማጠናከር እና አሉታዊ ጎኖችን በማሰወገድ በሂደትም ያጋጠሙ ችግሮችን በጋራ ለመፍታት ጥረት ለማድረግ ታቅዷል:: የጋራ ምክክሮች ከፍ ባለ ደረጃ (ክልልና ዞን አመራሮችን ጨምሮ) በየሶስት ወሩ የሚካሄድ ሲሆን የኮሚሽኑ አመራሮችና ፕሮጀክት አስተባባሪዎች ከአማካሪዉ እና ከተቋራጩ የስራ ኃላፊዎች ጋር በጋራ በመሆን በየወሩ በፕሮጀክቶች ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ላይ ግምገማ እንዲያካሂዱ ተደርጓል::
- ከፕላንና ልማት ኮሚሽን ጋር በተቋሙ የአምስት አመት (2013-2017) ዕቅድ ዝግጅት ዙሪያ በቅንጅትና ተናብቦ የመስራት ሥራዎች ተከናውኗል፡፡
- ከገንዘብ ሚ/ር እና ከውጭ ጉዳይ ሚ/ር ጋር በልማት ትብብሮችና ፈንድ በማፈላለግ ዙሪያ አስፈላጊ የሆኑ ስራዎችና ጥረቶች ተደርገዋል፣
- ከምርምር ማዕከላት እና ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር ትስስር እና ቅንጅት በመፍጠር የአጭርና የረዥም ጊዜ የአቅም ግንባታ ስራዎች ለመስራት ጥረቶች ተደርገዋል፣
- ከአካባቢ፣ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ጋር በአረንጓዴ ልማትና በCRGE ትግበራ ዙሪያ በጋራ ተቀናጅቶና ተናብቦ ለመስራት ጥረቶች ተደርገዋል፡፡

## III. በበጀት ዓመቱ 6 ወራት በማጠቃለያ ምዕራፍ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- በበጀት ዓመቱ ሊተገበሩ የታቀዱ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የማጠቃለያ አፈፃፀም ሪፖርት ተዘጋጅቶ በከፍተኛና መካከለኛ አመራሩ እና በየዳይሬክቶሬቱ ባሉ ፈፃሚዎች ግምገማ ከተካሄደ በኋላ ወደሚመለከታቸው የበላይ አካላት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡
- በተደረገው ግምገማ መሠረት በአፈፃፀም ወቅት የተከሰቱ ችግሮችን በመለየትና እነዚህም በቀጣይ የሚስተካከሉበትን አሰራርና አካሄድ በማስቀመጥ ያልተከናወኑ ሥራዎችን በዕቅድ ውስጥ አካቶ ለመስራት አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡
- ከፕሮጀክቶች ትግበራ ጋር በተያያዘ ከተለያዩ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰሩ ተግባራት አፈፃፀም ያሉበትን ደረጃ በመገምገም በጥንካሬ የተስተዋሉት ይበልጥ ተጠናክረው እንዲቀጥሉና በድክመት የተለዩትን መቅረፍ በሚቻልበት ሁኔታ ላይ አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡
- በቀጣይ ወራቶች በዘርፉ የተሻለ ለውጥ ማምጣት እንዲቻል ትኩረት የሚሻቸው ጉዳዮች ተለይተው እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡

## IV. ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

- ከገንዘብ ሚኒስቴር ለበጀት አመቱ የተፈቀደ በጀት በጊዜ ሰሌዳው መሠረት እንዲለቀቅና በወቅቱ ስራ ላይ እንዲውል ማድረግ፣
- የተመደበ በጀትን ለውጤታማና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ መጠቀም፣
- የተቋሙን የማስፈጸም አቅም ደረጃ ለማሻሻል በብቁ የሰው ኃይልና በማቴሪያል ማሟላት እንዲሁም በዘርፉ ለተሠማሩ ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠትና የተሻለ አፈጻጸም ካላቸው አገራት ጋር የልምድ ልውውጥ እንዲኖራቸው ጥረት ማድረግ፣
- በዘርፉ የጥናት፣ ዲዛይን እና የግንባታ ስራዎች ላይ ለሚሠማሩ የአገር ውስጥ አማካሪዎችና ተቋራጮች አቅም ግንባታ ላይ ድጋፍ ማድረግ እንዲሁም ልምድ ካላቸው የውጪ ተቋራጮችና አማካሪዎች ጋር በጥምረት (Joint venture) የሚሠሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
- ወደግንባታ የሚገቡ ፕሮጀክቶች ጨረታ ከመውጣቱ በፊት የአዋጪነት ጥናታቸው በባለሙያ ተገምግሞ በትክክል መሬት ላይ መውረድ መቻላቸውንና አሳታፊ መሆናቸውን በመለየት ወደ ስራ የሚገቡበትን ስርዐት መንደፍና መፈጸም፣
- ፕሮጀክቶች በታቀደው ጊዜ፣ በጀትና ጥራት ደረጃ ተከናውነው እንዲጠናቀቁና ለተጠቃሚዎች እንዲደርሱ የሶስትዮሽ አሰራርንና አሳታፊ ዐቅድ ማዘጋጀት እንዲሁም የቴክኖሎጂ አጠቃቀምና አስተዳደር ስርዐትን ማስፈን፣

- ፕሮጀክቶችን በቢሮና በመስክ ያላሰለሰ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ሥራዎቻቸው ከዕቅድ ወደኋላ የሚቀሩ ፕሮጀክቶች ካሉ የማካካሻ ዕቅድ በማዘጋጀትና በትርፍ ሰዓትና በሺፍት በመስራት ዕቅዳቸውን እንዲያሳኩ ማድረግ፣
- በየፕሮጀክቱ የተጠቃሚ ዜጎች፣ የህዝብ አመራርና የፕሮጀክት ተዋንያን የጋራ የመሠረተ ልማት ኮሚቴ በማቋቋም ሥራዎች የሚገመገሙበትና ሁሉም አካል ለችግሩ መፍትሄ የሚሆንበትን ሥርዐት መዘርጋት፣
- ኮሚሽኑ በሚገነባቸው የመስኖ አውታሮች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ወይም መሰል የማህበራዊ ችግሮች እንዳይከሰቱ በመሠረተ ልማቱ ግንባታ ጥቅምና ፋይዳ ዙሪያ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የክልል፣ ዞንና ወረዳ አመራሮች እና ለህብረተሰቡ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ መስራትና እገዛና ትብብር እንዲያደርጉ ማድረግ፣
- አካባቢው ላይ የሚደረጉ ያለአግባብ ስራ ማስቆም፣ የመሰረተ ልማት ስራዎችን ማፍረስና ስርቆት የመሳሰሉት ችግሮች እንዳይከሰቱ ከጸጥታ አካላት ጋር ተቀናጅቶ መስራት፣
- የመሬት አቅርቦትና የግንባታ ግብዐት የሚመረትባቸውን ቦታዎች በሚፈለገው ፍጥነት ለተቋራጮች እንዲፈቀድ ማድረግ፣
- ለልማት ተነሺዎች ተገቢውን ካሣ በወቅቱ ለመክፈል ተሻሽሎ የወጣው የካሣ አዋጅ መመሪያ በፍጥነት ወደ ታች እንዲወርድ ግፊት ማድረግ፣
- የግሉ ዘርፍ በመካከለኛና ሰፋፊ የመስኖ ልማት ላይ በስፋት እንዲሰማራ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር እና ድጋፍ ማድረግ
- የሚነደፉ የመካከለኛና ሰፋፊ የመስኖ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ስርዓተ ፆታን ያገናዘቡ እንዲሆኑ ማድረግና እንደ አግባቡ በሚገነቡ ተቋማት ሴቶች ከፍተኛ ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሁኔታ ላይ ትኩረት መስጠት
- በፕሮጀክቶች የሚከናወኑ የግንባታ ተግባራትን እንደፕሮጀክቶቹ ሁኔታ በመከፋፈል ከአንድ በላይ በሆኑ ተቋራጮች ማከናወን፣
- ነባር የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶችን አስፈላጊውን ርብርብ በማድረግ አጠናቆ ወደ ልማት መስገባት፣
- አዲስ የሚጀመሩ ፕሮጀክቶች ዋናው ስራ ከመጀመሩ በፊት ግንባታ የሚካሄድበትን የመሬት አቅርቦት ጉዳይ አስቀድሞ ማጠናቀቅ፣
- በየፕሮጀክቱ የግብአቶች እጥረት (የሰው ሃይል፣ ማሽነሪ፣ ወዘተ) እንዳይከሰት ተገቢውን ክትትል ማድረግ፣
- በበጀት ዓመቱ የግንባታ ስራ የማይሰራበትን መሬት /Working corridor/ ለተማሩ ወጣቶች የመስኖ እርሻ እንዲውል ማድረግ፣

- ለወጣቶች መስኖ ልማት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ባለድርሻዎችን በማስተባበርና በመቀናጀት መፈፀም፣
- የወጣቶች መስኖ ከሂደት /process/ ወጥቶ በተጨባጭ ወደ ስራ የሚገባበትን አቅጣጫ ማስቀመጥ፣
- በመስኖ ቴክኖሎጂ አርሶ አደሩ እና የግል ባለሀብቱ ተጠቃሚ እንዲሆን እስከ ታችኛው አስተዳደር በጋራ መስራት፣
- ተቋሙ ከፍተኛ የመሠረተ ልማት ግንባታ እና መጠኑ ከፍተኛ የሆነ በጀት የሚያንቀሳቅስ ቢሆንም የተመደበለት የደመወዝ ስኬል ተመሳሳይ ሥራ ከሚያከናውኑ ድርጅቶች ያነሰ በመሆኑ ላሉትና ሌሎች ብቁ ባለሙያዎችን ከገበያ ላይ መቅጠር እንዲቻል የተቋሙ የደመወዝ ስኬል የሚስተካከልበትን መንገድ ማመቻቸት፣
- በዘርፉ በሁሉም ደረጃ ውጤታማነትን ለማረጋገጥ እንዲሁም ወቅታዊ የአፈፃፀም ሪፖርቶችም ሆኑ መረጃዎች በሚፈለገው ጥራት፣ወቅት፣አይነት ማግኘት እንዲያስችል የተጠናከረ የድጋፍ፣ ክትትል፣ ግምገማና ግብረ መልስ ስርዓትን በመዘርጋት የሚተገበር ይሆናል፡፡